**DSpace Institution**

**DSpace Repository** **http://dspace.org**

Ethiopian Languages and Literature - Amharic Thesis and Dissertations

2016-01

# þÿ5 E `p (!è sxÍs(@• èpÍ”u 5+Î}

þÿ(õ¤u, 5+ð

http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/15583

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

# ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

## ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ- አማርኛ- ትምህርት ክፍል

የአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ ድህረ ምረቃ ፕሮግራም


# ስላቅ በተመረጡየጌታቸውታረቀኝ የተውኔት ስራዎች


በ

ረድኤት አስራደ



ሰኔ 2015 ዓ.ም

ባሕር ዳር

# ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

## ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ- አማርኛ- ትምህርት ክፍል

### ስላቅ በተመረጡ የጌታቸው ታረቀኝ የተውኔት ስራዎች

ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፣ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነፅሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

አማርኛ ሥነፅሁፍ ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

በ

ረድኤት አስራደ

አማካሪ ፡- ዶ/ር ስንታየሁ ገነት

ሰኔ 2015 ዓ.ም

ባሕር ዳር

# መግለጫ

ስላቅ በተመረጡ የጌታቸው ታረቀኝ የተውኔት ስራዎች በሚል ርዕስ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል ለአማርኛ ስነ ፅሁፍ ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩንቨርሲቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም፡፡ ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸው መረጃዎችን በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ረድኤት አስራደው | ________ | 07/10/2015 |
| የተማሪው ስም | ፊርማ | ቀን |

# ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

# ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

# የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍ

# ጥናቱን ያረጋገጠው አካል መግለጫ

ስላቅ በተመረጡ የጌታቸው ታረቀኝ የተውኔት ስራዎች በሚል ርዕስ በአጥኚዋ ረድኤት አስራደው ለሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ፅሁፍ የተደረገውን ጥናት በደንቡ መሰረት እያነበብኩ ማማከሬን እያረጋገጥኩ ለቃል ፈተና እንዲቀርብ ስምምነቴን እገልፃለሁ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ዶ/ር ስንታየሁ ገነት | __________ | 07/10/2015 |
| የአማካሪው ስም | ፊርማ | ቀን |
| ዶ/ር ሰሎሜ ዘውዳለም | ___________ | 07/10/2015 |
| የትምህርት ክፍሉ ሀላፊ ስም | ፊርማ | ቀን |

## ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

## ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

እኛ ስማችን ከታች የተዘረዘረው የፈተና ቦርድ አባላት ስላቅ በተመረጡ የጌታቸው ታረቀኝ የተውኔት ስራዎች ውስጥ በሚል ርዕስ በረድኤት አስራደው የቀረበውን የመመረቂያ ፅሁፍ ፈትነን የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የመመረቂያ ፅሁፍ መስፈርትን ያሟላ መሆኑን እናረጋግጣለን፡ ፡

### የፈተና ቦርድ አባላት

| | | |
|---|---|---|
| ______________________ | __________ | ______________ |
| የውጪ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
| ______________________ | __________ | ______________ |
| የውስጥ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
| ______________________ | __________ | ______________ |
| የፈተናው ሰብሳቢ ስም | ፊርማ | ቀን |

# ምስጋና

ባለመሰልቸት፣በትግስት እና ከልብ በመነጨ ድጋፍ ጥናቱ የተሳካ እንዲሆን ላልተለዩኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ስንታየሁ ገነት ከልብ የመነጨው ምስጋናዬ ይድረስ፡፡

ዉድ መምህሮቼ ዶ/ር አንተነህ አወቀ፣ ዶ/ር ሂሩት አድማሱ፣ ዶ/ር አስቴር ሙሉ፣ዶ/ር ተስፋየ ዳኛው፣እና ዶ/ር ተ/ማርያም ገ/መስቀል በትምህርት ቆይታየ ስላደረጋችሁልኝ መልካም ነገር ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ትምህርቱን ስጀምር ላበረታህኝ እና ከጎኔ እስከ መጨረሻው ለነበርከው ውዱ ባለቤቴ አለባቸው ደጀን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ልጆቼ ቢታንያ አለባቸው እና አንኪዮን አለባቸው የእናትነት ጊዜየን ቀንሼ ለትምህርት ሳውለው በረብሻችሁ ስለተባበራችሁኝ እና እንድጠነክር ተስፋ ስለሆናችሁኝ እወዳችኋለሁ፡፡ እናቴ ፀጋነሽ ተስፋው ፣ወንድሜ በሀይሉ አስራደው፣እህቴ ጥሩአለም ስማቸው እህቴ ትግስት አስራደው፣እህቴ ዉዴ ባይነስ፣ ከጎኔ ሳትለዩ ስለነበራችሁ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በስራየ እንዳላሳብብ የቢሮ ስራየን በመሸፈን ላገዛችሁኝ ለባህር ዳር ከተማ ትምህርት መምሪያ ለአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ቡድን ባለሙያዎች ምስጋናዬ ከልብ ይድረሳችሁ፡፡

እንዲሁም ነጻ የትምህርት እድል እንዳገኝ ላደረገኝ የአማራ ክልል ሴቶች ፌድሬሽን በተለይ ለወ/ሮ ብርሀን ሁልጊዜ ምስጋናዬ ከልብ ይድረስ እላለሁ፡፡

በመጨረሻም የኔ ስኬት ሁሌ የምትናፍቀው ውዱ አባቴ ዛሬን አብረኸኝ ባትኖርም ይኸው ለዚህ ደርሻለሁ፡፡ ነፍስህን በአጸደ ገነት ፈጣሪ ያኑራት እያልኩ፤ ይህ ጥናት መታሰቢያ ነቱ ለውድ አባቴ ለአቶ አስራደው አያሌው ይሁንልኝ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ በተመረጡ የጌታቸው ታረቀኝ የተውኔት ስራዎች ዉስጥ ስላቅ በምን መልኩ እንደተከሰተ  ማሳየት ነዉ፡፡ በተውኔት ስራዎች ላይ የጥናት ክፍተት መኖሩ እና ተውኔቶቹን በስላቅ ማንጸሪያ መመልከት አመቺ ሆኖ መገኘቱ እንደመነሻ ሃሳብ በመያዝ ተጠንቷል፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ ጥናት በመሆኑ ቴክስቶችን በተገቢው መልኩ በመፈተሸ የገላጭ ስልት እና የቴክስት ትንተናን በመጠቀም ተከናውኗል፡፡ በጥናቱም የስላቅ የመሳለቂያ ዘዴዎች በርካታ ቢሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ከስላቅ የመሳለቂያ ዘዴዎች ውስጥ አለመመጣጠን፣ ማጋነን፣ማዛባት እና ምጸት ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ በተመረጡት ተውኔቶች ውስጥ መስተካከል ያለበት ጉዳይ በስላቅ መንገድ ቀርቦ የታየበት ነው፡፡ በተጨማሪም በተውኔቶቹ ውስጥ ለስላቅ የቀረበው ጉዳይ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ይዘት ያለው መሆኑ በስፋት ተቃኝቶበታል፡፡ በተለይም የትኛው አካል ለስላቅ እንደቀረበ በስፋት ተቃኝቶበታል፡፡ በስላቁ የተገኘውግኝት መንግስት፣ ፖለቲከኞች፣ረጅ  ድርጅቶች ፣የውጭ መንግስታት፣ስግብግብ ግለሰቦች፣ ከስርአት የወጡ የሀይማኖት አባቶች ፣አስመሳይ ምእመናን  እና ሌሎችም ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ህፀፆች በማንሳት ከችግራቸው እንዲውጡ እና መልካም ስራ እንዲሰሩ ትችት ተሰጥቶበታል፡፡

## ማውጫ

ምዕራፍአንድ...1
መግቢያ...1
1.1 የጥናቱ ዳራ ...1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ...4
1.3 የጥናቱ ዓላማ ...5
1.4. የጥናቱ ጥያቄዎች ...5
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ...5
1.6 የጥናቱ ወሰን ...6
1.7 የጥናቱ ዘዴ ...6
1.7.1 የተውኔቶቹ አመራረጥ መስፈርት ...7
1.7.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና ሂደት ...7
1.7.3 የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችና ሂደት ...7
1.8. የጥናቱ አደረጃጀት ...7
ምዕራፍ ሁለት ...9
ክለሳ ድርሳናት...9
2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ...9
2.1.1 የስላቅ ምንነት ...9
2.1.2 የስላቅ አነሳስ እና ዋናዋና ጸሀፍቶች ...12
2.1.3 የስላቅ አላማ...15
2.1.4 የስላቅ ተግባራት...16
2.1.4 የስላቅ ባህርያት ...18
2.1.5 የስላቅ ዘዴዎች...20
2.1.5.1 ማጋነን...21
2.1.5.2 ማዛባት ...22
2.1.5.3 አለመመጣጠን...22
2.1.5.4 ማጥቃት...23
2.1.5.5 ምጸት...23
2.1.5.6 ፓሮዲ...24
2.1.5.7 ተገላቢጦሽ...24

2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 25
ምዕራፍ ሦስት ........ 27
የስላቅ ትንተና በተመረጡ ተውኔቶች ውስጥ ........ 27
3.1 የስላቅ ዘዴዎች ........ 27
3.1.1 ማጋነን ........ 27
3.1.2 ማዛባት ........ 37
3.1.3 ምጸት ........ 46
3.1.4 አለመመጣጠን ........ 52
3.2 የይዘት ትንተና ........ 59
3.1.1 ፖለቲካዊ ስላቅ ........ 59
3.1.2 ማህበራዊ ስላቅ ........ 66
ምዕራፍ አራት ........ 69
ማጠቃለያ ........ 69
አባሪዎች ........ 71
አባሪ 1፡ የሳጥናኤል አበሳ አጽመ ታሪክ ........ 71
አባሪ 2፡ ቤጌዮሎጅ (የልመና ጥበብ) አጽመ ታርክ ........ 72
አባሪ 3 የሽልማቱ ተውኔት አጽመ ታሪክ ........ 73
አባሪ 4 ስለተውኔቶቹ የህትመት ዘመን ማብራርያ ........ 74
አባሪ 5 የቃላት የመገኛ ቋንቋቸው ፍች ........ 75
ዋቢጽሁፎች ........ 76

# ምዕራፍአንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ሥነ-ጽሁፍ በሰው ልጅ ታሪክ ለረጅም ዘመናት የቆየ ኪነጥበብ በመሆኑ ብዙ ሀሳቦች የተሰነዘሩበት፣ብዙ ክርክሮችና ምርምሮች የተደረጉበት መስክ ነው፡፡ ስለምንነቱ፣ ስለአፈጣጠር ሚስጥሩ፣ ስለሚያካትታቸው ነገሮች፣ በሰዎች ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖና ስለሚሰጠው አገልግሎት የዘርፉ ምሁራን ብዙ ጽፈዋል፤ ምርምሮችንም አድርገዋል (ዘሪሁን፤1996፣1)፡፡ ስነ-ጽሁፍ በባህሪዉ ድንበር ተሻጋሪ በመሆኑ በርካታ ርዕሰ ጉዳዮችንና ንድፈ-ሃሳቦችን ከተለያዩ የሙያ መስኮች ወስዷል፤ ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎችና የሌላ ዘርፍ ባለሙያዎችም ከሙያቸው መንፈስ እና አቅጣጫ እየተመለከቱት የየራሳቸውን ትርጓሜ ሰጥተውት እናገኛለን፡፡

ላዛር ስለ ስነ ጽሁፍ ሲገልጹ 5 ዋና ዋና ነጥቦችን ያነሱ ሲሆን ጠቅለል ተደርገው ሲውሰዱ እንደ ሚከተለው ተገልጾ እናገኛለን፡፡ ስነፅሁፍ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ስሜት እና ሀሳብ ነው፡፡ ስነፅሁፍ አንባቢዎች ወይም አድማጮች ግላዊ ምላሻቸውን እንዲያጭሩ የሚያደረግ የቋንቋ አጠቃቀም ነው፡፡ ስነፅሁፍ የፈንጠዝያ፣ የሀዘን ፣ የስሜት ፣ የራዕይ ዓለምን በቃላት ማስቀመጥ ነው፡፡ ስነፅሁፍ ማለት ሰዎች ዘንድ መድረሻ፣ ሁኔታዎችን በተለያየ መንገድ ማመልከቻ፣ ሃሳብን፣ አዕምሮን፣ ራሳችንን የበለጠ ማሳወቂያ ነው፡፡ ስነፅሁፍ ማለት የብዙዎችን አመለካከት፣ አስተሳሰብና አተያይ በማጤን ራሳችንን በተሻለ መንገድ ማወቅ ነው፡ :(ላዛር፤ 1993፣ 1)

ሥነ-ጽሁፍ ሀሳባችንን እና ስሜታችንን የምንገልጽበት ሰፊ ማእቀፍ ሲሆን በውስጡ ከያዛቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱ ተውኔት ነው፡፡ተውኔት በመድረክ ላይ የሚመደረክ የሰውን ልጅ የህይዎት ገጠመኝ በተዋናኝ አማካኝነት የሚቀርብበት ነው፡፡ ፈንታሁን(1999፣3) ተውኔት (ድራማ) የሚለው ቃል የተገኘው "ድራን" ከሚለው የግሪክ ቃል እንደሆነ ትርጉሙም ማድረግ ወይም መከወን ማለት እንደሆነ እና ከሰው ልጆች እውነተኛ ድርጊት የሚከተብ የኪነ ጥበብ ዘረፍ እንደሆነ ሲገልጽ፤ አያልነህ (1992፣3) በበኩሉ "ድራማ የሚለው ቃል በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ ትርጉሞች የሚሰጡት ጥበብ ሁኗል፡፡ ገፀ ባህሪያት በተላበሱ ተዋንያን የሚተረጎም

ቃል ተውኔት ድራማ መባሉን አብዛኛዎቹ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ ድራማ ከሀዘን እስከ ስቃይ፣ ከአስቂኝ እስከ ቧልታይ ያሉትን የቴያትር ዘርፎች አጠቃሎ የያዘ የኪነጥበብ ዘርፍ ነው" በማለት ይገልጻሉ፡፡

ተውኔት፣ ትያትርና ድራማ የሚሉትን ስያሜዎች በተለዋዋጭነት የምንጠቀምባቸው ስያሜዎች ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ ዕድገት ዉስጥ የተዉኔት ሥራዎች ጉልህ ስፍራ አላቸው፡፡ ይህን ሀሳብ አንተነህ እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

> በኢትዮጵያ የአማርኛ ስነጽሁፍ ታሪክ ተውኔት የተጀመረው በበጅሮንድ ተክለ ሃዋርያት ተክለ ማርያም በ1913ዓ.ም የተጻፈው ፋቡላ (የአውሬዎች ኮሜዲ) በቀዳሚነት ይጠቀሳል፡፡ ተክለሀዋርያት ተክለ ማርያምን ተከትለው ብዙ ጸሐፍት ተፈጥረው እንደነበር ፤በተለይም ዮፍታሄ ንጉሴ፤ መላኩ በጎሰው፤ ሐዲስ አለማየሁና ስንዱ ገብሩ ዋናዋና የዘመኑ ጸሀፍት እንደነበሩ ይገልጻል (አንተነህ፤ 2001) ፡፡

ተውኔት እንደ ስነጽሁፍ እደገት ከሌሎች የስነጽሁፍ ዘውጎች ጋር አብሮ እየወደቀ እየተነሳ እስከ አሁን ድረስ ለተመልካች በመድረክ ላይ እየቀረበ ይገኛል፡፡ ተውኔት ከመመድረኩ ባሻገር ስለምንነቱ የተለያዩ አሳቤዎች ሲሰነዘሩ ቆይተዋል እየተሰነዘረም ይገኛል፡፡

ተውኔት የሰው ልጆችን የዕለት ተዕለት ገጠመኝ አስመስሎ የሚያቀርብ፤ በጊዜና በቦታ ተወስኖ የሚመደረክ ፤የሰውን ልጅ ባህል እና እሴት የሚያንጸባርቅ፤ የገጸ ባህርያት ታሪክ በተዋናኝ አማካኝነት የሚቀርብበት፤ በዝርው እና በመናባንብ መልኩ የሚነገር፣ ከሰው ልጅ እውነተኛ ድርጊት የሚቀዳ ነው በማለት (ደበበ፤1973፣ፈንታሁን፤1999 እና አያልነህ፤1992) ያብራራሉ፡፡

ተውኔት ከሰው ልጅ የእለት ከእለት እንቅስቃሴ የሚቀዳ፤የሌሎችን ባህሪ፣ ሁናቴ እና ንግግር ለጊዜው ወርሶ ለተዝናኖት ፋይዳው ሲባል አንድ አይነት ተግባርን ከቋንቋ ጋር አገናኝቶ የመጫወት ጉዳይን የሚመለከት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ዘሪሁን (1996፣161) ይህንን በማፅናት የተዉኔትን ከሌሎች የስነ-ጽሑፍ ዘዉጎች ሲያስረዱ "ተውኔት በደራሲው ወይም በፅሀፌ ተውኔቱ በተመረጠ ጠባብ የቦታ እና የጊዜ ክልል ህይወትን በድርጊት በመድረክ ላይ ስለሚቀርብ ከቀሩት የስነ-ፅሁፍ ዘሮች ይበልጥ ለስሜታችን ቅርበት አለው"ሲሉ ይገልጻል፡፡

ተውኔት የተለያዩ የአጻጻፍ ዘዴዎችን የሚጠቀም ሲሆን  ከእነዚህ የአጻጻፍ ዘዴዎች መካከል አንዱ ስላቅ (satire) ነው፡፡ ለጸሀፍት ስላቅን በተውኔት፣ በልቦለዶች፣ በቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፣ በስነ-ግጥሞች፣ በመጽሄቶች እና በካርቶን ፊልሞች እንደ አንድ ቴክኒክ መጠቀም የተለመደ ነው፡፡ ስላቅ አጀማመሩ በጥንት ሮማውያን ተቺዎች እና ጸሐፊዎች ይጠቀሙበት እንደ ነበር ይነገራል፡፡ አሪስቶፋነስ የጥንት ስላቃዊ ግጥሞችን የጻፈ የግሪክ ባለቅኔ ነበር፡፡ በጣም ታዋቂው ስራው ሊሲስታራታ (Lysistrata) እንደ ነበር (ሉክ፤2022) ይገልጻል፡፡

ስላቅ አጀማመሩ በጥንት ሮማውያን ተችዎች ቢሆንም ጸሀፍት ስላቅን የሚጠቀሙት አንድ ነገር እንዲስተካከል ለማድረግ እንደሆነ ዩጎሊኒ (2016፣2) እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ “ጸሀፍት በስራቸው ውስጥ ስላቅን የሚጠቀሙት አንድን ሰው ወይም የሆነ ነገር ትምህርታዊ በሆነ መንገድ ለመተቸት ሲፈለጉ እንደ ቧልት ፣ ማጋነን ፣ ምፀት) እና የመሳሰሉትን እንደ መሳሪያነት ይጠቀማሉ፡፡ የስላቅ ዋና አላማ ማሳቅ ሳይሆን እያዋዙ ትላልቅ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ እና መሰል ችግሮችን በማቅረብ ችግሮች እንዲስተካከሉ ለማድረግ ነው”፡፡

ስላቅ አንድን ችግር ለማስተካከል ሲባል ጥበባዊ በሆነ መንገድ የምንገስጽበት የስነ ጽሁፍ ዘዴ ነው፡፡ ስላቅ መሳለቂያ በሆነ በማንኛውም የስነ-ጽሁፍ ወይም የጥበብ ስራ ላይ የሚተገበር ቃል ነው፡፡ በማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ትችት ውስጥ ጉልህ ተግባራት አሉት፡፡ በስነ-ጽሁፍ ውስጥም እንደ ከንቱነት፣ ግብዝነት፣ እና ስሜታዊነት ያሉ እኩይ ተግባራትን ያጋልጣል፡፡ ስለሆነም እንዲህ ባለው መጋለጥ ምክንያት ለዉጥ ለማምጣት ጥረት ያደርጋል፡፡

የዚህ ጥናት ስራዎች ባለቤት የሆነው ጌታቸው ታረቀኝ ለህዝብ ያበረከታቸው ከ20 በላይ የተውኔት ስራዎች አሉት፡፡ ጌታቸው የተውኔት ጸሀፊ ሲሆን በመጽሀፍ መልኩ አዘጋጅቶ ለህዝብ ለንባብ ያበቃቸው የተዉኔት ስራዎቹ፡- *የእንስሳት ጥናት እና ሌሎች የቲያትር ጨዋታዎች፡(2007ዓ.ም) በታተመው መጽሀፉ ውስጥ ((የሳጥናኤል አበሳ(2007)፣ ሽልማቱ(1983)፣ የመጨረሻው ሰርግ (በ1983 ዓም* በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና በኋላም በአ.አ. ማዘጋጃ ቴአትር ቤት ‹እዝለ ጥበብ› ወይም ‹ዝክረ ጥበብ› ከተባለ የሙዚቃና ተዉኔት ፕሮግራም ጋር ለተመልካች የቀረበ)፣ *ቤጊዮሎጅ (የልመና ጥበብ1984)፣ ማሙሽ(1985)፣ የእንስሳት ጥናት(ያልታየ)እና እስረኛው ንጉስ(ቀ/የ))፣* በአንድ መድብል የታተሙ ስራዎቹ ሲሆኑ፤ *ሆቴሉ( 2019)፣ አልወለድም እና የሙት ምስክር(እ.ኤ.አ 2012* በግጥም መልኩ የተዘጋጀ መነባንብ)፣*ወጥመዱ(2013)፣እስረኛ ንጉስ፣ የአቤቶልጅ እያሱ(እ.ኤ.እ2015)፣ አባባ*

*መንግስቱ(እ.ኤ.አ2018)፣ ኮንዶ(2009ዓ.ም ከመጽሀፉ የተወሰደ) መልእክተ ወዛደር፣ደራሲው በሰማይ ቤት(ቀ/የ)፣ ጀግናዋ ሴትዮ(ቀ/የ) ካሊጉላ(ቀ/የ)፣ በርባን(እ.ኤ.አ 2018)፣ ክፍት የስራ ቦታ(ቀ/የ)* እና ሌሎችም ስራዎቹም ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በዚህም ጥናት *የሳጥናኤል አበሳ(2077)፣ ቢጊዮሎጅ(2013) እና ሽልማቱ(1983)* የጥናቱ ትኩረት ሲሆኑ በተውኔቱ ውስጥ ምን አይነት የስላቅ ዘዴ እንደተንጸባረቀ፣ ይዘቱ ምን ላይ እናዳተኮረ እና ለስነጸሁፉ ምን አይነት ስነጽሁፋዊ ፋይዳ እንዳለው ተዳሰበታል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህንን ጥናት ለማጥናት መሰረታዊ ከሆኑ ምክንያቶች ውስጥ የመጀመሪያው ገፊ ምክንያት፤ የጌታቸው ከ20 በላይ ተውኔቶች ያሉት ሲሆን ተውኔቶቹ ሳቅን እያጫሩ በፌዝ መልኩ የተበላሸውን ለማስተካከል ጥረት የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ስለሆነም ተውኔቶቹን በሚገባ በመፈተሽ የሚሳለቁት ምን ጉዳይ ለማስተካከል እንደሆነ ለማወቅ ከፍተኛ ጉጉት እንዲያድርብኝ አድርጓል፡፡ ስለዚህ የጌታቸውን ስራዎች ስላቅን እንደማንጸሪያ በመጠቀም ማጥናት አመቺ መሆኑ የመጀመሪያው ገፊ ምክንያት ነው፡፡

ሁለተኛው ገፊ ምክንያት የጥናት ክፍተት መኖሩ ነው፡፡ ተዉኔት ከክዋኔዉ ባሻገር ያሉት የተዉኔት ጽሑፍ ዘዉጎች የሥነ-ጽሑፍ ጥናት ትኩረቶች መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ማለትም የተዉኔት ጽሑፍም ሆነ ሌሎች የሥነ-ጽሑፍ ስራዎች የሚመነጩት ከጸሐፊ ተዉኔቱ ወይም ከደራሲዉ እይታና እምቅ ምናባዊ ፈጠራ ነዉ፡፡ ይህንን ፈጠራ አጥንቶ ለተደራሲ ማድረስ የዘርፉ ምሁራን ተቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ ነገር ግን በአማርኛ ቋንቋ የተፃፈ የተዉኔት ሥራን ተተኳሪ አድርገዉ የተሰሩ ጥናቶች በበቂ ሁኔታ አልተጠኑም፡፡ ይህ ክፍተት እንዳለም አጥኝዋ "የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ ቅኝት" ላይ በነበራት ትምህርት የተውኔት ጥናት ላይ ከሌሎች የስነጽሁፍ አይነቶች አንጻር ክፍተት እንዳለ አስተውላለች፡፡ ስለሆነም ተዉኔት ከተጀመረበት ዘመን እና ካለዉ ስነጽሁዊ ፋይዳ አንጻር በስፋት አለመጠናቱ በዘርፉ ያለውን የጥናት ክፍተት ለመሙላት ሌላው ገፊ ምክንያት ነው፡፡ በተጨማሪም ጌታቸው ብዙ የተውኔት ስራዎችን ለመድረክ ያበቃ ቢሆንም ስራዎቹ ግን እስከሁን ያልተጠኑ እና ያልተዳሰሱ ናቸው፡፡ ስራዎቹ በርካታ ሂስ ነክ ጽንሰ ሃሳቦችን ለመዳሰስና ለመመርመር ጥሩ መድረክ ሆነዉ ማገለገል ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ስራዎቹ ቢጠኑ ለስነጽሁፍ እድገት የሚያበረክቱት ፋይዳ ቀላል አይደለም፡፡

ይህንን አጉልቶ ማሳየት የአጥኝዋ ፍላጎት ነው፡፡አጥኝዋ ያነሳችው እስካሁን በአጥኚዎች ያልተተኮረን የጽሀፍቱን ስራዎች መሆኑ ሌላው ምክንያት ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በተመረጡ የጌታቸው ታረቀኝ የተውኔት ስራዎች ዉስጥ ስላቅ እንዴት እንደተከሰተ ማሳየት ነዉ፡፡

የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ፡-

- በተዉኔቱ ዉስጥ የተንጸባረቁትን የስላቅ ዘዴዎች መለየት
- በተውኔቱ ውስጥ የቀረበውን የስላቅ ይዘት መተንተን፤
- ስላቆቹ ለተዉኔቱ ዉበት ያበረከቱትን ስነጽሁፋዊ ፋይዳ መፈተሽ

## 1.4. የጥናቱ ጥያቄዎች

የጥናቱን ዝርዝር አላማዎች ለማሳካት የሚያግዙ ጥያቄዎች፡-

1. በተዉኔቱ ዉስጥ ጎልተው የተንጸባረቁት የስላቅ ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?
2. በተውኔቱ ውስጥ የቀረበውን የስላቅ ይዘት ምንድን ነው?
3. ስላቆቹ ለተዉኔቱ ዉበት ያበረከቱትን ስነጽሁፋዊ ፋይዳ ምንድን ነው?

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ስላቅ በተውኔቱ ዉስጥ እንዴት እንደ ተንፀባረቀ እና ጥቅም ላይ እንደዋለ በስፋት የሚዳስስ እና ለተውኔቱ ያበረከተው ስነጽሁፋዊ ፋይዳ የሚተነተንበት ስለሆነ ጥናቱ ሁለት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ይህን ጥናት አግኝተው ለሚጠቀሙበት አጥኚዎች የጥናት ክፍተት የሚሞላ ሲሆን፤ የሌሎችን ጸሀፍት ስራዎች ለመፈተሽ ስላቅን እንደ ማንጸሪያ አድርገው ለመጠቀም መነሻ በመሆን ያገለግላል፡፡ በተለይም በስላቅ ዙሪያ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ አጥኚዎች እንደ መረጃ ምንጭነት አልያም እንደ መነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ሁለተኛው ጠቀሜታ ስላቅን በተዉኔት *ሥራዎች* ዉስጥ ስለሚፈትሽ የተዉኔት ድርሰቶች በ*ሥነ-ጽሑፍ* ዘርፍ እንዲጠኑ አስተዋፅ*ዖ ያ*ደር*ጋ*ል፡፡ ይህም በተዉኔትና በሌሎች የ*ሥነ-ጽሑፍ* ድርሰቶች *መ*ካከል *ያ*ለዉን *መ*ስተ*ጋ*ብር የሚዳስስ ስለሆነ ተዉኔት ተተኳሪ የጥናት ጉዳይ እንዲሆን *ያ*ግዛል፡፡ በዘርፉ *ያ*ለዉንም የዕዉቀት ክፍተት ይሞላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከጌታቸው *ታ*ረቀኝ ተውኔቶች ውስጥ *የሳጥናኤል አበሳ(2007)፣ ቤጊዮሎጅ(2013) እና ሽልማቱ(1983)* በሚሉት ስራዎቹ ላይ ይሆናል፡፡ በእርግጥ ጸሀፌ ተውኔቱ በርካታ የተውኔት ስራዎች እንዳሉት ይታወቃል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ግን ሦስቱ ተዉኔቶች ላይ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ከተመረጡት በስተቀር ሌሎች ስራዎቹ የጥናቱ ተተኳሪ አልተደረጉም፡፡ ለጥናቱ መተንተኛ የተመረጠዉ ንድፈ-ሃሳብ ስላቅ የተሰኘው ንድፈ ሃሳብ ነው፡ ፡ የስላቅ የተለያዩ የማቅረቢያ ዘዴዎች እና መሰረታዊ ነገሮች ያሉት ቢሆንም በዚህ ጥናት በዋናነት የታዩት ማጋነን፣ ማዛባት፣አለመመጣጠን እና ምጸት ናቸው፡፡ ይህ ጥናት የተዉኔት ስራዎች ላይ ቢያተኩርም የተዉነቶቹ ትንታኔ ያጠነጠነዉ የድርሰት ጽሑፎቹን መሰረት በማድረግ ሥነ-ጽሑፋዊ ሂስ ማድረግ ላይ ነው፡፡ ስለዚህ ጥናቱ የተዉኔቶቹን ክዋኔ ወይም ሌሎች ከመድረክ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ጉዳዮችን አልተመለከተም፡፡ ነገር ግን በጽሁፍ ስለ ተዋንያን ድርጊት የተገለጸ ፅሁፋዊ ማብራሪያ አብሮ ትንታኔ ተደርጎበታል፡፡

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ንዑስ ክፍል የተካተቱት የተውኔቶቹ አመራረጥ መስፈርት፣የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እና የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ናቸዉ፡፡

ጥናቱ የስነ ጽሁፋዊ ጥናት እንደ መሆኑ መጠን ቴክስት ትንተና እና አይነታዊ ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ የስላቅ ንድፈ ሀሰብ ላይ በመመርኮዝ ለምርምር በተመረጠዉ *የሳጥናኤል አበሳ(2007)፣ ቤጊዮሎጅ(2013) እና ሽልማቱ(1983)* ተውኔት ላይ ጥልቅ ንባብ እንዲሁም ዝርዝር ትንተና እና ትርጓሜ በጥቅም ላይ ውሏል፡፡

### 1.7.1 የተውኔቶቹ አመራረጥ መስፈርት

በዚህ ጥናት ተግባራዊ የሆነው የተውኔቶች አመራረጥ ዘዴ ዓላማ ተኮር የአመራረጥ መስፈርት ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የተመረጡት የጌታቸው ታረቀኝ ስራዎች ስላቅ የሚንፀባረቅባቸው መሆናቸው እና ካሁን በፊት በስላቅ ማንጸሪያነት ጥናት ያልተደረገባቸው በመሆናቸው እና ለትንተና አመቺ በመሆናቸው ተመራጭ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል፡፡

### 1.7.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና ሂደት

ጥናቱ ሁለት አይነት የመረጃ ምንጮች ማለትም ቀዳማይ ና ካልዐይ ተጠቅሟል፡፡ በቀዳሚ የመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት የጥናቱ ቀጥተኛ ተተኳሪ የሆኑት *የሳጥናኤል አበሳ፣ ቤጊዮሎጅ እና ሽልማቱ* የተሰኙት የጌታቸው ታረቀኝ ተውኔቶች ናቸው፡፡ ካልአይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ ስለ ስላቅ ንድፈ ሃሳብ የሚያትቱ ጥናታዊ ጽሑፎችና መጻሕፍት፣ ድኅረ ገፆች እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ሰነዶች ናቸው፡፡

### 1.7.3 የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችና ሂደት

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መተንተኛነት የዋለው ዘዴ በዋናነት የቴክስት ትንተና ነው፡፡ በተጨማሪም አጥኚዋ የመረጠቻቸውን ተውኔቶች ጥልቅ ንባብ አድርጋለች፡፡ ይህ ጥናት ተመሳሳይ ጥናቶች ከተፈተሹ በኋላ የንድፈ ሃሳብ ማእቀፍ ለማስቀመጥ የስላቅ ንድፈ ሀሳብ በስፋት ተነቧል፡፡ በተለይም የስላቅ ምንነት፣ታሪካዊ ዳራው፣ዋናዋና ጸሀፍቶቹ፣የስላቅ ዘዴው፣ የስላቅ ባህርያት እና ሌሎች ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች በስፋት ተነበዋል፡፡ የጥናቱ ዋነኛ ማዕከል የሆነዉን “የሳጥናኤል አበሳን”፣ “ቤጊዮሎጅ” እና “ሽልማቱ” ተውኔት ጽሁፍ በጥልቀት ከተነበበ በኋላ ለትንተና የተመረጠዉ ታሪክ ራሱን ችሎ በሚቀመጥ የጥናት ክፍሎች ትንተናና ትርጓሜ ተሰጥቶበታል፡፡

### 1.8. የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ በአራት ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ ሲሆን የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ እንዲሁም የጥናቱ አደረጃጀት የተካተቱበት

ሆኗል፡፡ ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ በምዕራፍ ሦስት ደግሞ በክለሳ ድርሳን የተነሱ ተያያዥ ጽሁፎችንና ንደፈ-ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ ትንታኔ የሚቀርብበት ሆኗል፡፡ ምዕራፍ አራት በጥናቱ የተደረሰበትን ውጤት የሚሰፍርበት ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ክፍል ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጽሁፎች ለጥናቱ ማስኬጃና መቀንበቢያ የሚያገለግሉ ንድፈ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡ ይህ ምዕራፍ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ስለ ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ የሚከልስ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ዝምድና ያላቸው ቀደምት ጥናቶች የተዳሰሱበት ክፍል ነው፡፡

## 2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ

### 2.1.1 የስላቅ ምንነት

ስለ ስላቅ ምንነት የተለያዩ ምሁራን ትርጓሜ ሰጥተውት እናገኛለን፡፡ ባህሩ(2006) ስላቅ "ቀልድን፣ ፌዝን፣ ዝብብትን፣ ማላገጥን እና የንቀት ንግግርን " እንደሚገልጽ ሲያስረዱ፡፡ የኢትዮጲያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል (1993፣161) ሀሳቡን በመደገፍ ስላቅ ፌዝን፣ለገጥን፣ቀልድን እንደ ሚገልጽ ያስረዳል፡፡

በሌላ በኩል ናይት (2004፣25) እንዳስቀመጠው ስላቅ (Satire) የሚለው ቃል የመጣው "ሳቱር" ከሚለው የላቲን ቃል ሲሆን ትርጉሙም "ጥሩ ምግብ" ማለት ነው፡፡ "ላንክስ ሳቱራ" በሚለው ሐረግ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ትርጉሙም "ብዙ ዓይነት ፍራፍሬዎችን የያዘ ምግብ" ማለት ነው፡፡ እነዚህ ቃላቶች ከስላቅ ፍቺ በጣም የራቁ ቢመስሉም የጥንት ሮማውያን ተቺዎች እና ጸሐፊዎች ዛሬ ስላቅ ብለን የምናውቀውን ነገር ለማመልከት ይጠቀሙበት ነበር፡፡

ስላቅ ማኅበራዊ አስተያየት ወይም ትችት ቀልድን በተላበሰ እና ባማረ ቋንቋ የሚሰጥበት መንገድ ሲሆን፣ የተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ዘውጎች (ለምሳሌ ተዉኔቶች፣ አጫጭር እና ረጃጅም ልቦለዶች፣ ግጥም እና አስቂኝ የዜና መጣጥፎች ወይም ድርሰቶች) ስላቅን እንደ ቴክኒክ ይጠቀማሉ፡፡ የስላቅ ለዛ ከተራ ጨዋታ አዘል አዝናኝ አስተያየት እስከ የሰላ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ትችት ሊያካትት እንደሚችል (ከርናን፤1973፤ፌይንበርግ፤1967፣547) ይገለፃሉ፡፡ በተጨማሪም ዩጎሊኒ(ይህንኑ ሲያስረዱ ስላቅ ከጥንታዊው ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያለ በመሆኑ ዘርፈ ብዙ እና ጊዜ የማይሽረው መሆኑን በመጥቀስ የሚከተለዉን ብለዋል፡፡

> ስላቅ አንድን ሰው ወይም የሆነ ነገር ትምህርታዊ በሆነ መንገድ ለመተቸት እንደ ቧልት፣ ማጋነን ወይም ምፀታዊ መሳሪያዎችን መጠቀም ነው። የህዝብ ተወካዮች፣ፖለቲከኞች፣ የፖለቲካ ቡድኖች፣ ታዋቂ ፈላስፋዎች እና ታዋቂ ሰዎች ከተለመዱት የስላቅ ኢላማዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። (ዩጎሊኒ፤ 2016፣5)

ስላቅ ብዙውን ጊዜ በቴሌቪዥን ድራማዎች እና ሥነ-ጽሑፎች ውስጥ ይገኛል። በካርቶን ፊልሞች እና በሌሎች የእይታ ጥበቦች ዉስጥም አገልግሎት ሲሰጥ ይስተዋላል:: በርካታ የስነ-ጽሁፍ ተቺዎች ለስላቅ ቋሚ ፍቺ ለማምጣት አስቸጋሪ እንደሆነ በተደጋጋሚ የሚገልጹ ቢሆንም፣ የሚከተለዉ ከድረ-ገጽ የተወሰደ የስላቅ ብያኔ አብዛኞችን የሚያስማማ ትንታኔ ሊሆን ይችላል፡-

> ስላቅ በማናቸውም ተንኮል ወይም እኩይ ተግባር ላይ የሚሰነዘር ጥቃት ወይም ትችት፣ ወይም ደራሲው እንደ አደገኛ ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሥነ ምግባራዊ ወይም ማኅበራዊ ደረጃዎች የሚያያቸው ትችቶችን የሚሳይ ነው። ስላቅ በተለይ በዘመነ-አብርሆት (Enlightenment) ወቅት ጥቅም ላይ ይዉል የነበረ ተወዳጅ ቴክኒክ የሆነ ፣ በዚህ ጊዜ አንድ አርቲስት ጥበብን እንደ መስታወት በመጠቀም ለማህበረሰቡ በማንፀባረቅ ክፋተትን ማረም ይችላል ተብሎ ይታመን ነበር። ሰዎች አሽሙርን ሲመለከቱ እና ስህተታቸው በተዛባ ነጸብራቅ ሲጎላ ሲያዩ ባህሪያቸው ምን ያህል አስቂኝ እንደሆነ ይገነዘባሉ ከዚያም በራሳቸው ውስጥ ይህን ዝንባሌ ያስተካክላሉ። *[https://www.studymode.com/essays/The-Definition-Of Satire1333906. Html]*

ስላቅን ለሀይማኖታዊ፣ፖለቲካዊ፣ስነ መግባራዊ እና ማህበራዊ ብልሽቶችን ለማስተካከል ሲባል አገልግሎት ሲሰጥ እንደ ነበር እና ለስላቅ የቀረቡት ቡድኖችም ሆኑ ግለሰቦች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ የሚያደርግ ትልቅ መሳርያ ነው።

አብዛኞቹ የስላቅ ፀሐፍቶች ልዩነታቸውን ለመግለጽ የተለያዩ እና አንዳንድ ጊዜ ተቀራራቢ ቃላትን ይጠቀማሉ። ለምሳሌ፡- ለቀልድ የሰው አኳኋንን በኩረጃ (burlesque) ፣ ምጸት እና የታወቀን ስራ በአስቂኝ መንገድ መኮረጅ (parody) ከስላቅ ጋር መስተጋብር ይፈጥራሉ። ስላቅ ብዙውን ጊዜ አሽሙርን ይጠቀማል፤ በቁጣም ከነገሮች ጋር የማይጣጣሙ ትክክለኛ

ሁኔታዎችን ለማመልከት ያገለግላል (Pollard፤ 1970፣ 3፣ Nichols፤1971፣14፣18፣ Fletcher፤1987፣ix)፡፡ በማለት ሲገልጹ አጋቤይ (2021፣433) በበኩሉ ስላቅን ሲገልፅ "ስላቅ የአንድን ተቋም ወይም ሰው ጉድለቶች ለማሾፍ ወይም ለማጋለጥ በማሰብ ጥቅም ላይ የሚዉል የአጻጻፍ ዘዴ ነው፡፡ እንዲስተካከል ያሰበውን ነገር ደራሲዉ ቧልት በሆነ እይታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ስለሆነም ስላቅ ብልህነትን እና ጥበብን የሚፈልግ የጥበብ አይነት ነው" በማለት ይገልጻል፡፡

ስላቅ አንድን ማህበረሰብ ለማንቃት እና እየደረሰበት ያለውን ተጽእኖ ለመጠቆም እንዲሁም ችግሩን ለራስ ጥቅም በማሰብ በህብረተሰቡ ላይ ችግር በሚፈጥሩ አካላት ላይ የሰላ ትችት ለማድረግ ጥቅም ላይ የሚውል ዘዴ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ስላቅ የግለሰቦችን እና የህብረተሰቡን ተንኮል እና እኩይ ተግባር ለማጋለጥ እና ከተቻለም ለእንደዚህ አይነት የተሳሳቱ ድርጊቶች ፍትህ ለመስጠት ምጸተኛ እና ተቺ መሆን የስላቅ  ባህሪ መሆኑን ከምሁራን ሀሳብ መረዳት ይቻላል፡፡

ይህንን ሀሳብ በማጠናከር ናይት (2004፣15) ሲገልጹ "ስላቅ የተለያዩ አይነት ድንበሮችን ያልፋል፣ በእነዚያ ድንበሮች በሁለቱም በኩል ካሉ መሰረታዊ ነገሮች ጋር ለመጫወት እና የተለያዩ ግዛቶችን እና አመለካከቶችን ለማስተካከል ጥቅም ላይ ይውላል" በማለት ሲገልጹ ሉክ በበኩሉ ይህን ሀሳብ በመደገፍ እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

> "ስላቅ የማህበረሰቡን ድክመቶች አልፎ ተርፎም እኩይ ምግባሮችን ለመጠቆም ማጋነን ፣ ምጸትን ፣ ቧልት ወይም አሽሙርን መጠቀም ነው፡፡ ይላል እዲሁም በማህበረሰቦች ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን የመተቸት እና የማጋለጥ መንገድ ነው፡፡ በማለት ሲያብራራ ስኬታማ ስላቆች ብዙውን ጊዜ ትኩረታቸው ፖለቲካ ላይ ነው ይላል" (ሉክ ፤2022፣)

ስላቅ የሰው ልጅ ተፈጥሮን እስከ ትችት እና ንቀት የሚይዝ ዘውግ እና የስነ-ጽሁፍ መሳሪያ ነው፡፡ ስላቅ  ብዙውን ጊዜ ፖለቲካ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ጸሃፊዎች ምጸትን፣ ቀልድን እና ማጋነንን በመጠቀም የተሳካ ስላቅን ይፈጥራሉ፤ ስላቅ በሰው ልጅ ተፈጥሮ እና ተቋማት ላይ በመተቸት ለውጥ ለማምጣት የሚሰራ ነው፡፡ ስላቅ ሁሌም ወቅታዊ መሆኑን እና ደራሲው መጋለጥ ወይም መወገዝ እንዳለበት ብሎ ያሰበዉን ጉዳይ እያዋዛ የሚገልጽበት ስልት ነው፡፡ ግሪን (1927፣60) በበኩሉ ይህን ሀሳብ በመደገፍ እንዲህ

በማለት ይገልጻል"ስላቅ ህብረተሰቡን ለማገዝ አገልግሎት ላይ የሚዉል የስነ-ጽሁፍ ዘዴ ነው:: ከሌሎች ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ተቃውሞዎች የሚለየው በምፀቱ ሲሆን ተሳላቂዎች ስህተትን ለማስተካከል ምፀት እና ማጋነን ይጠቀማሉ"::

ስላቅ ምጸታዊ እና ብልሃተኛ በመሆኑ የሰውን ልጅ እኩይ ተግባር እና ውሸት የሚያጋልጥ፣ ብርታትን የሚሰጥ፣ በሳቅ እያዋዛ ለወጥ ለማምጣት የሚያገለግል የስነ-ጽሁፍ ዘዴ ነው:: የሰው ልጆችን አሰራር እና የሰውን አስተሳሰብ ለማሻሻል የሚጠቅም የአጻጻፍ ስልት ነው ማለት ይቻላል። ጸሀፍት በስራቸው ውስጥ ስላቅን የሚጠቀሙት አንድን ሰው ወይም የሆነ ነገር ጥበባዊ በሆነ መንገድ ለመተቸት ሲፈለግ እንደ ቧልት፣ ማጋነን፣ ምፀት እና የመሳሰሉትን እንደመሳሪያነት ይጠቀማሉ። የስላቅ ዋና አላማ ማሳቅ ሳይሆን እያዋዙ ትላልቅ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ እና መሰል ችግሮችን በማቅረብ ችግሮች እንዲስተካከሉ ማድረግ ነው።

## 2.1.2 የስላቅ አነሳስ እና ዋናዋና ጸሀፍቶች

ስላቅ የጀመረው በጥንታዊ ግሪክ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሲሆን ጸሀፍቶች ሳቅን እያጫሩ ማህበራዊ ወይም ስነ-ጽሁፋዊ ትችት ይሰጡ እንደ ነበር ይነገራል። ስላቅ በጥንታዊቷ ሮም በስፋት ይጠቀሙበት እንደ ነበር እና የስላቅ አባቶች ሆራስ እና ጁቬናል ስማቸው ለሁለቱ መሰረታዊ የስላቅ አይነቶች ሰጥተው እንዳለፉ (አፐልቢ፤1997፣584) ይገልጻል። በተጨማሪም "ስላቅ በአሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን አውሮፓ ውስጥ በጣም ተወዳጅ እንደነበረር በተለይም በእንግሊዝ ውስጥ የስላቅ "ወርቃማ ዘመን" የሚባለው የአሌክሳንደር ፖፐ እና ጆናታን ስዊፍት ዘመን እንደነበር አፐልቢ ያስረዳል።

የሮማውያን ደራሲዎች ሆራስ እና ጁቬናል ቀደምት ባህሪያቱን በመቅረጽ እንዲሁም በኋላ ላይ በኒዮክላሲካሊዝም ዘመን መነቃቃቱን በማነሳሳት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደነበራቸው ይገለጻል። ይህን ሀሳብ በማጠናከር Simpson (1954፣49)"የክላሲካል ዘመን ስላቅ፣ በተለይም ከጥንታዊው ሮም እና በአሥራ ስምንተኛው ክፍለ-ዘመን በብሪታንያ ትችት በአንጻራዊነት ችግር የሌለበት የአጻጻፍ ዘዴ እንደነበር"ይገልጻል።

የስላቅ አጀማመር ጥንታዊ ቢሆንም በዋናነት ስላቅ በአሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን የተስፋፋው በአስቂኝ ግጥሞች እና ድራማዎች ነው:: ተሳላቂዎች ግብዝነት፣ ትዕቢት፣ ስግብግብነት፣ ከንቱነትና ተንኮልን በማጋለጥ በከፍተኛ ደረጃ የዳበረውን ሥልጣኔ ከብልሹ

አሰራር ለማላቀቅ ይሰራበት እንደ ነበር አፐልቢ ይገልጻል። በተጨማሪም አፐልቢ ስላቅ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን በታዋቂነቱ የደበዘዘ ቢመስልም በ 20 ኛው ክፍለ ዘመን ፣ እንደገና የማንሰራራት አዝማሚያ እንደነበረው እና በ21ኛው ክፍለ ዘመን እንደገና እንዳበበ ይገልጻል።

**የስላቅ ዋና ዋና ጸሀፍቶች :-**

1. **ዴሲሙስ ጁኒየስ ጁቬናሊስ** (Decimus Junius Juvenalis)

ጁቬናሊስ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ እና በሁለተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ንቁ የሆነ ሮማዊ ገጣሚ ነበር። ተሳላቂ በመባል የሚታወቁት የአስቂኝ ግጥሞች ስብስብ ደራሲ ነው።

የጁቬናል ስላቆች ሁለት ዋና ዋና ጭብጦችን ይይዛሉ። ይኸውም በሮም ከተማ ውስጥ ያለው የህብረተሰብ ብልሹነት እና የሰው ልጅ ክፋት እና ጭካኔዎች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። በአንደኛው ስላቁ ጁቬናል መጥፎነትን ፣ ወንጀልን እና ሀብትን አላግባብ መጠቀም ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ተናግሯል ፣ ሁለተኛው ደግሞ ወንድ ግብረ ሰዶማውያን መነሻ በማድረግ ይሳለቃል።

የጁቬናል በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን በሮም ስለነበሩት የአይሁድ ሕይወት በርካታ ዘገባዎችን የሰጠው የጁቨናል ስላቅ እንደ ጄ. ጀስተር (J. Juster) እና በቅርቡ ደግሞ ፒር ናሖን (Pe-ter Nahon) ባሉ ምሁራን ዘንድ ስለ ጥንት የአይሁድ እምነት ጠቃሚ ምንጭ ተደርገው ይታዩ እንደነበር ነበር ይገለጻል።

2. **ኲዊንተስ ሆራቲየስ ፍላከስ** (Quintus Horatius Flaccus)

በእንግሊዘኛ ተናጋሪው ዓለም ሆራስ ተብሎ የሚታወቀው ኲዊንተስ ሆራቲየስ ፍላከስ በዘመኑ የሮማውያን ገጣሚ ነበር። ተጽእኖ መፍጠር የቻሉት Horatius ስራዎች Sappho, Epicurus, Phil-odemus የሚሉት ስራዎቹ እንደሆኑ ይነገራል።

ሆራስ በግጥም ህይወቱ ውስጥ ፖለቲካን፣ ፍቅርን፣ ፍልስፍናን እና ስነምግባርን በርካታ እርስ በርስ የተያያዙ ጭብጦችን ያነሳል። ሆራስ የ‹‹Odes› በተባለው ተከታታይ መጻሕፍ መሪ ሃሳቦች ወደ አዲስ ደረጃ እንዳደረሰ ይነገርለታል። “የሆራስ ስላቅን በጨዋታ፣ በዝግታ እና በማስተዋል ለውጥ ለማምጣት ይሞክራል” (አፐልቢ ፣1967፤584) በማለት ይገልጻል።

### 3. ጆርጅ ኦርዌል (George Orwell 1903—1950)

ስላቅ  በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን በፖለቲካ ፌዝ ተወዳጅነቱ ለውጥ የታየበት ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ እንደ "የቱብ ታሪክ" ያሉ የመጀመሪያዎቹን ስላቃዊ ጽሁፎች ተጽፈው ነበር፡፡ ኦርዌልም በዚህ ዘመን  የፍፁም አምባገነን መንግስታትን መቃወም የአስቂኝ ምሳሌ የሆኑ ልብ ወለዶችን ፃፈ፡፡ ምንም እንኳን የእሱ መጽሃፍቶች በራሳቸው አስደሳች ታሪኮች ቢሆኑም በህብረተሰቡ ውስጥ ስላለው ሁኔታ ብዙ የሚናገሩት ነገር ነበራቸው፡፡ ከእሱ ልብ ወለድ ውስጥ በስላቅ እውቅናን ያተረፈው Animal Farm (1945) የሚለው ስራው እንደነበር ይነገራል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ደራስያን ስላቃዊ ጽሁፎችን በመጻፍ የሚታወቁ ቢሆኑም የሮማ ገጣሚያን ሥራዎች ጋር በማመሳሰል ብዙ ተሳላቂዎች እስከ ዛሬ ድረስ ሆራቲያን ወይም ጁቬናሊያን የአጻጻፍ ስልቶችን ሲከተሉ ይስተዋላል፡፡

አብዛኞቹ የስላቅ ዓይነቶች በስላቅ ጽንሰ-ሀሳቦች በሰዋዊ የስነ-ጽሑፍ ትችት ውስጥ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ብዙ ዓይነት  የስላቅ ዓይነቶች ቢኖሩም ሆራቲያን ስላቅ እና ጁቨናሊያን ስላቅ በጣም ተወዳጅ የስላቅ ዓይነቶች ናቸው፡፡ በማለት  (Bogel፤2001፣ Feinberg፤1967፣ Highet፤ 1962፣ Knight፤2004፣ Sander፤1971፣ Simpson፤2003) ይገልጻሉ፡፡ የጁቨናሊያን እና የሆራቲያን ስላቆች ከፅንሰ-ሀሳብ አንጻር እና ከቴክኒኮቻቸው አንፃር ተቃራኒዎች ተብለው ይገለጻሉ፡፡ ይህን ሀሳብ በመደገፍ ሲንደር (1971፣254) እንደሚከተለው ይገልጻል "የሆራስ ስላቅ ከኮሚዲ ጋር የሚገናኝ ሲሆን፣ ጁቨናልስ ደግሞ ለትራጀዲ ቅርብ ነው፡፡ የሆራስ ስላቅ ሳቅ ሲቀሰቅስ፣ የጁቨናል ስላቅ ቁጣን ያነሳሳል…"፡፡

ሆራትያን ስላቅ ገራገር፣ አዛኝ የሆነ የስላቅ አይነት ነው፡፡ የሆራቲያን ስላቅ በአስቂኝ ዘዴ ተመልካቾች እንደ ተጫዋቾቹ በራሳቸው እንዲስቁ የመጠየቅ አዝማሚያ አለው፡፡ ሆራቲያን የሞራል መሻሻልን ለማምጣት በሳቅ እያዋዛ ስላቅን ይጠቀማል፡፡ የሆራቲያን ስላቅ ዝነኛ ምሳሌ የአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ገጣሚ አሌክሳንደር ፖፕ "The Rape of the Lock" ግጥም እንደ ምሳሌ ይነሳል፡፡ የሆራቲያን ስላቅ ከማህበረሰባዊ ጉዳዮች ይልቅ በሰዎች ላይ ያሉ ጉድለቶች ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ዋና ግቡ በትልልቅ ጉዳዮች ላይ ከማስተማር ይልቅ በተዛማጅ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በመመስረት ማዝናናት ነው፡፡ ሆራቲያን ስላቅ በጨዋታ እና አዝናኝ በሆነ መንገድ  ለውጥ ለማምጣት ይሞክራል፡፡ ሆራቲያን በተጫዋችነት መጥፎ ድርጊቶችን በጥበብ፣ በማጋነን፣ በብልሀት እና በቀላል ልብ ሰቀላ በማፌዝ ይወቅሳል፡፡

ሁለተኛው የጥንት የሮማ ተሳላቂዎች ጁቬናል የተሰየመው የጁቬናሊያን ስላቅ በመባል ሲሆን፣ ለስላቅ ትክክለኛ እና ትራጀዲ አቀራረብ ያለው ነው። (Highet፤1962፣Sander፤1971)። ጁቬናሊያን ስላቅ ንቀት እና ውግዘት የሚደርስበት የከፋ፣ መራር የሆነ የስላቅ አይነት ነው። የጁቨናሊያን ስላቅ ብዙውን ጊዜ በህብረተሰብ ወይም በቡድን ውስጥ ያሉ ጉድለቶችን፣ኢፍትሃዊ ድርጊቶችን ወይም ሌሎች ችግሮችን ለማጋለጥ የሚያገለግል የፖለቲካ ፌዝ ነው። ብዙውን ጊዜ በድምፀ ከሆራቲያን ስላቅ የበለጠ ከባድ ነው። ጁቬናሊያን ብዙውን ጊዜ መራራ እና ብልሹ አሰራርን ወይም የብቃት ማነስን በንቀት እና በንዴት ይወቅሳል።

ሆራቲያን ስላቅ ለማስተማር ሲሞክር የጁቬናሊያን ስላቅ ይቀጣል። በተለይ ማህበራዊ "ክፋተቶችን" ወይም ብልሹ አሰራርን በመጠየፍ፣ በንዴት እና በአረመኔያዊ ፌዝ ይወቅሳል፤ ብዙውን ጊዜ ተስፋ አስቆራጭ ማህበራዊ ጉዳዮችን ለመተቸት የሰላ ስላቅን በመጠቀም ይታወቃል፤ ከቀልድ ይልቅ በሥነ ምግባር ላይ ያተኮሩ ስላቆችን ይጠቀማል። ከፖለቲካዊ ፌዝ ጋር የተያያዘ የስላቅ አይነት ነው። (አፐልቢ ፤1967፣54)።

ጆናታን ስዊፍት በተባለው ታዋቂው መጽሃፉ ጉሊቨር ትራቭልስ ላይ የጁቬናሊያን ስላቅ ይጠቀማል። የጁቨናሊያን ስላቅ "የጨለመውን ሳቅ ያነሳሳል። ብዙውን ጊዜ መራራ እና ሙስና ወይም ብቃት ማነስን በንቀት እና በንዴት ይወቅሳል" (አፐልቢ፤1967) በማለት ሲገልጽ ፍርየ (1971a) በበኩሉ ይህን ሀሳብ በመደገፍ "ጁቬናል ስላቅ ጠንከር ያለ ቃና ሲኖረው፤ የሆራቲያን ስላቅ በተዋዛ ቋንቋ አጠቃቀም በመጠቀም ስነመግባርን ለማምጣት ጥረት ያደርጋል። የስዊፍት ስራዎች የጁቬናል ስላቅ ምሳሌ ሲሆን ለሆራቲያን ስላቅ ምሳሌ የፖፕ ስራዎች እንደ ምሳሌ ይነሳሉ" በማለት ይገልጻል ።

### 2.1.3 የስላቅ አላማ

የስላቅ ዓላማው መሳለቂያ በሆነ በማንኛውም የስነ-ጽሁፍ ወይም የጥበብ ስራ ላይ የሚተገበር ነው። የሚከተለዉ ከድረ-ገጽ የተወሰደ ብያኔ አብዛኞችን የሚያስማማ ትንታኔ ሊሆን ይችላል።

> ስላቅ አንድን ሰው ወይም የሆነ ነገር ትምህርታዊ በሆነ መንገድ ለመተቸት እንደ ቀልድ፣ ማጋነን ወይም ምፀታዊ መሳሪያዎችን መጠቀም ነው። የህዝብ ተወካዮች፣ ፖለቲከኞች፣የፖለቲካ ቡድኖች፣ ታዋቂ ፍልስፍናዎች እና ታዋቂ ባህል ከተለመዱት የስላቅ ኢላማዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

[ https://liberalarts.oregonstate.edu/wlf/what-satire.]

በሌላ በኩል ይህንን ሀሳብ በማጠናከር ግሪን(1927፣61) ስለ ስላቅ አላማ እንዲህ ይላል “የስላቅ ተግባር መጥፎውን መወንጀል ወይም መልካሙን ማሞገስ፣ በጉድለቶች እና በጥሩዎች መካከል ያለውን አለመመጣጠን ማስተካከል ወይም ማስታረቅ ነው”። የስላቅ አላማ አንድን የታየ ጉድለት ማስተካከል ነው። ስላቅ አላማ እንዳለው ሁሉ የራሱ የሆነ ኢላማዎች አሉት። ስለስላቅ ኢላማ ከድህረ-ገጽ የተገኘ ብያኔ ስገልጽ “የስላቅ ኢላማ ከንቱነት፣ ግብዝነት፣ ሀይማኖት፣ ኅጠኝነት፣ የሰው ልጅ ምግባራት፣ ስሜታዊነት፣ ስግብግብነት፣ ዝነኛ አምልኮ፣ ፍቅረ ንዋይ፣ ከመጠን ያለፈ ኩራት፣ የትምህርት ማዳከም፣ ንቀት፣ ጭካኔ፣ ግድየለሽነት እና ስንፍናን ለማጋለጥ ያለመ ነው”በማለት [https://www.chsd1.org/cms/lib] ይገልጻል።

ተሳላቂዎች የሚቃወሟቸውን እምነትና መከራከሪያ ለመናድ ጨካኝ ወይም ኢሰብአዊ እንደሆኑ በማሳየት አቋማቸውን ያንጸባርቃሉ። ጥሩ ስላቅ ለማጥፋት ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ ችግሮችን ለማስተካከል ያለመ ገንቢ ጥበብ ነው። ስላቅ እራሱ የትችት አይነት ሲሆን ሰዎች በተፈጥሮቸው ድክመቶቻቸውን ማጉላት እና ማጋለጥን አይወዱም። ነገርግን የስላቅ ዋና አላማ የተደበቀን እኩይ ተግባር ማጋለጥ ነው። የስላቅ ጸሃፍቶች እና ፈጻሚዎች ሰዎችን የማጥላላት ወይም የማጋለጥ ዓላማ ይዘው ስላቅን እንደ መሳሪያ ሲጠቀሙበት ይታያል።

የስላቅ ዓላማ አንድን የተበላሸ ጉዳይ የማስተካከል እና ወደ ተሻለ ነገር መለውጥ ሲሆን የስላቅ ዋና ዋና ታላሚዎች የህዝብ ተወካዮች፣ ፖለቲከኞች፣ የፖለቲካ ቡድኖች፣ ታዋቂ ፈላስፋዎች፣ ባለሀብቶች፣ አርቲስቶች፣ የሀይማኖት አባቶች እንዲሁም ህዝብን የሚጎዱ ሙሰኞች ከስላቅ ኢላማዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

## 2.1.4 የስላቅ ተግባራት

ስላቅ አብዛኛውን ጊዜ በማህበራዊ ስምምነቶች ወይም በፖለቲካ የግለሰቦች እና ቡድኖች ላይ ያነጣጠረ ነው። ስላቅ በፌዝ መልኩ ስለ ዘመኑ ጠባያት፣ ፖለቲካ ወይም ባህሪ ለአንባቢዎች ጥቆማ ይሰጣል። ፖለቲካዊ ሽርሙጥና የስላቅ ንኡስ ዘውግ ነው። በሥነ ጽሑፍ ውስጥ፣ ፖለቲካል ስላቅ የሚያመለክተው በገሃዱ ዓለም ያሉ የፖለቲካ ጉዳዮች ወይም ምስሎች የሚጋለጡበት፣ የሚተቹበት ወይም የሚሳለቁበት እንደ ምጸት፣ ቧልት፣ ንፅፅር እና ማጋነን ባሉ ቴክኒኮች ነው። ስላቅ በአብዛኛው ግለሰቦችን፣ቡድኖችን ፣ተቋማትን፣ህብረተሰብን እና

በአጠቃላይ በሰው ልጅ ላይ የሚያነጣጥር ትችት ነው፡፡*ስላቅ የፖለቲካ ጉዳዮችን በመሳለቅ ለመተቸት ይጠቅማል*:: (*Bates.A ፣1906)*

*ፖለቲካ የሚለው ቃል በተለምዶ ከመንግስት እና ከህዝብ ፖሊሲ ጋር የተያያዘ ማንኛውም ነገር እንደሆነ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ፖለቲካዊ ስላቅ የሚመለከተው በስልጣን ላይ ያሉትን ቡድኖች ወይም ግለሰቦችን እንዲሁም ሀብትን በማከፋፈል እና ህጎችን በማውጣት ላይ ባሉ አካላት ላይ የሚሳለቅ ሲሆን በስላቅ ስልቱም ምጸትን እና ማጋነን በመጠቀም አንድን ሰው ወይም የሆነ ነገርን በማሾፍ ዋናውን እውነት ወይም ኢፍትሃዊነትን ለማሳየት እንደሚሞክር* (*ሃሪስ* ፣1990) *ይገልጻል፡፡ ይህን ሀሳብም* (https://study.com/learn/lesson/political-satire-overview-examples.html) *የተባለ ድህረገጽ ይደግፈዋል፡፡*

*በፖለቲካቅ ስላቅ ዋና ዋና ታላሚዎች የፖለቲካ ሰዎች ( ጠቅላይ ሚኒስትሮች እና ንጉሳዊ አገዛዝ)፣የፖለቲካ ቡድኖች (ኮንሰርቫቲቭ እና የሰራተኛ ፓርቲዎች)፣የፖለቲካ ጽንሰ-ሀሳብ ስርዓቶች (ካፒታሊዝም፣ኮሙኒዝም, ወዘተ.)፣የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም፣ በተለይም የፖለቲካ ሥርዓትን መሠረት ያደረጉ መዋቅሮች፣የፖለቲካ አቋም (የግራ ፖለቲካ፣ የቀኝ ክንፍ ፖለቲካ)፣ አመለካከቶች እና ጭፍን ጥላቻ (ትምክህተኝነት፣ ዘረኝነት) ተተኳሪ ናቸው፡፡*

*ለተወሰኑ ሰዎች ሳይሆን ለርዕዮተ ዓለሞች እና አመለካከቶች በሰፊው ያነጣጠረ የፖለቲካ ሽርሙር ሜኒፔያን ስላቅ በመባል ይታወቃል:: ሜኒፔን ስላቅ ከሰዎች ይልቅ አእምሮአዊ አመለካከቶችን እና ሀሳቦችን የሚያፌዝ እና የሚተች ምሁራዊ የስላቅ አይነት ነው::*

*የፖለቲካ ስላቅ አስፈላጊነት፤ በኃያላን ቡድኖች እና ተቋማት ውስጥ የሚፈጸመውን የስልጣን አላግባብ መጠቀም ለመተቸት የፖለቲካ መሳለቂያ ጠቃሚ መሳሪያ ነው:: ነገር ግን ተሳላቂዎች ተንታኞች ብቻ አይደሉም፤በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በሚሰነዝሩት ትችት የፖለቲካ ምህዳሩን የመቀየር እና ትልቅ ለውጥ የማምጣት አቅም አላቸው::*

*የፖለቲካ መሳለቂያ በባህሪው መቻቻል ወይም አለመቻቻል፣ የዜጎች ነፃነት እና የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ያንፀባርቃል :: በጠቅላይ ገዥዎች ስር በፖለቲካዊ ስርዓት ላይ የሚሰነዘር ማንኛውም ትችት እና በተለይም ጭቆናን ይታገዳል::*

*ሌላው የስላቅ ተግባር ማህበራዊ የሆኑ ጉዳዮች እንዲስተካከሉ መተቸት ነው:: ለተፈጥሮ እና ለማህበራዊ ሚናው ስላቅ በብዙ ማህበረሰቦች ውስጥ በታዋቂ ግለሰቦች እና ተቋማት ላይ*

ያፌዛል። የስላቅ ግፊት ማህበራዊ ውጥረትን የመፍታትን አቅም አለው። ስላቅ እንደ የአምልኮ ሥርዓት ያሉ ተቋማትን ለጸረ-ማህበረሰብ ዝንባሌዎች መግለጫ በመስጠት በህብረተሰቡ ዘንድ የተጋረጡ አፋኝ ገፅታዎች በማንሳት የሚሞግት ነው። ይህን ሀሳብ ራንኪን እንደሚከተለው ትገልጸዋለች።

> ስላቅ የአንድን ማህበረሰብ ማህበራዊ እና ባህላዊ ጉድለቶች ለማመልከት የታሰበ አስቂኝ ትችት ነው። ማኅበራዊ ስላቅ የሚያተኩረው በህብረተሰቡ በራሱ ገፅታዎች ላይ ሲሆን ይህም ወቅታዊ ሁነቶችን፣ ተስፋ ሰጪ አስተሳሰቦችን እና የፖለቲካ ተቋማትን ይጨምራል። ስላቅ በታዋቂው ባህል እና መዝናኛ ላይ ያተኩራል። ከጥንት ግሪኮች እና ሮማውያን የመነጨው ማኅበራዊ ስላቅ ለብዙ መቶ ዘመናት አለ። አሁንም በዘመናችን ለማህበራዊ ትችቶች ተወዳጅ ቴክኒክ ነው።(ራንኪን፣2023)

ስላቅ ፐለቲካዊ ጉዳዮችን እንደሚተች ሁሉ ማህበራዊ እና ባህላዊ ጉዳዮችን እያነሳ የሚተች ነው። በዚህም ትችቱ መስተካከል ያለበትን ጉዳይ በሳቅ እያዋዛ መስተካከል ያለበትን ጉዳይ የመገሰጽ ተግባር አለው።

### 2.1.4 የስላቅ ባህርያት

የስላቅ ባህርያት እና የስላቅ መሰረታዊ ነገሮች ያን ያህል ልዮነት ስሌላቸው ባህርያቱን እና መሰረታዊ ነገሮች ናቸው የሚባሉትን በዚህ ርእስ ስር የሚጠቃሉ ይሆናል።

ስላቅ በስድ ንባብ ወይም በግጥም፣ የሰውን ክፋትና ጭካኔ ለማጋለጥ ወሳኝ ቀልዶችን ይጠቀማል። ሚቸል (2003) ስላቅ ጎላ ያሉ ባህሪያትን በማንፀባረቅ ተቋሞች ወይም ግለሰቦች ሙሰኛ ናቸው ብሎ የሚገምታቸውን በአሽሙር ይሞግታል። በሌላ አገላለጽ፣ የስላቅ አንዱ ባህሪ የስነምግባር ማሻሻያ ጉዳይ ነው። ሚቸል እንዳሉት "የስላቅ ባህሪ መጥፎ ድርጊት እንዲያስቅ ወይም እንዲወቅስ ያደርጋል። በዚህም ባህሪው ስህተት በሚሰሩ ሰዎች ላይ ማህበራዊ ጫና ይፈጥራል በማለት ይገልጻል።

ስላቅ ማህበራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ትችት ሲያደርግ የሚጠቀማቸው የሚንጸባረቁ የስላቅ ባህርያት አሉ ። እነዚህን የስላቅ ባህርያት ጆህንስተን(1998) እንዲህ ሲል ይገልጻል "የስላቅ አንዱ ባህሪ

ተመልካቾችን ተቃውሞ እንዲያሰሙ ለማድረግ በትክክል ግልጽ ቋንቋ የመጠቀም ፍላጎት ነው:: በዚህ ምክንያት የተሳላቂው ቋንቋ ምጸት፣ ፓራዶክስ፣ ተቃርኖ፣ ቃላታዊነት፣ ጸያፍነት፣ ዓመጽ፣ ግልጽነት እና ግነት ይንጸባረቃሉ" በማለት ያብራራል፡፡ የጆሀንስተንን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ ፌይንበርግ የስላቅ ባህሪያት እንደሚከተለው ይገልጻል፡-

> የስላቅ አስፈላጊ ባህሪያቱ መዝናኛነቱ እና ትኩስነቱ ናቸው፡፡ የስላቅ በሥነ-ጽሑፋዊ ብቃቱ፣ ብሩህነቱ፣ ጥበቡ፣ ቀልዱ፣ እና ትኩስነቱ ነው:: ስለዚህ ስላቅ ጊዜ ያለፈባቸውን ነገሮችን በአዲስ መንገድ በማሳየት በእውነታው እና በማስመሰል መካከል ያለውን ንፅፅር በጥበብ መግለጽ ነው:: ስላቆቹ የሚነበቡት እንደ ሥነ ጥበብ ሥራዎች በውበት የሚያረኩ በመሆናቸው እንጂ በሥነ ምግባራዊ ጤናማ ወይም በሥነ ምግባር አስተማሪ ስለሆኑ ብቻ አይደለም:: ነገር ግን አነቃቂ እና መንፈስን የሚያስደስቱም ናቸው፡፡ (ፌይንበርግ ፣1967፡16)

ስላቅ አንድንየተረሳ የሚመስል ጉዳይ በአዲስ እያነሳ የሚሞግትም ዘዴ ሲሆን አንድ ጉዳይ እስኪስተካከል ድረስ ትችቱን የማያቆም ዘዴ ነው፡፡

**አምስቱ የስላቅ ባህርያት (መሰረታዊ ነገሮች)**

1. ***ማጥቃት*** (Aggression)፡-

ስላቅ ጥቃት ነው፣ ግን አብዛኛውን ጊዜ ቀጥተኛ ሳይሆን አስቂኝ ነው:: እንደ ፌዝ እና አሽሙር ያሉ ቀጥተኛ ጥቃቶች የስላቅ ባህሪ ናቸው::

2. **ውሳኔ**( Judgment)

አንድ ጊዜ ጸሃፊው አንድ ነገር ወይም አንድ ሰው የሚያናድድ ወይም የሚያስቅ ነው ብሎ ከወሰነ፣ ከዚያም ጸሃፊው ያ ሰው ወይም ነገር ከትክክለኛው ያነሰ እና ለፌዝ ብቁ ነው ብሎ ይወስናል:: በሌላ አገላለጽ፣ ጸሐፊው መጻፍ ሲጀምር የሚሳለቅበት ጉዳይ ላይ አስቀድሞ ይወስናል:: ውሳኔዎች ብዙውን ጊዜ በአንድ ርዕዮተ ዓለም ፣ በሥነምግባር እና ስብዕና ላይ የተመሰረቱ ይሆናሉ፡፡

3. **ፌዝ** (Wit)

ፌዝ ብዙ ጊዜ ስልታዊ ግን አስቂኝ በሆነ መንገድ በቃላት የመጫወት ችሎታ ነው። ጥቃትን እና ጨዋታን በማጣመር አያዎ የሚፈጥር ነው።

4. **ቧልት** (Humor)

ስላቅ ለውጥ ለማምጣት በጸሐፊው ፍላጎት ተገፋፍቶ እንደ ማስመሰል፣ ፌዝ ወይም ቧልት ሳቅ ላይፈጥር ይችላል። ነገርግን ምጸት፣ የቃላት ጨዋታ፣ ፓሮዲ እና ሌሎች የስላቅ ቴክኒኮች ሳቅን ሊፈጥሩ ይችላሉ። ነገር ግን አንዳንዴ የስላቅ ዋና አላማ ሳቅን ላይፈጥር ይችላል።

5. **አመለካከትንየመለወጥ ፍላጎት** (Desire to Instigate Reform (Intent))፦

ስላቅን ከአሽሙር የሚለየው ዓላማው ነው። የአሽሙር አስተያየቱ ቧልት እና ሳቅ የሚያጭር ሊሆን ቢችልም የተናጋሪው አላማ በህብረተሰቡ ዘንድ የተሳሳተ ነገርን ለመለወጥ ሊሆን ይችላል። ተሳላቂው ጉዳዩን በተዘዋዋሪ መንገድ ግን ተፅዕኖ በሚያሳድር መልኩ ለመፍታት ስላቅን ይጠቀማል። አንድ ስራ መሳለቂያ ይሆን ዘንድ መስተካከል የሚገባው ግብ ወይም ማሻሻያ መኖር አለበት።

## 2.1.5 የስላቅ ዘዴዎች

የስላቅ ዘዴዎች ስለ አንድ የተወሰነ ርዕሰ ጉዳይ ወይም ባህሪ አስተያየት ለመስጠት ወይም ለመተቸት ይጠቅማሉ። ስላቅ ከሌሎች ጽሑፎች የሚለየው በሚጠቀማቸው ዘዴዎች ነው። ስላቅ ሀሳቦችን በማጣመር ወይም በማነፃፀር ደስታን የመስጠት ኃይል አለው። ተሳላቂዎች መልእክቶቻቸውን ለማስተላለፍ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ።

አንዳንድ የስነጽሁፍ ስራዎች ራሳቸውን ለስላቅ ያጋልጣሉ። ስላቅ የራሱ የሆነ የማቅረቢያ ዘዴዎች ያሉት ሲሆን ጥቂቶቹ ማጋነን፣ ማዛባት፣ማሳነስ፣ንቀት፣ፓሮዮማሲያ፣ ዘዩግማ፣ አሻሚነት፣ ማስመሰል፣ዘይቤ፣ ኦክሲሞሮን፣ ምሳሌ ፣አሊጎሪ፣ልዩነት እና ውጫዊነት ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ (ሀሪስ፤1990 እና ፌንብርግ 1967) ሲገልጹ ሌሎች ምሁራን፣ እንደ Matthew Ho-gart, Gilbert Highet እና Northrop Frye, invective, caricature፣ burlesque እና absurdum ይጨምራሉ።

ስላቅን ለመጠቀም ቧልት፣ማጋነንን፣ ምጸት፣ አሽሙር፣ፓሮዲ፣ማዛባት፣ ማሳነስ፣ ማስመሰል፣ አሊጎሪ፣ ፓራዶክስ፣ ወለፈዲነት ወዘተ በመጠቀም ጠንካራ መሳለቂያን መጠቀም ይቻላል።

### 2.1.5.1 ማጋነን

በስላቅ ውስጥ በብዛት ጥቅም ላይ ከሚውሉ ዘዴዎች አንዱ ነው። ማጋነን እኩይ ተግባር መኖሩን ለማሳወቅ የምንጠቀምበት መንገድ ነው። ማጋነን እንደ ምፀት አስፈላጊ ባይሆንም በስላቅ ውስጥ በብዛት ጥቅም ላይ ከሚውሉት ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ነው። ተሳላቂው የሚያጋንነው መጥፎነትን፣ ክፋትን፣ ግብዝነትን ሲሆን የሚተወው ደግሞ ጥሩነትን፣ አስተዋይነትን እና ታማኝነትን ነው። ተሳላቂዎቹ የሚያስቃዩ ወይም የወለፈዲያዊ ሁኔታዎችን ወይም ተንኮለኛ ወይም ክፉ ሰዎችን በተቻለ መጠን ለመግለጽ ማጋነን ይጠቀማሉ። (ሀሪስ፤ 1990 እና ፌይንበርግ፤1967)

ስለዚህ ማጋነን አንዳንድ ባህሪያትን ከእውነታው በላይ በመግለጽ ወይም በማሳነስ ሁኔታውን ወይም ሰውን ከነሱ የተሻለ ወይም የከፉ እንዲመስል ማድረግን ያካትታል። ማጋነን በተለምዶ የአንድን ሰው ወይም የሁኔታውን ትክክለኛ ባህሪ ይመለከታል። የተለመዱ እና የሚዘወተሩ የማጋነን አይነቶች፦

1. ካሪካቸር፦

ካሪካቸር አካላዊ ባህሪያትን ማጋነን ነው። ለምሳሌ አንድን ሰው ረጅም ነው ብለው ከገለፁት ከዛፍ ወይም ከህንጻ ጋር ማወዳደርን የሚያመለክት ነው።

2. Burlesque

የሚያመለክተው በቋንቋ ውስጥ አስቂኝ የሆነ ማጋነን ነው። ብዙውን ጊዜ በቃላት እና በሁኔታዎች መካከል ያለውን ልዩነት የማይመጣጠኑ ያደርጋል። በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ያሉ ገፀ-ባሕርያት እንዲናገሩ ወይም በሚያስቅ ሁኔታ ተገቢ ባልሆኑ መንገዶች እንዲናገሩ በማድረግ በጣም ከባድ የሆነ ሁኔታን እንዲያደናቅፉ የሚደረግበት ነው። በሌላ አገላለጽ ቡርሌስክ በሁኔታው ወይም በገጸ ባህሪያቱ እና ድርጊቱን በሚናገሩበት ወይም በሚሰሩበት ዘይቤ መካከል ትልቅ ክፍተት ይፈጥራል።

3. ከመጠን በላይ መግለጽ እና ማቃለል

ይህ ዘዴ የአንድን ሰው፣ የቁስ ወይም የሃሳብ መጠን ወይም ጠቀሜታ ይጨምራሉ ወይም ይቀንሳሉ። ይህ ዘዴ አንድን ጉዳይ ከመጠን በላይ በማሳነስ ወይም ከመጠን በላይ በመጨመር የምናቀርብበት ዘዴ ነው።

## 2.1.5.2 ማዛባት

የስላቅ ዘዴ ከሆኑት ውስጥ ሁለተኛው ማዛባት ሲሆን ማዛባት እንደ ሀሪስ ገለጻ የአንድን ሁኔታ ወይም ክስተት እይታ በመነጠል ወይም አንዳንድ ገጽታዎችን በማጉላት እና ሌሎችን በማደብዘዝ የሚገለጽበት እንደሆነ ያስረዳል ። (ሀሪስ፤1990)

ማዛባት አንድን ነገር ከነበረው በተቃራኒ መንገድ መጠቀምን የሚያመለክት ሲሆን ለማዛባት ገጽታውን በማጉላት፣ በማግዘፍ እና በማኮሰስ ልንጠቀም እንችላለን። ማዛባት አንዳንድ ጊዜ የግነት ማቅረቢያ ስልት ሆኖም ሊያገለግል ይችላል።

## 2.1.5.3 አለመመጣጠን

አለመመጣጠን ሌላው የስላቅ ዘዴ ሲሆን ማጋነንን፣ ማቃለልን፣ ንፅፅርን፣ማወዳደርን፣ ማጣመምን፣ ተንኮለኛ ፊዞችን እና ፓራዶክስን የሚጠቀም የስላቅ ዘዴ ሲሆን፤ ብዙውን ጊዜ ወለፈንዲያዊ የስላቅ ዘዴ ሲሆን ያልተጠበቀ ነገር ወደ ሌላ የተለመደ ትዕይንት ወይም ታሪክ የሚቀርብበት ስልት ነው። የስላቅ ጸሃፊዎች ይህንን ዘዴ በብዛት የሚጠቀሙት በአንድ ትዕይንት ውስጥ ያሉ ገፀ-ባህሪያት ያልተለመዱ ድርጊቶች የተለመደ በሚመስሉ ሆኔታዎች ሲቀርቡ ሲሆን መግለጫ ጽሑፉ ወለፈንዲያዊ ስላቅን ያሳያል ሲል (https://www.indeed.com/career-advice/career-development/satire tecniques) የተባለ ድህረ ገጽ ይገልጻል።

ወለፈንዲነት አንዱ ያለመመጣጠን መገለጫ ሲሆን ስለ ወለፈንዲነት ካሙ እንዲህ ሲል ይገልጻል "የሰው ልጅ በህይወት ኡደት ውስጥ ለሚገጥሙት እያንዳንዱ የህይወት ውጣ ውረዶችም ሆነ ለራሷ ለህይወት ትርጓሜ ለመፈለግ በሚያደርገው ጥረት እና ዓለም በምትሰጠው የተዛባ፣ተስፋ አስቆራጭ እና ትርጉም አልባ ምላሽ መካከል የሚፈጠር ግጭት ነው" (ካሙ፤2000፣11) በማለት ሲገልጽ ኮርንዌል (2013) በበኩሉ ወለፈንዲ ብዙ ጊዜ ጸያፍ

ወይም የተከለከሉ ርዕሰ ጉዳዮችን ቀለል በማድረግ፣ ወይም ሆን ብሎ ለአንባቢ የበታችነትን ለማሳበቅ እና ወሲባዊ ጉዳዮችን ወይም የሞት ጭብጦች ለማንሳት ያለመ እንደሆነም ያስረዳል።

ወለፈንዲነት ለህይዎት ትርጓሜ ለመፈለግ ሲባል ያልተመጣጠነ አገላለጽን የምንጠቀምበት ሲሆን የወሲብ እና ሞት ጭብቶችን እንድናነሳ ያስገድደናል፡፡ ይህንን በስላቅ መንገድ ማቅረቡ ደግሞ ጉዳዩን እንዳይመጣጠን ያደርገዋል፡፡

## 2.1.5.4 ማጥቃት

ሌላው ተዘውታሪ የስላቅ ዘዴ ማጥቃት ነው፡፡ ማጥቃት በጣም ተሳዳቢ፣ አብዛኛው ጊዜ የተለየ ዒላማ ላይ ያነጣጠረ ቋንቋን ይገልጻል ለምሳሌ፣ እርግማን። ማጥቃት ብዙውን ጊዜ በጣም አስቂኝ ሊሆን ይችላል ነገር ግን የስላቅ ዘዴው በጣም ትንሹ ፈጠራ ነው፡፡ ኢንቬክቲቭ ሰውን ወይም ነገርን የሚያጠቃበት ወይም የሚሳደብበት ቋንቋ እና ቃና የሚጠቀምበት የስነፅሁፍ መሳሪያ ነው። ማጥቃት ብዙውን ጊዜ ከአሉታዊ ስሜቶች ጋር አብሮ የሚመጣ ሲሆን ማጥቃት በሁለት ዓይነቶች ሊከፈል ይችላል፡፡ ይኸውም ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ማጥቃት ይባላሉ፡ ፡ ከፍተኛ ማጥቃት መደበኛ እና የፈጠራ ቋንቋ መጠቀምን ሲጠይቅ፤ ዝቅተኛ ማጥቃት ደግሞ ባለጌ እና አጸያፊ ምስሎችን ይጠቀማል፡፡

## 2.1.5.5 ምጸት

ምጸት ማለት የቃሉ ፍቺ ፊት ለፊት ከምናየው ተቃራኒ የሆነበት ድርብ ትርጉም የያዘ ነው። ስላቅ ሁልጊዜ ምጸትን ይጠቀማል። በስላቅ መልክ ምጸት መጠቀሙ ለአንድ ጉዳይ ወይም ነገር አጽንኦት እንዲሰጥ ያደርገዋል፡፡ ምፀት በቃላት ወይም በክስተቶች ከሚጠበቀው የተለየ እና ተቃራኒ የሆነውን እውነታ የሚያስተላልፍ የአገላለጽ ዘዴ ነው። የተመልካቾች አስገራሚ እውቅና ብዙውን ጊዜ አስቂኝ ውጤት ያስገኛል፡፡ ይህም ምጸቱን አስቂኝ ያደርገዋል።ሀሪስ "ምፀት ግብዞችን የማጥቂያ ዘዴ ነው" (ሀሪስ፤ 1990) ሲል ጆሀንስተን በበኩሉ "አስቂኝ ጨዋታ ውስጥ ሁለት ተቃራኒ ትርጉሞችን እንደሚያመጣ ይገልጻል፡፡ ትክክለኛው ትርጉሙ የላይኛውን ትርጉም የሚጻረር ሆኖ ሲገኝ ምጸት ይሆናል። ነገር ግን ምጸታዊነት በስላቅ ብቻ የተገደበ እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል" (ጆሀንስተን፤ 1998)፡፡ በማለት ያስረዳል፡፡

ምጸት አንድ ቃል ወይም ክስተት ከትክክለኛው ትርጉሙ የተለየ እና ብዙ ጊዜ የሚቃረን ነገር የሚቀርብበት ሥነ-ጽሑፋዊ መሣሪያ ነው:: ምፀቱ በእውነታው እና በአንድ ነገር ገጽታ ወይም

በሚጠበቀው መካከል ያለው ልዩነት ነው:: ይህም በታሪክ አውድ ውስጥ ሲቀርብ በተፈጥሮ ላይ ውጥረትን ይፈጥራል። ይህ ባህሪውም በስላቅ ውስጥ ወሳኝ መሳሪያ በመሆን እንዲያገለግል ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም ሰዎች ስለ አንድ ሁኔታ በሚናገሩበት ወቅት በሁኔታው እና በእውነታው መካከል ያለውን ርቀት አጉልቶ ያሳያል፡፡ ምጸት በሥነ ጽሑፍ ውስጥ በዋናነት በሦስት ዓይነቶች ይገኛል ይኸውም የቃል ምጸት፣ ድራማዊ ምጸት እና ሁኔታዊ ምጸት ናቸው።

## 2.1.5.6 ፓሮዲ

ፓሮዲ አንዱ የስላቅ ስልት ሲሆን የአንድን ሰው ስራ፣ ቴክኒክ ወይም ዘይቤን በመኮረጅ በዋናው ላይ የማሾፍ ዘዴ ነው፡፡ ፓሮዲ የተሳካ እንዲሆን አንባቢ ጸሀፊው እየተሳለቀበት ያለውን ዋናውን ጽሑፍ ማወቅ አለበት፡፡ አለበለዚያ ግን ፓሮዲ መሆኑን መረዳት ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ ፓሮዲ የአንድን ሰው ስራ ወይም ሁኔታ ለመሳለቂያት የማቅረቢያ ዘዴ ነው፡፡

## 2.1.5.7 ተገላቢጦሽ

ሌላው የስላቅ ማቅረቢያ ዘዴ ተገላቢጦሽ ሲሆን፤ ተገላቢጦሽ አንድ ደራሲ ሁኔታውን በመገልበጥ ነገሮች ወደ አንባቢ እንዴት እንደሚመለሱ የተገላቢጦሽ አቀራረብን ይጠቀማል። ብዙውን ጊዜ ስለ ጉዳዩ አስቂኝ አስተያየት ለመስጠት ከመደበኛነት ተቃራኒውን የሚያቀርብ ታሪክን ያካትታል [https://www.i ndeed.com/career-advice/career-development/satire-techniques]በማለት ያስረዳል።

የስላቅ ዘዴዎች ከላይ የተብራሩት ብቻ ሳይሆኑ ብዙ ናቸው። ለምሳሌ፡- ሀሪስ፣ ፌይንበርግ እና ማቻል የጠቀስኳቸውን ብናይ ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም ስንጠቀማቸው የትርጉም ለውጥ የሚያመጡ ነገር ግን ለስላቅ ማቅረቢያ ዋና ዘዴዎች መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ የስላቅ ዘዴዎች፣ የስላቅ መሰረታዊ ነገሮች እና ባህርያት እንብዛም የማይለያዩ ነገርግን በስላቅ ውስጥ ስናገኛቸው ስላቁን የሚያጎሉ የአጠቃቀም ስልቶች ናቸው።

## 2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ይህን ጥናት ለማካሄድና በምርምሩ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ በቅርብም ይሁን በሩቅ ዝምድና ያላቸዉ ጥናቶች ፍተሻ ተደርጎባቸዋል፡፡ በፍተሻ ሂደቱም  በጌታቸው ታረቀኝ የተውኔት ስራዎች ላይ የተካሄደ ጥናት ለአጥኝዋ አላጋጠማትም፡፡ ስላቅን ማንጸሪያ በማድረግ በአማርኛ ቋንቋ የተጠና ጥናትም አላጋጠማትም፡፡ ነገርግን አጥኝዋ በውጭ ቋንቋ የተጠኑ ጥናቶች ከሀገር ውስጥ አንድ የሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ፣ ከውጭ ሀገር   አንድ ጥናት  ለመዳሰስ ችላለች፡፡

የመጀመሪያው የስንታየሁ (2000 ዓ.ም) “Political and soclal satire as reflected in Bewketu Seyum’s Enqilf ena Edmie and Berari Kiteloch” በሚል ርዕስ ለአዲስ አበባ ዩቨርሲቲ የውጭ ቋንቋዎች ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋነኛ ትኩረትም በተመረጡ የበውቀቱ ስዩም ስራዎች ውስጥ  ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ስላቅን መተንተን ነበር፡፡ በተጨማሪም የስላቅ ባህርያት፣ የስላቅ ዘዴዎች ፣ የኮሚዲ እና የስላቅ ተፈጥሮ በስፋት ተተንትኖበታል፡፡ በተለይ ከስላቅ ዘዴዎች ውስጥ ማጋነን፣ አሽሙርና አግቦ ተለይተው ተብራርተዋል፡፡ ይህ ጥናት ከመፈከሪያ  አንጻር ስላቅን  እና ከስላቅ ዘዴ እና ባህርያት መጠቀሙ ለትንተና የቀረበው ቴክስት የተጻፈበት ቋንቋ አማርኛ መሆኑ በእጅጉ ከአጥኝዋ ጥናት ጋር የሚቀራረብ ቢሆንም ልዩነቱም የዝያን ያህል ነው፡፡ የመጀመሪያው ልዩነት የስንታየሁ ጥናት የልቦለድ ስራዎች ላይ ሲያተኩር የአጥኝዋ ጥናት ተውኔት ላይ መሆኑ፤ ሁለተኛው የአጥኝዋ ጥናት ትኩረቱ በዋናነት  የትኛው የማህበረሰብ ክፍል ላይ ስላቅ እንደቀረበ፣ የትኛዉን የስላቅ ዘዴ በስፋት እንደታየ፣ የቀረበው የስላቅ ይዘት ምን እንደሚመስል  በስፋት የሚተነተንበት ስለሆነ ልዩነት አለው፡፡

ሁለተኛው ጥናት በ Lauren Combs (2016) “The Power of Politcal satire: dose it nfluence viewers to participate in politics?” በሚል ርእስ በኦክላሆማ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ሲሆን የዚህ ጥናት አብይ ዓላማዉ ለፖለቲካዊ ስላቅ መጋለጥ ለተመልካች ያለውን ጠቀሜታ መተንተን ሲሆን በጥናቱም የቴሌቭዥን ተመልካች ዳታ በመሰብሰብ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡ መረጃ ለማግኘትም የፖለቲካ ተሳትፎን የሚያሳይ የመራጮች ዳታ ከቴሌብዥን፣ ከኦላይን ላይ መረጃ ተወስዶ ተተንትኗል፡፡ በተጨማሪም በቃለ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቦ ተተንትኗል፡፡ ይህ ጥናት ከአጥኝዋ ትልመ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው መፈከሪያው ስላቅ መሆኑ ሲሆን ልዩነታችን የዚህ ጥናት የመረጃ መተንተኛ

እና መሰብሰቢያ ዘዴው ከአጥኝዋ ጥናት ጋር ፈጽሞ የተለየ ነው፡፡ የአጥኝዋ ጥናት ትኩረቱ ቴክስት ትንተና ላይ ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት ፖለቲካዊ ስላቆች የሚመለከቱ ሰዎች ያገኙትን ጥቅም መረጃ ከቴሌቭዥን እና ከኦላይን በመሰብሰብ አሀዛዊ ትንተና መስጠት ነው፡፡ ስለዚህ የጥናቱ ትኩረት ተመልካች ላይ ነው፡፡ ስለዚህ Combs ጥናት ከአጥኝዋ ጋር በአጠናን ዘዴ እና በመረጃ መተንተኛ ዘዴው እንዲሁም ከጥናቱ አላማ አንጻር ልዩነት አለው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የስላቅ ትንተና በተመረጡ ተውኔቶች ውስጥ

በቀደሙት ሁለት ምዕራፎች ተደጋግሞ እንደተነሳው የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ በተመረጡ የጌታቸው ታረቀኝ የተውኔት ስራዎች ዉስጥ ስላቅ በምን መልኩ እንደተከሰተ መተንተን ነው። በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ የተመረጡትን ተዉኔቶች ከስላቅ መገለጫ ባህሪያት አንፃር የመጀመሪያው **የሳጥናኤል** አበሳ(2007 ዓ.ም) ቀጥሎ **ቤጊዮሎጂ**(2013ዓ.ም) በመቀጠል **ሽልማቱ**(1983ዓ.ም) የተሰኙት ተውኔቶች በቅደም ተከተል አጥኚዋ ተንትናለች። በተጨማሪም ከላይ በጥናቱ አደረጃጀት ስር እንደተገለፀዉ የተዉኔቶቹ አፅመ-ታሪኮች የትንተናዉን አደረጃጀት ለመጠበቅ በማሰብ በአባሪነት ተያይዘዋል።(አጽንኦት የኔ)

### 3.1 የስላቅ ዘዴዎች

ከጌታቸው ታረቀኝ የተውኔት ድርሰቶች መካከል፣ ***የሳጥናኤል አበሳ(2007) ፣ቢጊዮሎጂ(2013) እና ሽልማቱ(1983)*** ከድርሰቶቹ ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው። ***የሳጥናኤል አበሳ*** ባለ 4 ገቢር ሲሆን በውስጡም ያሉ ገፀ-ባህርያት ሳጥናኤል ፣ ዲሚትሪ፣ አበራ፣የሚቹ እናት ፣ሚቹ ፣ ነፍስ አባት ፣የሳጥናኤሌ እናት፣ጋሽ እርዚቁ ፣ዳንሰኞች/ለቀስተኞች፣ሰውየው ናቸው። ***ቢጊዮሎጅ (የልመና ጥበብ)*** ባለ 5 ገቢር ሲሆን በውስጡም ያሉት ገፀ-ባህርያት ክቡር ተሰማ መቅደሱ ፣መምህር አልአዛር፣ ሮዚና፣ ፓንድ፣ ሚስተር ቦብ ጃክሰን፣ምስክር፣ አስናቀች፣ ጥጋቤ ፣ አበራ፣ ቤቲ፣ ተማሪዎቹ ናቸው። ***ሽልማቱ*** ባለ 1 ገቢር ተውኔት ሲሆን በውስጡም ያሉት ገፀ-ባህሪያት የኮሚቴዉ ሰብሳቢ (ዘርጋባቸዉ) ፣አባል ቁጥር 1፡ ( ኃ/ ማርያም)፣አባል ቁጥር 2፡ (ሰማኸኝ) እና አባል ቁጥር 3 (አስመላሽ) ናቸው። በእነዚህ የተውኔቱ ገቢሮች ውስጥ የተከሰቱ ዋና ዋና የስላቅ ዘዴዎች ተተንትነዋል።(አጽንኦት የኔ)

#### 3.1.1 *ማጋነን*

በስላቅ ውስጥ በብዛት ጥቅም ላይ ከሚውሉ ቴክኒኮች አንዱ ማጋነን ወይም ግነት ነው። ስለማጋነን የምሁራንን ሀሳብ መነሻ በማድረግ በክፍል ሁለት በስፋት ተብራርቷል። በሳጥናኤል አበሳ ተውኔት ውስጥ ካሪካቸር ( Caricature) ተከስቶ እናገኛለን። ካሪካቸር አካላዊ ባህሪያትን የማጋነን ተግባር ነው ። ሳጥናኤል በሲኦል ውስጥ ሬሳውን ሲያስጎበኝ በሲኦል ያሉት ሰዎች

ማንነት እና ወደ ሲኦል እንዴት እንደገቡ ፣አሟሟታቸው ምን እንደ ነበር ሲያስተዋውቅ እናያለን፡፡ መብራቱ የተሰኘው ገጸባህሪ አሟሟት ሲያብራራ አሟሟቱ ብልት ለማሳደግ ያላአግባብ በተወሰደ የባህል መድሃኒት ሰበብ ብልታቸው ከመጠን በላይ አድጎ ጠልፎ እንደገደላቸው ተገልጾ እናገኛለን፡፡ ለማሳያም ከተውኔቱ የተወሰደ ቅንጫቢ ማየት እንችላለን ፡፡

ሳጥናኤል፡-ይሄዋ ቀስ እያለ ይመጣልሃል…ብቻ የሚያሳዝነዉ ልበልህ…እሳቸዉም ወትሮም የአበሻ መድሐኒት ብለዉ ንቀዉ ትተዉት ነበርኮ…ግን አንድ ቀን አልጋቸዉ ላይ ተኝተዉ ድንገት መፋቅ ጀመሩና..ሳያስቡት መፋቂያዉን አፋቸዉ ዉስጥ አድርገዉ በዚያዉ እንቅልፍ ይወስዳቸዋል…ታዱያ ያ መፋቂያዉ ድንገት ስራዉን ይጀምርልሃል…እንትናቸዉም ሲያድግሲያድግ…ሲያድግ ከአልጋ ወርዶ መሬት ላይ ደረሰ…

ሬሳ፡- እያደገ?..

ሳጥናኤል፡- ታዲያስ…መፋቂያዉን ማን ከአፋቸዉ ያዉጣዉ…ከዛ እንትናቸዉ ሲያድግ ሲያድግ አድሮ ማለዳ ላይ ለሽንት ድንገት ተነስተዉ ወደ ሽንት ቤት ሲሄዱ የራሳቸዉ ብልት …ያ የተናቀዉ ጠልፎ ጣላቸዉና ከወደቁበት ሳይነሱ በዚያዉ አረፉ…እዚህ ያሉት ሰዎች …‹መብራቱ፡ ጠላቱ ብልቱ›..እያሉ ነዉ" (አጽንኦት የኔ)

(ጌታቸው ታረቀኝ፣2007፣15)

የብልት እድገት ጠልፎ እስኪጥል ድረስ ማደጉ አካላዊ ግነት የተንጸባረቀበት ሲሆን ሌላው ያለአግባብ በመመገቡ ሆዱ ብልቱን እንደሸፈነው እና ለግብረ ስጋ ግንኙነት መቸገሩን በግነት ቀርቦ እናገኛለን፡፡ ሀሪስ(1990) ስለግነት እንዲህ ሲል ይገልጻል "ተሳላቂው ለስህተቶች የተሰጡትን መግለጫ ወደ አመክንዮአዊ ጽንፍ ያመጡታል፣ ወይም ቢያንስ ከመጠን በላይ በማጉላት የማይታየውን እንዲታይ እና ብልሹ አሰራርን በመቃወም ችግሩ እንዲወገድ ያደርጋሉ"፡፡ ስለዚህ በዚህ ተውኔትም ተገልጾ የምናየው ያለአግባብ መመገብ በጤና ላይ የሚያደርሰው ጉዳት እንዳለ ሁሉ የማህበራዊ ጉዳት እና ለስነልቦናዊ ቀውስ ሊያጋልጥ

እንደሚችል ከመብራቱ የሆድ ማደግ፣ የሚስቱ መናቅ እና ብልት ለማሳደግ የሚወሰድ የባህል መድሃኒት መረዳት ይቻላል፡፡ የባለቤታቸው ንቀት የሚነሳው ከወስብ ፍላጎት አለመመጣጠን ጋር የተነሳ ሲሆን ይህም በቤተሰብ ውስጥ ማህበራዊ ችግር እንደሚፈጥር እና እስከ ትዳር መፍረስ ሊያደርስ እንደሚችል በስላቅ ሲገለጽ እናያለን፡፡ በትዳር ውስጥ የሚፈጠረውን ማህበራዊ እና ስነልቦናዊ ጉዳት ሲገልጽ አካላዊ ግነትን በመጠቀም ነው፡፡ ሌላው የምንረዳው ነገር የባህል መድሃኒት በሀገራችን በስፋት የምንጠቀምበት ቢሆንም እንኳ ያለ አግባብ ስንጠቀም የሚያደርሰውን ጉዳት ለማሳየት የሞከረ ነው፡፡

በዚሁ ተውኔት ውስጥ የሞተ ሰው የህይወት ታሪክ ሲቀርብ እና ሲለቀስ በግነት ዘዴ ሲገለጽ እናገኛለን ፡፡ለቀስተኞቹ የተለመደውን የኢትዮጲያዊ አለቃቀስ ይዘው ሳይሆን የሚያለቅሱት በዳንስ እና በዳንኪራ የህዝብ ዜማዎችን በማስገባት ሲሆን የህይወት ታሪኩም የሚነበበው ያደርግ የነበረው እኩይ ባህሪው ተመርጦ ሲቀርብ እናስተውላለን፡፡ ሚች በባህሪው የተለየ፣ ክፋት፣ምቀኝነት፣ስግብግብነት፣ቅናትና ጥላቻ የተሰኙ ረቂቅ ባህርያት የሚገለጹበት ሰው ነው፡፡ ሚች ሰው ነው ለማለት የሚያስቸግር ስነ ባህሪ እንዳለው የሞተ እለት በሚነበብለት የህይዎት ታሪኩ ውስጥ ሲገለጽ እናገኛለን፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆን ከተውኔቱ ማየት እንችላለን፡፡

> ይበቃል እባካችሁ…ሀዘን ለቅሶ ቢበዛ የሞተን አይመልሰዉም… እባካችሁ ይበቃል..ሀዘንን ማብዛት ተገቢ አይደለም…በሱ በፈጣሪ ስራ መግባት ነዉ….መቼም የጊዜ ጉዳይ እንጂ ሁላችንም ከመሄድ አንቀርም…(ዳንሱ ያበቃል…አበራ ከኪሱ ወረቀት ያወጣል)….እድሜዉ ለትምህርት ሲደርስ ትምህርት ቤት ገብቶ ቢማርም ከተራ መሀይም የባሰ ጠማማ አስተሳሰብ የነበረዉ እጅግ ጠማማ ሰዉ ነበር…ገና በልጅነቱም የሌሎች ህፃናትን ልብስና መጽሐፍ መቅደድ፤ የሚማሩበትን መደበቅ የሚወድ ተንኮለኛ የነበረ ሲሆን በርግጥም የሰዎችን መልካም ስራ ለማራከስና ለማንቋሸሽ ተግቶ የሚሰራ እጅግ ምቀኛ የነበረ ሰዉም ነበር፡፡ …ሰዎች ሲወደሱ በስራቸዉ ሲመሰገኑ የሚከፋዉ …(ለቅሶ ሞቅ ይላል)…የሰዉ ማጣትና መቸገር የሚያስደስተዉ ..‹‹እገሌ አገኘ›› ከሚሉት ይልቅ ‹‹እገሌ አጣ ተዋረደ›› የሚለዉ የሚያዝናናዉ…በአስተሳሰቡ ብቻ ሳይሆን በአበላሉና አጠጣጡም እጅግ የተለየ ስግብግብ ሰዉ ነበር…
>
> (ጌታቸው ታረቀኝ፣2007፣4)

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ የምናየው አበራ የተሰኘው የህይዎት ታሪክ አንባቢ የሚችን እኩይ ተግባር እየመረጠ ሳቅን በሚያጭር የማጋነን ዘዴን በሞተው ሰው ላይ ሲሳለቅ እናያለን፡፡ የሰው ልጅ ክፉም ይሁን ጥሩ በሚሞትበት ወቅት የሚጻፍለት የህይዎት ታሪክ ጥሩ ነገር የሰራው ካለ ያንን ስራ በማጉላት ለህዝብ የሚጠቅም እንደነበረ ሰውን ሊያሳዝን እና ሊያስለቅስ በሚችል መንገድ ሲነበብ ክፉ የሚባል ሰውም ሲሞት የህይዎት ታሪኩ ከጥሩ ሰው ባልተናነሰ ለህዝብ የሚጠቅም ፣ደግ እና ጥሩሰው አጣን ተብሎ ያልሰራው ጥሩ ስራ እንደሰራ ተደርጎ ሲቀርብ እናያለን፡፡ በዚህ ተውኔት ውስጥ ግን ሚች የሰራው ስራ ሚቹ ሰው መሆኑን እስክንጠራጠር ድረስ ቃላዊ ግነት ተደርጎበት ሲቀርብ እናስተውላለን፡፡ የግለሰቡን በአለም ላይ ሲኖር የተጠላ፤ ልቅሶ የማያስፈልገው መሆኑን ለመግለጽ ግነት የተንጸባረቀበት ሲሆን ስላቁ ለህዝብ የማይጠቅሙ ሰዎች ሲሞቱ ህዝቡ መጨነቅ ያለበት በሀዘን ሳይሆን በደስታ ሞቱን መቀበል እንዳለበት የሚያሳይ ነው፡፡ በተለይም ለቀስተኞቹ በማልቀስ ፈንታ የለቅሶው እለት እየደነሱ እንደነበር የህይዎት ታሪኩ ሊነበብ ሲል ዳንስ ማቆማቸው ሲገለጽ እናያለን፡፡ በተጨማሪም ለቀስተኞቹ ዳንስ ላይ የነበሩ መሆናቸውን ከለቀስተኞቹ የለቅሶ ዜማ እና ለቅሶው ምን እንደሚመስል በማስረጃ ማየት ይቻላል፡፡

(…በሁለት አቅጣጫ ለቀሰተኞች ሞቅ ባለ ዳንኪራ/ዝማሬ ይገባሉ…የለቅሶ ዜማ ሳይሆን የዘፈን መሆን አለበት)

ለቀስተኞች፡- ዋይ ዋይ…ደበረህ ወይ

ዋይ ዋይ…ተከፋህ ወይ

ዋይ ዋይ…ከሄዴክማ ከተከፋህ

መንገዱን ጨርቅ ያርግልህ

ስትወጣ በሩ እንዳይመታህ

(ከዋና ለቀስተኞቹ ጋር ከሁዋላ የሚያሽበሽቡ ዘመድ ወዳጆች ይታያሉ…ዘፈኑ ጋብ ሲል የስልክ ጥሪ ይሰማል…)

(ጌታቸው ታረቀኝ ፣2007፣2)

ከለቀስተኞቹ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ለቅሶው ከተለመደው የአለቃቀስ ስርአት ውጭ ሳቅን በሚያጭር መንገድ በዳንስ እና በዳንኪራ ሟችን የጠየቁ በማስመሰል ሲሳለቁ ይስተዋላል፡፡ ሳቅን የሚያጭረው "ደበረህ ወይ.ተከፋህ ወይ…" የሚለው የቃላት አጠቃቀም አልቃሾች በሟች ላይ እያሾፉ መሆናቸው እና በግለሰቡ ሞት መደሰታቸው የሚገልጹ ናቸው፡፡ "ከሄዴክማ ከተከፋህ መንገዱን ጨርቅ ያርግልህ…" የሚለው ሟች በዓለም ላይ ሲኖር ምንም ያልጎደለበት ነገርግን የሰውን አኖኗር የሚያጎድል እንደነበር የሚገልጽ ነው፡፡ ስላቁ የቀረበበት ዘዴ በቋንቋ የማጋነን ስልት በመጠቀም ተንጸባርቆ እናገኛለን ፡፡ ለቅሶው በዳንስ እና በጭፈራ የቀረበበት ምክንያት ለህዝብ የማይጠቅሙ፤ በህዝብ የተጠሉ እና እኩይ ተግባር የሚፈጽሙ ግለሰቦች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ እና ህዝብ የሰለቸ እለት አቀባበራቸው ከስርዓት ውጭ ሊሆን እንደሚችል የሚያሳይ ነው፡፡

ሌላው ተንጸባርቆ የምናገኘው የግነት ዘዴ ሳጥናኤል ሟችን ሲያስጎበኝ ስለሙታን ገለጻ ሲያደርግ ከምናገኘው አንድ የሙታን ታሪክ ላይ ነው፡፡ ሟች በአለም እያለ የቬንዜውላ ፕሬዘዳት የነበረ ቢሆንም ሳጥናኤልን በማያውቀው ቦታ ከማያውቀው ሰው ጋር በማመሳሰሉ ሲኦል መግባቱን ይነግረዋል፡፡

> እሳቸዉም ትልቅ ስህተት ስለ ሰሩ ሁሌጊዜም አዲስ ከመጣዉ ጋር እየተቀመጡ እኔን በደምብ እንዲመለከቱ የተፈረደባቸዉ ናቸዉ፡፡ ለምን መሰለህ?..የተባበሩት መንግስታት የሚባለዉ የስብሰባ ቦታ ላይ ንግግር ሲያሰሙ…ጆርጅ ቡሽ የሚባዉን ሰዉዬ ‹ሰይጣን› ነዉ ብለዉ... ባልዋልኩበት ቦታ ከማላዉቀዉ ሰዉ ጋር እኔን ስላመሳሰለኝ…ሌላ ጊዜ እድሉን ካገኙት እኔን በደምብ እንዲለዩኝ እና የተባበሩት መንግስታት ከሚባለዉም የስብሰባ ቦታ እኔ ራሴ መሄድ እንደምፈራ እንዲያዉቁት ተብሎ ነዉ እዚህ እንዲውል የተፈረደባቸዉ፡፡ እንደምታያቸዉ መሳቅ እንኳ አይችለም፡፡( አጽንኦት የኔ)

(ጌታቸው ታረቀኝ፣17፣2007)

ከዚህ መረዳት የሚቻለው የተንጸባረቀው ግነትም በተባበሩት መንግስታት የሚፈጸመውን እኩይ አስተሳሰብ እና ሴራ ለመግለጽ ሳጥናኤል እንኳ የተባበሩት መንግስታት ድርጁት ስብሰባን እንደሚፈራው መገለጹ ነው፡፡ ሳጥናኤል በእኩይ ተግባሩ እና በክህደቱ ከገነት እንደተባረረ ቅዱሳን መጸሀፍት ሲያስረዱ እናገኛለን፡፡ ነገር ግን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሴራ ከሳጥናኤል ክፋት የላቀ እንደሆነ የግነት ዘዴን በመጠቀም በስላቅ መልኩ ቀርቧል፡፡ የተባበሩ መንግስታት ድርጀት በአለም ሀገራት ላይ በተለይ በታዳጊ ሀገሮች ላይ የሚፈጥሩት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጫና ለራሳቸው ጥቅም ብቻ በማሰብ ያላደጉ ሀገራትን የረዱ በማስመሰል ነው፡፡ የመንግስት አካላት በህዝቡላይ የሚያደርሱት በደል እና ስቃይ ከመጠን ያለፈ ስለሆነ ይህ መስተካከል እንዳለበት ለመጠቆም ሲባል በስላቅ መንገድ ተገልጾ እናገኛለን፡፡

***ቤጊዮሎጂ*** ተውኔት ውስጥ ግነት ተንጸባርቆ እናገኛለን፡፡ ቢጊዮሎጂ ተውኔት የልመና ስልትን እየቀያየሩ ሳይሰሩ መበልጸግ እና ሳይሰሩ መኖር የተገለጸበት ተውኔት ሲሆን የተውኔቱ ገጸባህርያት ምሁራን፣የልመና መምህራን እና ተማሪዎች የሚሳተፉበት ነው፡፡ በዚህ ተውኔት ውስጥ ለልመና የተሰማሩት አካላት አካል ጉዳተኛ ሳይሆኑ አካል ጉዳተኛ መስለው፣ ችግር ሳያጋጥማቸው ችግር እንዳጋጠማቸው ተደርጎ አሳዛኝ ታሪክ ተፍጥሮላቸው እና ሳይታመሙ አሳዛኝ ህመም ተፈጥሮላቸው ወደ ልመና ገብተው የምናገኝበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህ ድርጊታቸውም ሲገለጽ ግነት ይታይበታል፡፡ ለዚህ ማስረጃ ይሆን ዘንድ ሚከተለውን መመልከት ይቻላል፡፡

ተሰማ፡- (...ሁለት እጃቸውን ወደፊት ዘርግተው ፀሎት ያሰማሉ)...ሀይ ሀይ ...ሁይ ሁይ

ሊቃዉንቱ፡- (ተነስተው አይናቸውን ጨፍነው እጆቻቸውን ወደ ተመልካች ይረዘረጋሉ)...ሀይ ሀይ ...ሁይ ሁይ

ተሰማ፡- አምጣ አምጪ አምጣ

ሊቃዉንቱ፡- ስጠኝ ስጪኝ መርቁልኝ!

ተሰማ፡- ...ሥራ ያደክማል!

ሊቃዉንቱ፡ ...በጣም ያደክማል!!

ተሰማ፡- መስራት ያናድዳል!!

ሊቃዉንቱ፡- ስራ ማለት፤ ራስ ምታት!!

ተሰማ፡- ስራ የሞኝ ቅዠት!!

ሊቃዉንቱ፡- አደናግሮ አጭበርብሮ መኖር ሲቻል!!

ተሰማ፡- ሰዉ እንዴት ስራ ይሰራል!፤

ሊቃዉንቱ፡- ኧረ በጣም ያማርራል!

ተሰማ፡- ሰርቶ መብላት ማለት፤ የፋራ ቅዠት...

ሊቃዉንቱ፡- የጅል ሩጫ፤ የንፋስ ጩኸት

ተሰማ፡- ላይጠቅመዉ ላያልፍለት

ሊቃዉንቱ፡- ቤጊዮሎጂ ሳይንሳችን፤ አለማቀፍ ነዉ ትግላችን!!

(ጌታቸው ታረቀኝ፣2013፣2)

ተሰማ የተባለው ገጸባህሪ የማዕከሉ ዋና ስራ አስኪያጅ ሲሆን በኢንጅነሪግ የዶክተሬት እና ፕሮፌሰርነት ማእረግ ያለው ምሁር ነው፡፡ ነገር ግን ለተሰብሳቢ አካላት ንግግር ሲጀምር የሚጀምረው በጸሎት ስልት እጁን ዘርግቶ ሲሆን ፀሎቱም ልመና እንዲስፋፋ፣ስንፍና እንዲፋፋ ፣ሰርቶ መለወጥ የሚባል አስተሳሰብ እንዲጠፋ እና የሰው ልጅ ወደ ልመና እንዲሰማራ የሚያበረታታ ነው፡፡ የተሰማ ንግግር ግነት የሚስተዋልበት የስላቅ ዘዴ ነው፡፡ ሊቃውንቱም ሲቀበሉ ተሰማ የሚለውን ነገር በማጋነን የስራ አሰልችነትን እና የልመናን ምቹነት ሲገልጹ እናያለን፡፡ የልመና ስልቱም በሀገር ውስጥ ብቻ የታጠረ ሳይሆን አለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ እንዲኖረው ታቅዶ የሚሰራ የልመና ስልት ሲሆን የቀረበበት መንገድ ግነታዊ ስላቅ ይስተዋልበታል፡፡ ይህ ልመና በተለይ ተማሩ በተባሉ ሰዎች ላይ ጎልቶ የሚታይ መሆኑ እና በእርዳታ ስበብ የሚደረገው ልመና ሰውን ወደ መጥፎ ልምድ እየወሰደው መሆኑን ለማስገንዘብ የተገለጸበት የስላቅ ስልት ነው፡፡ ለስላቅ የቀረቡትም ምሁራን እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች እንደሆኑ እናያለን፡፡

ውድ ተማሪዎች እናንተም ከዚህ ማዕከል ሠላሳ ስድስት ወራት በቲዮሪና በፕራክቲስ ሰልጥናችሁ ስትመረቁ፤ **ሳይንሱ በደም ቧንቧችሁ ስለሚዘዋወር ይሄ‹‹ስርቶ መብላት፤ ሀቅና እውነት›› የሚሉትን ፈተና ትገላገሉታላችሁ፡፡** እናም በሌሎች ድካሞች ላይ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ጥገኛ መሆኑ እጅግ አትራፊ ተግባር መሆኑንም በተጨባጭ ትደርሱበታላችሁ!... በሁለት እና በሦስት አመት ጊዜ ውስጥም ለልጅ ልጅ የሚተርፍ ሃብት ባጭር ጊዜ ታካብታላችሁ፡፡ የቤት እቃና መኪናም ብቻ አይደለም፤የሚያጫውታችሁ ውሻ ሳይቀር ከፈረንጅ አገር ታስመጣላችሁ፡፡አጽንኦት የኔ

(ጌታቸው ታረቀኝ፣2013፣6)

ልመና ዘመናዊ በሆነ መንገድ እየተስፋፋ መምጣቱ እና የሚሰራ የሰው ልጅ ጉልበት ያለ አግባብ መባከኑን እና ይህንንም አጸያፊ ተግባር እየተሰራ ያለው ልሂቃን በሚባሉ ሰዎች እንደሆነ ለመግለጽ የተንጸባረቀው ስላቅ በግነት ዘዴ መሆኑን ማየት እንችላለን፡፡ ሀሪስ (1990) እንደሚለው ለስህተቶች የተሰጡትን መግለጫ ወደ አመክንዮአዊ ጽንፍ ለማምጣት ወይም ከመጠን በላይ በማጉላት የማይታየውን እንዲታይ እና ብልሹ አሰራርን በመቃወም ችግሩ እንዲወገድ ለማድረግ የግነት ዘዴን እንደምንጠቀም ይገልጻል፡፡ በዚህ ተውኔት ውስጥም የምናየው የሰው ልጅን የመስራት አቅም እያዳከመ የመጣውን ሳይሰሩ የመበልጸግ ፍላጎት በደንብ እንድናይ አድርጎናል፡፡ በግነት ስልት ለልመና ማሰልጠኛ በማቋቋም ሰርተው የሚለወጠውን የሰው ሀይል በልሂቃን አማካኝነት ወደ ስንፍና አስተሳሰብ ሲቀየሩ ያሳየናል፡፡ ልሂቃን በእርዳታ ስም ሱፍ ለብሰው ፕሮጀክት ነድፈው በየተቋማት እየዞሩ በመለመን የስራ እድል ለመክፈት ነው፤ የሚለውን የማስመሰል አጀንዳ ይዘው የሚዞሩት የራሳቸውን ኑሮ ሳይሰሩ ለማመቻቸት እና የሚሰራውን የሰው ልጅ አእምሮ በእርዳታ ስም እየገደሉት መሆኑን ለማስገንዘብ እና ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ለመጠቆም የቀረበ ነው፡፡ ለዚህም ማሳያ በመንግስት ተቋማት ውስጥ ሀብት አፈላላጊ የሚል መዋቅር ተዘጋጅቶ ለልመና ተቋም ተዘጋጅቶለት እናገኛለን፡፡ ይህን ተቋም በስላቅ መንገድ ሲተች እናያለን፡፡

አልዓዛር፡- ምን ነበር የምትሰሩት?

ጥጋቤ፦ እ…ያው እሷ ጡቷን ደረቷን የእንቁላል አስኳል ቀብታ ስትተኛ ፤ እኔ ደግሞ ዝምቦቹን በጭራ እያባረርኩ /በዜማ/…"አይን አይቶ ልብ ይፈርዳል፤ ስቃይዋን እያየ እንዴት ይጨከናሉ፡፡ ወገን ተረዳዳ ኪስህንም ዳብሰዉ፤ ስጣት ከገንዘቡ ቁስሉን ትታከመዉ… / ያለ ዜማ/ እያልኩና ያው በሽታዉ ባይኖርባትም …በማስመሰል…

አልአዛር፦ቁጭ በል፡፡ …በስክሪን ከሽሬጅ እንኳ ብዙም ውጤት እንዳልተገኘ፤ አንዴ አምና የተመረቀ ቤጊዮሎጂስት በመመረቂያ ጥናቱ አስፍሮታል፡፡ …ሰፊ ቁስልን ማሳየት ከማራራትና ከማሳዘን ይልቅ የማስደንገጥ ኃይል ከፍተኛ ስለሆነ፤ ሰው እጁን ለምፅዋት ከመሰንዘር ይልቅ ፊቱን አዙሮ ፍጥነት ጨምሮ እንደሚጓዝ ነው የተረዳው፡፡ በተለይ መርካቶ አካባቢ ትንሽ ቁስል ለማሳየት ሲል እርቃናቸውን መጋደም ስለሚወዱ… ቁስል ሳይሆን እናቱ እንደ ፈጠረችው ራቁቱን ተንጋሎ መታየቱ ሰውን እንደሚያስበረግግ ሲግመን ሮይድም ፅፍታል፡፡

አስናቀች፦(ድንገት ተነስታ)…እኔ ግን ከወገቤ በላይ ብቻ ነበር የማወልቀው፡፡

አልዓዛር፦ደህና ግሩም ነው…የተቀረውንና ከወገብ በታች የሚያስወልቀውን በሌሎቹ ኮርሶቻችሁ ትማሩታላችሁ፡፡ በነገራችን ላይ ስንት አመትሽ ነዉ? (ጌታቸው ታረቀኝ፣2013፣15-14)

የማስመሰል ልመና አካልን ከማጋለጥ እስከ አሳዛኝ የአካል ጉዳት ድረስ ሲገለጽ ግነት ተጠቅሞ የቀረበ ነው፡፡ የእውነት ተቸግረው መንገድ ላይ የወጡ ሰዎች ሰው በአግባቡ እንዳያግዛቸው እና የእለት ጉርሳቸውን እንዳያገኙ የሰለጠኑት ለማኞች ፈተና እንደሆኑባቸው ያሳየናል፡፡ ከዚህም ባለፈ የሰለጠኑት ለማኞች በቂ ስልጠና ተሰጥቷቸው ልመናው ካልተሳካ ሰዎችን በማማለል ለወሲብ መጋበዝም አንዱ የገንዘብ ማግኛ ስልታቸው ነው፡፡ በተለይ በየቡና ቤቱ እና በየመንገዱ ዳር ቆሞ እራስን አጋልጦ ለወሲብ ሰዎችን መገፋፋት ሌላው የገንዘብ ማግኛ ስልታቸው እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ የእውነት ተቸግረው ይህንን ስራ ለሚሰሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ህብረተሰቡ አዝኖ እንዳይረዳቸው እና ከችግራቸው እንዳያወጣቸው ማነቆ መሆኑን ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡፡ ለስላቅ የቀረቡትም ሳይሰሩ በሀብት ለተንበሸበሹ የማህበረሰብ ክፍሎች እና እያወቁ ሀገር ለሚገሉ ተማርን ለሚሉ ልሂቃን ነው፡፡

***በሽልማቱ*** ተውኔት ውስጥ ግነታዊ ስላቅ እናገኛለን፡፡ ስላቁም በአንድ ድርጅት ውስጥ የተሻለ አፈጻጸም ላላቸው አካላት በተዘጋጀ ሽልማት ላይ ነው፡፡ ሽልማቱንም የሚሸልሙ ኮሚቴዎች ተደራጅተዋል፡፡ ነገርግን እነዚያ ኮሚቴዎች ሽልማቱን በሙሉ ሲወስዱ ያሳየናል፡፡ በዚህ ተውኔት ውስጥ አንድን ጥፋት አጥፍቶ አላጠፋሁም ለማለት የማስመሰል ልቅሶ በኮሚቴው ሰብስቤ ንግግር ሲፈጸም እናያለን፡፡

> እንዴት ያሉ ጠንካራ ሰዎች መሰሏችሁ…በዉነቱ በእነኚህ አባላት ያላሰለሰ ጥረትና አስተባባሪነት የተከናወነዉን ታላቅ ተግባር ሳስበዉ…በእዉነቱ ከደስታ ብዛትም ሊሆን ይችላል …አልቅስ አልቅስ ይለኛል (ያለቅሳል) ይቅርታ…ይቅርታ..ግን ይገርመኛል…እስቲ አሁን እኛ ምን አደረግን? …እ? …እ?…ምን አደረግን? ...ገና የሰራነዉ ስራ በስርአቱ ሳይታይ …ሳይመረመር…‹‹በዘመድ ነዉ፡ በትዉዉቅ ነዉ፡፡ በጉቦ ነዉ››… ተብሎ ለምን ይወራብናል? …እ?…እ? …ይሁንና ዛሬ ሁሉንም በአደባባይ ለማዉጣትና ወሬኛዉንም አፉን ለማስያዝ እነሆ ከፉታችሁ ቀርበናል፡፡
>
> (ጌታቸው ታረቀኝ1983፣172)

የኮሚቴው ሰብሳቢ ስህተታቸውን ለመሸፈን እና የሰሩት ስራ ተአማኝነት ለመግለጽ በሚያደርጉት ንግግር ውስጥ ስላቅ እናገኛለን፡፡ ኮሚቴዎቸው የተጣለባቸውን የመንግስት አደራ ወደጎን ትተው ለራሳቸው ጥቅም ብቻ በማሰብ የተዘጋጁትን ሽልማቶች በሙሉ ለራሳቸው ያደረጉ ቢሆንም የሰብሳቢው ንግግር ግን ፍጹም ተአማኒነት ያለው የኮከብ ሰራቸኞች የሽልማት ምልመላ እንደተደረገ በመግለጽ ሙሰኞች መባላችን ስህተት ነው፡፡ እኛ የምንሰራው ስራ በአደባባይ የሚታይ ስለሆነ በሰጣችሁን ስም ታፍራላችሁ በማለት ሲገልጽ እናያለን፡፡ በዚህ ሀሳብ ውስጥ ተንጸባርቆ የምናየው ሳይቀድሙኝ ልቅደም ብለው እድሉን ስላገኙ ብቻ በየመድረኩ የራሳቸውን ንጽህና ራሳቸው የሚናገሩ ባለስልጣናትን ለመተቸት የቀረበ ነው፡፡ “ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሀል” የሚለውን የህዝብ ምሳሌያዊ አነጋገር እንድናስታውስ የሚያደርግ ነው፡፡ በስላቁም ባለስልጣናትን ለመገሰጽ ጥረት የተደረገ ሲሆን ንግግራቸው እና ተግባራቸው እንዲመሳሰል፤ ለራስ ጥቅም ሳይሆን ለህዝብ ጥቅም እንዲቆሙ ለመገሰጽ ተሞክሮበታል፡፡

በተለይ የባለስልጣናቱ ስግብግብነት እና ማን አለብኝነት በግነት መንገድ እንደሚከተለው ተንጸባርቆ እናገኛለን፡፡

> …እንግዲህ ዛሬ ባልመጣዉ የኮሚቴ አባል ስም ጭምር…ለምን እንዳልመጣ አናዉቅም …አሁን እስቲ ምን የሚያሳፍር ነገር አለ?… እሱን ብሎ ‹‹ተፈራ ኪዳኑ››፤ ምቀኛና የስልጣን ጥማተኛ መሆኑን እናዉቃለን፡፡ ለእሱ ያዘጋጀነዉን ሽልማት…እጣ አዉጥተን አንዳችን እንወስደዋለን…ቅጥል ይበል ቢፈልግ፡፡ ደሞም ‹‹ሌላ ቦታ ስራ እፈልጋለሁ›› ሲል ነበር አሉ፡፡ ለምን ጥርግ አይልም…
>
> (ጌታቸው ታረቀኝ፣1983፣178)

ኮሚቴዎቹ የተዘጋጀውን ሽልማት ቦታ እየተቀያየሩ ጠቅልለው ከመውሰዳቸው በተጨማሪ በእነሱ ውሳኔ አልስማማም ያለውን የኮሚቴ አባል እራሳቸው እጣ ተማተው ሊወስዱ እንደሚችሉ በሰብሳቢው በሰብስቤ አማካኝነት ሲገለጽ እናያለን፡፡ ይህ የሚያሳየን ለህዝብ የቆመ ባለስልጣን ከስርአቱ እንደሚወገድ እና ያገኝ የነበረው የስራ ጥቅማጥቅም እንደሚነጠቅ ያሳየናል፡፡ የኮሚቴ አባላቱ የሚያደርጉት የማን አለብኝ የስራ እንቅስቃሴ በስልጣን ላይ ያሉ አካለት እያደረጉ ያለውን ሁኔታ የሚያሳይ ሲሆን ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ እና ለኔ የሚለውን የእኔነት ፍላጎት ትተው ለህዝብ መቆም እንዳለባቸው ለመጠቆም ጥረት ተደርጎ እናገኘዋለን፡፡ በተለይ በሽልማቱ ያልተገኘውን ኮሚቴ ስብዕና ተከትለው እንዲያገለግሉ የሚያሳይ ነው፡፡ ስላቁ የቀረበበት ሁኔታ ግነትን በመጠቀም ነው፡፡

## 3.1.2 ማዛባት

***በሳጥናኤል አበሳ*** ተውኔት ላይ ሌላው ተንጸባርቆ የምናገኘው የስላቅ ዘዴ ማዛባት ነው፡፡ እንደ *ሀሪስ* ገለጻ ማዛባት የሚያመለክተው “የአንድን ሁኔታ ወይም ክስተት እይታ በመነጠል ወይም አንዳንድ ገጽታዎችን በማጉላት እና ሌሎችን በማደብዘዝ የመገለጽ ነው” (ሀሪስ፤ 1990)፡፡ ማዛባት አንድን ነገር ከነበረው በተቃራኒው መንገድ መጠቀምን የሚያመለክት ነው፡፡ በዚህ ተውኔት ውስጥም የመላዕክት እና የሀይማኖት አባቶች ስራ በተዛባ መንገድ ተገልጾ እናገኛለን፡፡ በተጨማሪም የሀዘን ስርአት በተዛባ መንገድ ተንጸባርቆ እናገኛለን፡፡ ከመላእክት አገልግሎት አንጻር ቅዱስ ጴጥሮስ በሀይማኖት አባቶች ዘንድ የሙታን ፋይል ያዥ ተደርጎ ሲገለጽ ፤ በሳጥናኤል በኩል ደግሞ ክፋትን እንዲተው እና መልካም አሳቢ ለመሆን ሲፈልግ እንደ ፈቃጅ

ተደርጎ ተገልጧል። ነገር ግን የቅዱስ ጴጥሮስ ተግባር በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖታዊ አስተምሮ የሚታወቀው ሀዋሪያ ስለሆነ የማስተማር ተግባር ነው። በተለይ የቅዱስ ጴጥሮስ አገልግሎት ከሀዋሪያነት ባለፈ እግዚያብሔር የሰውን ልጅ እንዲጠብቅ አደራ የተሰጠው ነው። የመንግስተ ሰማያት ቁልፍ ያዥ እንደሆነ እና የሀይማኖቱ ተከታዮች ንስሀ ሲገቡ መንግስተ ሰማያት እንዲከፈትላቸው ለቅዱስ ጴጥሮስ አደራ እንደሚሰጡ በሀይማኖቱ አስተምሮት ውስጥ እናገኛለን። ለዚህ ማሳያ የሚሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ ሀሳብ ማየት ይቻላል።

> እርሱም፣አላቸው። ሰምኦን ጴጥሮስም መልሶ፣ "አንተ ሕያው የእግዚያብሄር ልጅ ክርስቶስ ነህ" አለው።ጌታችን እየሱስ ክርስቶስም መልሶ እንዲህ አለው፣ "የዮና ልጅ ስምኦን ሆይ ፣አንተ ብፁኅ ነህ ፤በሰማይ ያለው አባቴ እንጂ ስጋ ይህን አልገለጠልህምና።እኔም እልሀለሁ አንተ አለት ነህ፤በዚች አለት ላይም ቤተ ክርስትያኔን እሰራለሁ፤የሲኦል በሮችም አይበተቱባትም።የመንግስተ ሰማያትንም መክፈቻዎችን እሰጥሀለሁ።በምድር የምታስረው በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የምትፈታው በሰማይ የተፈታ ይሆናል።(ማቴ.16፥15—19)

ስለዚህ የቅዱስ ጴጥሮስ ተግባር ከላይ የተገለጸው ቢሆንም በሳጥናኤል አበሳ ተውኔት ግን በተዛባ ስላቅ ዘዴ እንደ ማመልከቻ ተቀባይ ሆኖ ተገልጾ እናገኘዋለን። በተጨማሪም ቅዱስ ጴጥሮስ የሰውን ልጅ እንዲጠብቅ አደራ እንደተሰጠው በሀይማኖቱ አስተምህሮት ውስጥ እናገኛለን። "የዮናስ ልጅ ሰምኦን ጴጥሮስ ሆይ ፣ በጎቼን ጠብቅ፣ ጠቦቶቼንም አሰማራ፣እንኪየስ ግልገሎቼን ጠብቅ" ።(ዮሐ 21፥15—17) ነገር ግን በዚህ ተውኔት ተግባሩ ተዛብቶ የሚጸድቁ እና የሚኮነኑ ሰዎች ማመልከቻ ተቀባይ እና ፋይል ያዥ ሆኖ እናገኘዋለን። ለዚህም ማሳያ የሚሆን ከተውኔቱ ማየት ይቻላል።

እናት፡- ቦታ ሞላ?…የምኑ ነዉ ቦታ የሚሞላዉ?

ነፍስ አባት፡-(የስልኩን አፍ ሸፍነዉ ..በሹክሹክታ) ..መንግስተ ሰማያት ቦታ የለም ነዉ የሚሉኝ… ሀሎ…እዚህኮ አስመስክረን…ቃለ ጉባኤዉን ሁሉ ኮፒ አርገን….አያይዙ የተባለነዉን ሁለ አሟልተን ነበርኮ የላክነዉ…መቼም ቅደስ ጴጥሮስ ሁኔታዉን አይተዉ…ምንአሉኝ?

እናት፡-    አባታችን በደምብ ያስረዱልን… ቅደስ ጴጥሮስን ያናግሩልኝ…ለሱ የሚሆን ቦታ አያጡም…

(ጌታቸው ታረቀኝ፣2007፣6)

በህይወት ዘመኑ ጥሩ ስራ ሰርቶ የማያውቀው ሚች በመጨረሻው ሰአት የማስመሰል ንስሀ በመግባት በማመልከቻ እና በሰነድ ማስረጃ ወደ መንግስተ ሰማያት ለማስገባት ሲደረግ የነበረው ጥረት ባለመሳካቱ ቅዱስ ጴጥሮስ ጉዳዩ በማመልከቻ እንደደረሰው እና ጉዳዩን ቢሰማ ሊፈጽመው እንደሚችል ከነፍስ አባትየው ከሰማይ ቤት ካሉ ቅዱሳን መላእክት ጋር ባለው የስልክ ምልልስ መረዳት እንችላለን፡፡ ስለዚህ የቅዱስ ጴጥሮስ አገልግሎት፣ የነፍስ አባቶች አገልግሎት እና  ሰማይ እና የምድር ሚስጥራዊ ግንኙነት ከመንፈሳዊነቱ ይልቅ አለማዊ በሆነ የአሰራር ሂደት በመቀየር ድርጊቱን በተዛባ የስላቅ ስልት ሲቀርብ እናያለን፡፡ የነፍስ አባትየው የመንግስተ ሰማያት መሙላትን ለሚች እናት ሲገልጽ  የስልኩን አፍ ሸፍኖ በሹክሹክታ ነው፡፡ ይህ ድርጊት ሳቅን እና ግርምትን የሚፈጥር ሲሆን መዛባቱ ደግሞ ቅዱሳን መላእክት በግልጽ ካልተነገራቸው የማይሰሙ እና የማያዩ የሰው ልጅ ባህሪ ያላቸው ፍጡራን ተደርገው ቀርበው እናገኛለን፡፡ በተውኔቱ ውስጥ በማዛባት ስልት በምድር ላይ ያልሰራነው ጥሩ ስራ በፍትሀት እና በልመና ሊስተካከል እንደማይችል አሳይቶናል፡፡ የሀይማኖት አባቶችም ሰው ሲሞት በፍታት ነፍስን ወደ መንግስተ ሰማያት ለማስገባት ከመጣር ይልቅ የሰው ልጅ በህይወት እያለ ሀይማኖታዊ ስርአቱ በሚፈቅደው መንገድ እንዲኖሩ ማስተማር እንደሚገባ ያሳያል፡፡

ሌላው ***በሳጥናኤል አበሳ*** የቀረበው የማዛባት ስልት  የሀይማኖት አባቶችን ከሀይማኖታዊ አገልግሎታቸው ይልቅ የሚሰጡት ሀይማኖታዊ አገልግሎት ገንዘብ ተኮር መሆኑን ሳጥናኤል ንስሀ ገብቶ ወደ ሰው መቀየር ሲፈልግ የሳጥናኤል እናት የሰው ልጅ እንድትቀየርባቸው አይፈልጉም ፤ በአንተ እያሳበቡ መኖር ይፈልጋሉ እባክህ አትልፋ ትለዋለች፡፡ ሳጥናኤል ግን ክፋት በቃኝ ብሎ መቀየር ፈልጎ የደጋጎች ሀገር ኢትዮጵያናት ብሎ ወደ ኢትዮጲያ መጥቶ መቀየር እንደሚፈልግ ሀይማኖታዊ አገልግሎት ለሚሰጡ አካላት ሲነግራቸው፤ የሳጥናኤል መቀየር በአለም ላይ ሊፈጠር የሚችለውን ሰላም በማሰብ ሳጥናኤል እንደኛ ሰው ከሆነማ ማንን እናጠምቃለን፣ሰውና ሰው ሲጣላ በማን እናሳብባለን ፣ነጭ የነበረውን ሳጥናኤል ጥቁር ነው ብለን የነገርነውን ትርክት እንዴት አድረገን ለአፍሪካውያን እንናገራለን የሚሉ ስጋቶችን በመደርደር ሳጥናኤል እንዳይጠመቅ እና ንስሀ ገብቶ እንደሰው ልጅ በሰላም እንዳይኖር

ሲከለከል እናያለን፡፡ ነገር ግን የሀይማኖት አባቶች ተግባር በየትኛውም ሀይማኖት በአለም ላይ ሰላምና ፍቅር እንዲኖር መስበክ ነው፡፡ ሳጥናኤል ወደ ሲኦል የተወረወረው ፈጣሪውን ክዶ እንደሆነ በሀይማኖት አስተምህሮት ውስጥ ሲሰበክበት እናያለን፡፡ በዚህ ተውኔት ውስጥ የሀይማኖት አባቶች ተግባር ተዛብቶ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ትርጉም ተሰጥቶት ሲገለጽ እናያለን፡፡ ለማሳያ የሚከተለውን ማየት እንችላለን፡፡

> ሳጥናኤል፡- አዎ ክፋት መስራት ሰለቸኝ..በእኔ የተነሳ ብዙ ሰዉ ተንገላታ..ብዙ ቤትም ፈረሰ…እርሰዎንም ጨምሬ ብዙ ህዝብ አስቀየምኩኝ…ስለዚህ ሁሉን የሚምረዉ ጌታ እንዲምረኝ እዚሁ አጥምቁኝና..የእርስዎ አገልጋይ ልሁን…እዚህ እንደሰዉልኑር…
>
> ሰዉየዉ፡- (ወዲህና ወዲያ ይላል. እሱ ከስር ከስራቸዉ ይከተላል)…እና አንተ አሁን ብትጠመቅ በምድር ላይ ክፋትና መጠላለፉ ሊቀር?...የሚያብደዉ የተለከፈዉ ሁሉ ሊጠፋ?…እና ..ይሄ ሰይጣን ለከፈኝ እያለ በሌሊት የሚመጣዉስ?
>
> ሳጥናኤሌ፡- እኔ ከተጠመቅኩማ ማንም አይለከፍም፡፡ ማንም የሚመጣ የለም..እርስዎም ደስተኛ ይሆናሉ…በሌሊት በዉርጭ ተነስተዉ ያንን ቀዝቃዛ ጠበል መንካት የለብዎትም…አርፍደዉ ይተኛሉ…እሜትዬም ደስ ይላቸዋል…እርስዎም ያንን የሚወዱትን የአናጢነት ሙያ ለማበልፀግ ጊዜ ይኖርዎታል…የኢንቨስትመንት ፈቃድ አዉጥተዉ ብዙ ሰዎችን መርዳት ይችላሉ…እዚህ ሰይጣን ያዘኝ ከሚለዉ ሁለት ሁለት ብር ከሚነጥቁት ያኛዉ ይሻልዎታል…ግርማ ሞገስ ይሆንዎታል…ከእሜትየ ጋርም ተቃቅፈዉ ተኝተዉ ያረፍዳሉ…
>
> (ጌታቸው ታረቀኝ፤2007፤24-26)

ሳጥናኤል ወደ ኢትዮጵያ ሄዶ መጠመቅ እና መዳን ሲፈልግ የመጀመሪያው የማንነት ጥያቄ እንደሚቀርብበት በሁለተኛ ደረጃ ሰውየው ማጥመቅን እንደ መደበኛ ስራ ቆጥሮት ሳጥናኤልን ለማጥመቅ ሲቸገር እናያለን፡፡ ይህ የቀረበበት በማዛባት ቴክኒክ ነው፡፡ የሀይማኖት አባቶች ከመደበኛው የሀይማኖት ተግባር ወጥተው ለጊዜያዊ ጥቅም በማሰብ ሀይማኖታዊ አገልግሎት

ሲጥሱ የሚያሳይ ነው፡፡ ስላቁምየተሰጣቸውን ሀይማኖታዊ አገልግሎት በሚጥሱ አባቶች ላይ ነው፡፡ በተለይ በሀይማኖት አባቶች ዘንድ እየታየ ያለውን የገንዘብ ፍቅር የሚገስጽ ነው፡፡ ለሀይማኖት አባቶች  እግዚያብሄር ፈቅዶ ከሰጣቸው አይማኖታዊ አገልግሎት  እየራቁ መሆናቸውን ለማሳየት ሀይማኖት ለሚቀበል ምእመን ሀይማኖታዊ ትምህርት ከሚሰጡ ይልቅ የማንነት(የብሄር) ጥያቄ እንደሚያነሱ፣ ከሰው ልጅ ደህንነት ይልቅ ገንዘብ እንዲያስቀድሙ ተገልጾ የምናገኝ ሲሆን በዚህ ተግባር ላይ የተሰማሩ የሀይማኖት መሪዎች ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ለመገሰጽ ሞክሯል፡፡

> ሰዉየዉ፦ …ምን መሰለህ ወንድም ዲያቢልስ..አንተ ከተጠመቅክና ይሄን ደካማዉን ማሳበድ ማዘላበድ ካቆምክ…ምን እንበላለን?..ማለቴ ብዙ ችግር ይፈጠራል… መቅደሱን ሳይቀር ልናከራየዉ ነዉ ማለት ነዉ…የጀመርነዉ ኢንቨስትመንትም ይፈርሳል…
>
> (ጌታቸው ታረቀኝ፣2007፣26)

በኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት ውስጥ የአባቶች አገልግሎት አማኙን ከሳጥናኤል ጥፋት መጠበቅ እና በአለም ላይ ሰላም፣ፍቅር፣መተሳሰብ እንዲኖር እኩይ ተግባር እንዲጠፋ መስበክ ፣ እና ሀይማኖታዊ አገልግሎት መስጠት ነው፡፡ ከእነዚህም አገልግሎቶች ውስጥ አንዱ ማጥመቅ ነው፡፡ ማጥመቅ አንድም ከሀጥያት ለመንጻት በሌላ በኩል ከበሽታ ለመዳን የሚፈጸም ሀይማኖታዊ ስርአት ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ተውኔት ውስጥ ሳጥናኤል ከተጠመቀ ማበድ መወንበድ እንደሚቀር ካዛም አልፎ ተርፎ መቅደስ እንደሚዘጋ አጥማቂው ሰውየ ሲገልጹ እናያለን፡፡ እዚህ ላይ ምናየው ማዛባት ዘዴ የሀይማኖት አባቶች ከትክክለኛ ተግባራቸው በተቃራኒው የተገለጹ ሲሆን ከመደበኛው ሀይማኖት አገልግሎት ውጭ ለተሰማሩ አስመሳይ አገልጋዮችን ለመገሰጽ ታስቦ የቀረበ የስላቅ ዘዴ ነው፡፡

በሌላ በኩል የእስልምና ተከታይ የሆኑትን እርዚቁን ሳጥናኤል  ሰው መሆን እንደሚፈልግ ሲገልጽላቸው እርዚቁ ሳጥናኤል የሌላቸውን ገንዘብ እንዲኖራቸው ስላደረጋቸው ሰው ከሚሆን ይልቅ ለእሳቸው ገንዘብ እየሞላ አብረው እንዲኖሩ ሲያግባቡት እናያለን፡፡ ሳጥናኤል ግን ሰው ከሆንኩ ብር መስጠት አልችልም ሲላቸው ሳጥናኤልን ወደ ሰውነት በመቀየር ከእኩይ ተግባሩ ከማላቀቅ ይልቅ ሰይጣን እንደሆነ እዲቀጥል ሲያግባቡት ይስተዋላል፡፡ ይህም በማዛባት ዘዴ የሀይማኖት አባትነን ባዮች ላይ ሲሳለቅ እናያለን፡፡

ሳጥናኤል፡- ጋሽ እርዚቁ..ስለቸኝ..ክፋትና ተንኮል በቃኝ…በዚያ ላይ ደሞ..ይሄ ካላቅሙ ልኩን ሳያዉቅ እየበላ ቁንጣን ሲቀፈድደዉ..የሰራዉ ሀጢአት በርክቶ ሌት እንቅልፍ የሚያሳጣዉ..አረቄዉን ግፎ ቱቦ ዉስጥ የሚገባዉ…‹ሰይጣን ነዉ እንዲህ ያደረገዉ የሻጠረዉ› እየተባለ ስሜን የሚያጠፋዉ ስለበዛ እርስዎ ይርዱኝና ቁርአኑን ያስቀሩኝ…ምህረቱን አሰጡኝ..መስጊድ ይዉሰዱኝ..ክፋትና ተንኮል ሰለቸኝ…አለምን ይቀይሯት ጋሽ እርዚቁ…ሰዉ ይድርጉኝ..

እርዚቁ፡- አንተ ከተቀየርክማ አለምን ምኗን ቀየርኳት …የምቀይራትስ አንተ እሺ ብትለኝ እንዲህ ብሩን በሳጥን ብትሞላልኝ…አገሩን ሁሉ በገዛሁኝ…ፎቁን ሆቴሉን እየሰራን አብረን በከበርን…የጫት ጭማቂ ማሽን አስተክለን…አለሙን ሁሉ ባከፋፈልን ነበር አለምን የምንቀይራት …ግዴለህም እሺ በለኝና…አንተ ሰዉ ከምትሆን እኔን ሰዉ አርገኝ…እዚህ ጋ አስነጥፍልሀለሁ…

ሳጥናኤል፡- እኔማ ከተቀየርኩ…እዛዉ ተመስጊዴ ነዉ የምውለዉ..

እርዚቁ፡-መስጊድ ምን ትሰራለህ?...ግፊያዉን አትችለዉም ብትሄድ …እዚሁ አስተማሪ ቀጥሬ ትማራለህ…ይልቁንስ ስንት ቢዝነስ አለ መሰለህ…ብዙ ሰዎችንም አስተዋዉቅሀለሁ….

(ጌታቸው ታረቀኝ ፣ 2007፣29)

እርዚቁ ቁርአን የማስቀራት እውቀት ያለው፣ ምህረት ማሰጠት የሚችል(ጸሎቱ የሚሰማ) በእስልምና እምነት ውስጥ ሀይማኖታዊ ስልጣን ያለው ሲሆን ሳጥናኤል ወደ ሰው መልሰኝ ሲለው ሀይማኖታዊ አገልግሎት ከመስጠት እና አምላኩን በስራው ከማስደሰት ይልቅ በጊዜያዊ ምድራዊ ጥቅም ተታሎ ሳጥናኤልን አንተን ሰው ከማደርግህ እኔን ሰው አድርገኝ ፤አብረን እንስራ ዓለምን የምናድናት ብዙ በመስራት እና በመበልጸግ ነው፤ ስለዚህ እባክህ አትቀየር እያለ ሲለምን እናያለን፡፡ ስላቁ መደበኛ ስራቸውን ትተው በጊዜያዊ ጥቅም ለታለሉ የሀይማኖት አባቶች የሚገስጽ ነው፡፡ በዚህ ሀሳብ ውስጥ ለስላቅ ቀርበው የምኛገኛቸው የሀይማኖት አባቶችን

ነው፡፡ ስላቁም የሀይማኖት አባቶች ወደ መደበኛ ስራቸው ተመልሰው ለሰው ልጅ ሔማኖታዊ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚጠቁም ነው፡፡

***በቤጊዮሎጂ*** ተውኔት ውስጥ ማዛባት  እናያለን፡፡ ምሁራን ለአንድ አገር እድገት እና ስልጣኔ ወሳኝ አካል ሆነው ሳለ በዚህ ተውኔት ውስጥ የምሁራን አገልጋሎት ተገልብጦ ለልመና ፣ ለስንፍና እና ለእርዳታ ወሳኝ የስልት አቀናባሪ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

> አልዓዛር፡- (ያነባል)…ክቡር የማዕከሉ ዋና ስራ አስኪያጅ ክቡር ዶክተር ፕሮፌሰር ኢንጂነር አቶ ተሰማ መቅደሱ፤ ውድ የቤጊዮሎጂ ሊቀ ሊቃውንት መምህራን፤ ክቡራን እንግዶችና እንዲሁም …(ለተመልካች) … በዚህ አመት ወደ ማዕከላችን የገባችሁው ጀማሪ ተማሪዎች፤ እንኳን ለዚች ለተቀደሰች ቀን አደረሰን፡፡
>
> (ጌታቸው ታረቀኝ ፣2013፣2)

የተማሩ ሰዎች የስራ ድርሻ ሀገርን ማገልገል፣አዳዲስ ሀሳቦችን ማፍለቅ እና ለሀገር እንድታድግ እና ስራ አጥነት እንዲወገድ በማድረግ ሀገርን ማሳደግ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ተውኔት ውስጥ የምሁራን ስራ በማዛባት የልመና አስፋፊ እና መምህር ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ አልአዛር ተሰማን ሲያስተዋውቅ ምሁር እንደሆነ እና በስብሰባው ውስጥም ልሂቃን እና መምህራን እንዳሉ ይገላጻል፡፡ እነዚህ ምሁራን ግን የተገለጹት ለሀገር መፍትሄ ለማምጣት ሳይሆን ልመናን ለማስፋፋት መሆኑን እናያለን ይህም የምሁራን ተግባር ተዛብቶ በስላቅ መልኩ ቀርቧል፡፡ በዚህ መልኩ የምሁራን ተግባር የቀረበበት መንገድ ከረባት አስረው ያወቅን መስሏቸው ሳያውቁ ህዝብን በማደናገር የተዛባ መልዕክት በማስተላለፍ ሀገርን ወደ አዘቅት እየከተቱ ያሉ ስመ ምሁራንን ለመገሰጽ ነው፡፡ በሀገር  እድገት ውስጥ የምሁራን ድርሻ ትልቅ ሆኖ ሳለ መማራቸውን ለራስ ጥቅም ማግኛ ብቻ ያደረጉ ምሁራን አሉ፡፡ እነዚህ ምሁራን ከግለኝነት አስተሳሰብ ወጥተው ለሀገር የሚበጅ ቁም ነገር እንዲሰሩ የተገለጸበት ስላቅ ነው፡፡

ሌላው በዚህ ተውኔት ውስጥ ተዛብቶ የቀረበው ጸሎት እና ምርቃት ነው፡፡ ጸሎት የሰው ልጅ ከአምላኩ እንዲሆንለት እና እንዲደረግለት የሚያደርገው ልመና ሲሆን ምርቃትም የሰው ልጅ ከአምላኩ እንዲደረግለት ከሌላ አካል የሚለመን ጸሎት ነው፡፡ ነገር ግን በቤጊዮሎጅ ተውኔት ውስጥ ግን ጸሎት እና ምርቃት በማዛባት ዘዴ ለስላቅ ተግባር ቀርቦ እናገኛለን፡፡

"…(አይናቸውን ጨፍነው እጃቸውን ወደፊት ይዘረጋሉ) …ሀይ ሀይ …ሁይ

ሊቃዉንቱ፡-(ተነስተዉ እጃቸዉን ዘርግተዉ ይቆማሉ) …ሀይ ሀይ …ሁይ

ተሰማ፡- ገንዘብ፣ መሬት፣ ቤት፣ መኪና!

ሊቃዉንቱ፡- …ግቢ ወደ ቤቴ ሰተት በይና!

ተሰማ፡- የፈረንጅ ብር ዶላር

ሊቃዉንቱ፡- ዩሮ፤ የን፤ ሩብሌ ጭምር

ተሰማ፡- ሽልንግ፣ እስተርሊንግ ሳይቀር፤ ኮለል ይበል በቤታችሁ ይደርደር

ሊቃዉንቱ፡- ግቡ ከቤቴ እንበል እልል

ተሰማ፡- የአገሩ ብር ይክሰር

ሊቃዉንቱ፡- እንደ ዚምባቡዌዉ ዶላር!

ተሰማ፡- እንበል እልል ምቀኞችን ይከንበል

ሊቃውቱ፡- ጠላታችን እርር ይበል….

ተሰማ፡- ጦርነት፣ ረሀብ እና ሽብር ይስፋፋ,

ሉቃዉንቱ፡- ታላቁ ሳይንሳችን ከአጥናፍ አጥናፍ ይስፋፋ!!

ተሰማ፡- …ሀይ ሁይ …ሁይ ሀይ

ሉቃዉንቱ፡- …ሀይ ሁይ …ሁይ ሀይ… (ይቀመጣሉ)

(ጌታቸው ታረቀኝ ፣2013፣6-7)

ተሰማ ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ አይኑን ጨፍኖ፣ እጁን ዘርግቶ በጸሎት መልኩ ምርቃት ሲጀምር ሊቃውንቱም ከመቀመጫቸው ተነስተው አብረው እጃቸውን ዘርግተው ምርቃቱን ሲቀበሉ እናያለን። ይህም በተውኔቱ ውስጥ ስላቅ የሚታይ ሲሆን ስላቁም የቀረበበት ዘዴ በተዛባ መንገድ ነው። ምክንያቱም የተሰማ ጸሎት እና ልመና ሀገር እንዲረበሽ፣ ሳይሰሩ ተንደላቆ መኖር እና በሀገር ውስጥ የኑሮ ውድነት እንዲስፋፋ የሀገር ውስጥ ብር ዋጋ እንዲያጣ ዶላር ምንዛሬው እንዲጨምር ሲሆን ሊቃውቱም ይህን ልመና እና ምልጃ ሲቀበሉ እና አጉልተው ሲናገሩ እናያለን። ጸሎትና ልመናው በዚህ መንገድ የቀረበበት ምንገድ ለራሳቸው ጥቅም ብቻ ለሚጨነቁ የማህበረሰብ ክፍሎችን ለመገስጽ ነው። በተለይ የተሻለ የሀብት ገቢ ያላቸው እና በውጭ ሀገር ያሉ የዶላር ተከፋዮች በሀገር ውስጥ ያለው ብር ዋጋ ማጣት ለሚያስደስታቸው ማህበረሰቦች የቀረበ ትችት ነው። ምክንያቱም የዶላር መጨመር እና የሀገር ውስጥ ብር ዋጋ እንዲያጣ ስለሚያደርግ በህዝቡ ላይ የሚፈጥረው የኑሮ ውድነት የማያስጨንቃቸው ስግብግብ ነጋዴዎች እና ባለሀብቶች ተጠቃሚ ሲሆኑ አብዛኛው ህዝብ ግን ተጎጅ ነው። ይህንን ስግብግብነት ለመገሰጽ ጸሎት እና ልመና በተዛባ መንገድ ተንጸባርቆ እናገኛዋለን።

> ዛሬ አልፎ አልፎ ብቅ እያሉ የሚዘላብዱ የሳይንሳችን ምቀኞችም፤ ብን ብለዉ እንደሚጠፉ ቅዱሳን መፃህፍት ላይም ቁልጭ ብሎ ተቀምጧል ...ልምሳሌ በትንቢተ ኢሳያስ ምዕራፍ 51 ከቁጥር 7 እስከ 8 ያለዉን ብንመለከት...‹‹የሰውን ተግዳሮት አትፍሩ፤በስድባቸውም አትደንግጡ፤ እንደ ልብስም ብል ይበላቸዋል። አንደ በግ ጠጉርም ትል ይበላቸዋል...›› ተብሎ የተተነበየዉ እዉነት እየሆነ ነዉ።
>
> (ጌታቸው ታረቀኝ፣1984፣50)

በቢጊዮሎጅ ተውኔት ውስጥ ማሳደድ፣ማፈናቀል፣የሰውን ልጅ የተረጋጋ ህይዎት በመረበሽ ለራስ የልመና ስልት ማመቻቸት የሳይንሱ አላማ ሲሆን ሳይንሱን የማይቀበሉ ሰዎች ብን ብለው እንደሚጠፉ በቅዱሱ መጽሀፍ የተቀመጠውን የትንቢተ ኢሳያስ መልዕክት በማይመጣጠን አገላለጽ ሲጠቀም እናያለን።

### 3.1.3 ምጸት

*በሳጥናኤል አበሳ* ተውኔት ውስጥ ሌላው የሚታየው የስላቅ ዘዴ ምጸት ነው፡፡ ምጸት የቃሉ ፍቺ ፊት ለፊት ከምናየው ተቃራኒ የሆነበት ድርብ ትርጉም የያዘ ነው:: በስላቅ መልክ ምጸት መጠቀሙ ለአንድ ጉዳይ ወይም ነገር አጽንኦት እንዲሰጥ ያደርገዋል፡፡ ምፀት በቃላት ወይም በክስተቶች ከሚጠበቀው የተለየ እና ተቃራኒ የሆነውን እውነታ የሚያስተላልፍ የአገላለጽ ዘዴ ነው:: የተመልካቾች አስገራሚ እውቅና ብዙውን ጊዜ አስቂኝ ውጤት ያስገኛል፡፡ ይህም ምጸቱን አስቂኝ ያደርገዋል:: ሃሪስ (1990) ሲገልጽ"ምፀት ግብዞችን የማጥቂያ ዘዴ ነው"ይገልጻል፡፡ *በሰይጣን አበሳ* የቀረበው ምጸትም የሚች የህይወት ታሪክ ሲነበብ ሚች እንደተወለደ የሞተ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ይህንን ሀሳብ ከላይ ስናየው ሚች በህጻንነቱ ምንም ሳይሰራ የሞተ እንደሆነ የሚያመለክት ሲሆን ከሚች የህይዎት ታሪክ ግን የምንረዳው እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ ምንም አይነት መልካም ተግባር ያልስራ ከመፈጠሩ አለመፈጠሩ የሚሻል ከንቱ ሰው መሆኑን ለመግለጽ በምጸት ዘዴ ሲገለጽ እናያለን፡፡

> **የሚገርም አጋጣሚ ነዉ….ሰኔ ሃያ ሁለት ተወልዶ፤ ሰኔ ሃያ ሦስት የሞተ ማንም እንደሱ ያለ ሰዉ የለም** ….እድሜዉ ለትምህርት ሲደርስ ትምህርት ቤት ገብቶ ቢማርም ከተራ መሀይም የባሰ ጠማማ አስተሳሰብ የነበረዉ እጅግ ጠማማ ሰዉ ነበር…ገና በልጅነቱም የሌሎች ህፃናትን ልብስና መጽሐፍ መቅደድ፤ የሚማሩበትን መደበቅ የሚወድ ተንኮለኛ የነበረ ሲሆን በርግጥም የሰዎችን መልካም ስራ ለማራከስና ለማንቋሸሽ ተግቶ የሚሰራ እጅግ ምቀኛ የነበረ ሰዉም ነበር፡፡ **አጽንኦት የኔ**
>
> (ጌታቸው ታረቀኝ ፤2007፤3)

"ሰኔ ሃያ ሁለት ተወልዶ ሰኔ ሃያ ሦስት የሞተ ማንም እንደሱ ያለ ሰው የለም…" የሚለው የህይወት ታሪክ መግቢያ ስናይ ምጸት ነው፡፡ ሚች ምንም ሳይሰራ የሞተ ክፉ፤ምቀኛ፤ ለሰውልጅ በጎ ሳይሰራ እና ሳያስብ የሞተ መሆኑን ለመግለጽ ሲሳለቅ ምጸትን እንደ ቴክኒክ ተጠቅሞ እናገኛለን፡፡ ምጸት ለመሆኑም ቀጥሎ የቀረበው የሚች የህይዎት ታሪክ ሲነበብ እናያለን፡፡ ሃሪስ እንዳለው ምጸቱ የሚችን ስነ-ምግባር ምን እንደሚመስል ለመግለጽ የማጥቂያ

ዘዴ ሆኖ ሲተገበርበት እናያለን፡፡ ለዚህ የምጸት ዘዴ ሌላ ተጨማሪ ምሳሌ ከተውኔቱ ማየት ይቻላል፡፡

> ትዳር የሚባለዉን ባይመሰርትም በርካታ ልጆችን ከተለያዩ ሴቶች ማስወለድ ችሎ ነበር፡፡ አባት መሆን ቢያቅተዉም፡፡ እዉነትም አባ መስጠት...ቸር ነበር፡፡ ሁሉም ነበር የሚያዳርሰዉ... አጽንኦት የኔ
>
> (ጌታቸው ታረቀኝ፣2007፣4)

ሚች በየቦታው የሚወልድ ነገር ግን የአባትነት ጥያቄውን የማይቀበል የብዙ ልጆች አባት እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በዚህ ተውኔት ውስጥ በምጸት የቀረበው በየቦታው እየወለዱ የሴቶችን እና የልጆቻቸውን የወደፊት እጣ ፈንታ ያበላሹ ወንዶችን ለመገሰጽ ነው፡፡ በየቦታው ልጅ የሚወልዱ ወንዶች የመጀመሪያው በአንድ እንዲወሰኑ የሚገስጽ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለወለዱት ልጅ ሀላፊነት በመውሰድ የአባትነት ፍቅር እንዲሰጡ ለመጠቆም በምጸት መንገድ ቀርቦ እናገኘዋለን፡፡

በሌላ በኩል ሚች ለሰው የማያስብ፣ ከራሱ በላይ ለሌላ የማይጨነቅ፣ ብቻውን የሚበላ፣ ብቻውን የሚጠጣ፣ አጫሽ፣ ቃሚ፣ ዝሙተኛ፣ ምቀኛ እንደሆነ የህይዎት ታሪኩ ሲነበብ የሰማን ቢሆንም የሚች መግቢያ ገሀነም እሳት መሆኑ ሲታወቅ በአልቃሾች ዘንድ በምጸት መልኩ የሚች ስራ ሲገለጽ እናያለን፡፡ ለምሳሌ ከተውኔቱ የተወሰደ ሀሳብ ለማየት ብንሞክር፡-

> ለቀስተኞች፡-ገሀነበሳት የእሳት እራት... እሱ እንደሁ እርግማን የለበት...ሁሉም እያለዉ ዶክመት...የምን ገሀነበሳት...አባባ አባክዎ ይርዱት..አጽንኦት የኔ
>
> (ጌታቸው ታረቀኝ፣2007፣7)

ሚች እኩይ ተግባር እንዳለበት የህይዎት ታሪኩ ሲነበብ የተገለጸ ቢሆንም መንግስተ ሰማያት ሞልቷል ምትገባው ገሀነም ነው ሲባል አልቃሾች በምጸት እርግማን እንደሌለበት ይገልጻሉ፡፡ ምጸቱም እኩይ ተግባሩን ንስሀ በመግባት በማስመሰል እና ሌሎች የማሳመኛ ዘዴዎችን በንስሀ አባቱ አማካኝነት ዶክመት ቢያሟላም ጥሩ ስራ ካልሰሩ በሰነድ ጋጋታ እና በለቅሶ መጽደቅ እንደማይቻል ሲገልጹ እናያለን፡፡ ምጸት የቀረበባቸውም የማስመሰል የክርስትና ህይዎት

ባላቸው ሰዎች ላይ ሲሆን የክርስትናን ህይዎት በአግባቡ ካልኖሩበት እና መልካም ስራ ካልተሰራ መንግስተ ሰማይ መግባት እንዳማይቻል ለማስረዳት ጥረት ሲያደርግ እናያለን፡፡

*በቤጊዮሎጂ* ተውኔት ውስጥ ምጸት ዘዴ ተንጸባርቆ እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ፡-

> ዛሬ ቤጊዮልጂ ከብቸኛ ሳይንስነት አልፎም በየትኛውም ‹‹ሳይንስ ነኝ›› በሚል ጥናት ውስጥ በብልሃት መካተቱን እና ወደ ዘመናዊ የአኗኗር ዘዴ፤ ዋና መሰረትነት መሸጋገሩን ስናስተውል፤ **ሁላችንንም በሙያው እንድንኮራ አድርጎናል! አጽንኦት የኔ**
>
> (ጌታቸው ታረቀኝ 2013፣4)

ልመና በእርዳታ ሰበብ እንዴት ስር እንደ ሰደደ ፣ ህዝብን ከስራ ውጭ እያደረገው መሆኑን እና የልመና ስልቱም በታቀደ መንገድ እየተፈጸመ መሆኑን የሚገስጽ ነው፡፡ በዚህ ተውኔት ውስጥ አንዱ የምናገኘው ምጸት ተሰማ ለእንግዶች በሚያቀርብበት ንግግሩ ቤጊዮሎጂ በብልሀት ‹‹ሳይንስ ነኝ›› ከሚል ፍልስፍና ጋር መቀላቀሉን እና በዚህም ትልቅ ለውጥ እየመጣ እንደሆነ ሲገለጽ እናያለን፡፡ የተሰማ ንግግር ምጸት ነው ምጸቱም ልመና እንደ ሙያ ተቆጥሮ "ሁላችንንም በሙያው እንድንኮራ አድርጎናል" በማለት ሲገልጽ እናያለን፡፡ ነገር ግን ልመና የትም እንደማያደርስ እና የመጨረሻው መዳረሻ ስንፍና እና ድህነት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ በተለይ በእርዳታ እና በልመና ላይ የተመሰረተውን የመንግስት መዋቅር ለመተቸት የቀረበ ሲሆን ልመናው የትም ሊያደርስ እንደማይችል እና በልመና በመጣ ነገር ከመኩራራት ለሀገር የሚጠቅም ቋሚ የገቢ ምንጭ መንግስት ሊኖረው እንደሚገባ የሚጠቁም ነው፡፡ በሌላ በኩል ልመናን መተዳደሪያ አድርገው የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚገስጽ ሲሆን በልመና የትም እንደማይደረስ የተገለጸበት ስልት ነው፡፡

> አልአዛር፡- ሽብር አሪፍ ነገር ነዉ፡፡ ዛሬ በአሜሪካ ብቻ በትላልቅ ከተሞች አዉራ ጎዳናዎች ድልድዮች ስር እና በየድሀዉ መጠለያ የከተሙትን የቀድሞ ወታደሮች ብትመለከትና ለበርካታ የሳይሳችን ተጠቃሚዎች ትልቅ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ስትገነዘብ የበለጠ ይገባሃል፡፡ አሁን ያልዘመተዉ ጭምር የአበደበት ዘመን ላይ ነዉ ያለነዉ፡፡ አርቴፊሻል ፀጉር ሚፈልገው፤ ጡት፣ ዳሌና ቂጥ የሚያሳድሰዉ፤ ፆታዉን የሚቀይረው …ዘንድሮ በጣም ብዙ

ጉዳተኛ ነዉ ያለዉ፡፡ እንዳንተ አስተሳብ…ለምን ጦርነት እና ሽብር የሚወገድበት ሰላማዊ መንገድ አልተፈጠረም?…ለምን ህፃናትንና አዋቂዎችን የአካልም ሆነ የአእምሮ ጉዳተኛ የሚያደርጉ ችግሮች ላይ ትኩረት አልተደረገም ብለን ማለት አንችልም፡፡

ምስክር፡- ይሄንን ችግር ለሚፈጥሩት ሁሉ እንዲያዉም አለማቀፍ ሽልማት ሊሰጣቸዉ ይገባል!"

(ጌታቸው ታረቀኝ፣2013፣13)

በዚህ ተውኔት ውስጥ በአለም ላይ ሽብር የሚፈጥሩ ሰዎች ለመፈናቀል፣ላለመረጋጋት እና የሰው ልጅ ለችግር የሚጥሉ ስለሆኑ መሸለም እንዳለባቸው አልአዛር እና ምስክር ሲነጋገሩ እናገኛለን፡፡ ነገርግን የሽብር ጥሩነት የተገለጸው በምጸት ሲሆን ሽብርተኞች መሸለም አለባቸው የሚለው የምስክር ሀሳብም የቀረበው በምጸት መንገድ ነው፡፡ ምጸቱም ሽብር ለርሀብ እና ለችግር የሚዳርግ መሆኑን እና ይህንን ድርጊት የሚፈጽሙ ሰዎች መቀጣት እንዳለባቸው የሚያመለክት የስላቅ ስልት ነው፡፡ ነገርግን በዚህ ተውኔት ውስጥ መንግስት ለስላቅ ቀርቦ እናገኘዋለን፡፡ ጦርነት ላይ ቆይቶ የንጹሀን ዜጎች ደም ከፈሰሰ በኋላ ችግር የፈጠረው አካል ተገቢ የሆነ ቅጣት ሳይሰጠው በሰላም ሰበብ ተዳፍኖ ሲቀር ይታያል፡፡ የዜጎችን ደም ያላግባብ ማፍሰስ እና ተገቢውን ፍትህ አለመስጠት ልክ አለመሆኑን ለመግለጽ የተሞከረበት ነው፡፡

አልዓዛር፡- (ያነባል)…ክቡር የማዕከሉ ዋና ስራ አስኪያጅ ክቡር ዶክተር ፕሮፌሰር ኢንጂነር አቶ ተሰማ መቅደሱ፤ ውድ የቤጊዮሎጂ ሊቀ ሊቃውንት መምህራን፤ ክቡራን እንግዶችና እንዲሁም …(ለተመልካች) … በዚህ አመት ወደ ማዕከላችን የገባችሁው ጀማሪ ተማሪዎች፤ እንኳን ለዚች ለተቀደሰች ቀን አደረሰን፡፡

(ጌታቸው ታረቀኝ፣ 2013፣2)

አልአዛር የተሰማን የትምህርት ደረጃ (ማዕረግ) ሲገልጽ በምጸት ነው፡፡ ምክንያቱም ተሰማ ምንም አይነት ማእረግ የሌለው ሲሆን የሚጠራው ግን በኢንጅነሪግ የዶክትሬት እና የፕሮፌሰርነት ማእረግ እንዳለው ተደርጎ ነው፡፡ ነገር ግን የትምህርት ደረጃ እንደሌለው የሚያመላክት "አቶ ተሰማ መቅደሱ"ተጨማሪ ማእረግ ተጨምሮበት እናገኛለን፡፡ ነገር ግን

በትምህርቱ አለም የተማረሰው የሚጠራበት የማእረግ ስም ካለው “አቶ” በመባል አይጠራም፡፡ በዚህ ተውኔት ውስጥ ግን የተሰማ ማዕረግ “…ክቡር የማዕከሉ ዋና ስራ አስኪያጅ ክቡር ዶክተር ፕሮፌሰር ኢንጂነር አቶ ተሰማ መቅደሱ…” በምጸት መልኩ ለስላቅ ቀርቦ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ ተውኔት ውስጥ ለስላቅ የቀረቡት ሳይማሩ የትምህርት ማዕረግ ተሸክመው ለሚኖሩ ሰዎች ሲሆን ምጸቱም ሳይማሩ ማእረግ ተሸክመው ከሚዞሩ ተምረው የሞራል ጥያቄያቸውን እንዲመልሱ ለማድረግ ነው፡፡ በሌላ በኩል በምጸት መንገድ ልመና ሀውልት ሊያስቆም እንደሚችል ተገልጾ እናያለን፡፡ ለዚህም የሚከተለውን ማስረጃ ማየት ይቻላል፡-

> ተሰማ፡- ግሩም፤ … በተለይይ የሳቸው መንግስት በአለም ላይ የማያባራ ሁከትና ብጥብጥ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ለማድረግ ማቀዱ፤ የሳይንሳችንን ህልዉና ያለጥርጥር በአስተማማኝ መሰረት ላይ ያቆመዋል! …በጣም ደስ የሚል ነገር ነዉ!! …አለማቀፋዊ ማደናገርና ሰርከሱን ላስተዋለዉ እጅግ ደስ የሚል የተቀናጀ ታክቲክ ነዉ!! …ብሪሊያንት!!…ብሪሊያንት!! …ጦርነት ቢጠፋ እንኳ በላቦራቶሪ የተፈበረኩ በሽታዎችን ለማዳረስ የታቀደዉ ብልሃት ለሳይንሳችን ምንኛ ጉልበት እንሚሆነን ትልቅ ማረጋገጫ ነው፡፡ እኛም ተተኪው ትውልድ ይሄንን ድካማችንንና ጥረታችንን ሲመለከት **ሃውልት እንደሚያቆምልን ጥርጥር የለኝም፡፡ አጽንኦት የኔ**
>
> (ጌታቸው ታረቀኝ፣ 2013፣25)

ማበጣበጥ ፣ማደናገር፣በላብራቶሪ የተፈበረኩ በሽታዎችን በህዝቡ ላይ መልቀቅ እና ህዝቡ የተረጋጋ ኑሮ እንዳይኖር ማድረግ ሐውልት ሊያሥቆምላቸው እንደሚችል ተሰማ ይናገራል፡፡ ይህም ምጸት ነው፡፡ በአለም ላይ በየትኛውም ቦታ እኩይ ተግባር የሰራ ሲሸለም ውይም ሐውልት ሲቆምለት ታይቶ አይታወቅም፡፡ ነገር ግን በአለም ላይ ያለው የልመና ስልት ምን ድረስ እንደሆነ ለማስገንዘብ የተገለጸበት ሲሆን ምንአልባት ይህንን ስንፍና ለአለም ህዝብ ያስተዋወቁ እና ያስፋፉ ሰዎች ስማቸው በጥቁር መዝገብ ሊመዘገብ እንደሚገባ የሚያመለክት ነው፡፡ ይህን ድርጊት እያሥፋፉ ያሉ ቡድኖት ከድርጊታቸው እዲቆጠቡ ለማመላከት ተሞክሮበታል፡፡ ነገር ግን የልመና ተግባር ምን ድረስ እንደሆነ ለማስገንዘብ የምጸት ዘዴን በመጠቀም ሲሳለቅ ይስተዋላል፡፡

በተጨማሪ በትምህርት ዘርፉ ላይ እየደረሰ ያለው ሽቀጥነት በምጸት መንገድ ተገልጾ እናገኛለን፡ ፡ ለዚህም የሚከተለውን ምሳሌ ማየት ይቻላል፡፡

"ተሰማ፡- (አልዓዛርን) …የዘንድሮ ተመራቂዎች ስንት ናቸው?

አልዓዛር፡-አሁን ያለት ስድስት መቶ ሰማኒያ አራት ናቸው፤ በርግጥ ሁሉም ይመረቃሉ ብለን እንገምታልን፡፡ ማእከላችን አንድ ጊዜ ክፍያ ከፍሎ የገባን ተማሪ አያባርርም፡፡ ብቃት ባይኖረዉም እንደ ማንም ተመርቆ ዲግሪዉን ስንሰጠዉ የእድሉን ይሞክራል፡"

(ጌታቸው ታደቀኝ፣2013፣27)

አልአዛር የተመራቂ ተማሪዎች ብቃት ሲገልጽ በምጸት ነው፡፡ ምጸቱም ክፍያ እከፈለ የሚማር የግል ተማሪ ክፍያውን እስካላቋረጠ ድረስ መመረቅ እንደሚችል ሲገልጽ እናያለን፡፡ ይህም በትምህርት ስርአቱ የትምህርት አስጣጥ እና የማብቃት ስራ ላይ ሲሳለቅ እናያለን፡፡ በተለይ ትምህርት እንሰጣለን እያሉ በየቦታው የተከፈቱ የግል ተቋማት የሚያመርቱት የሰው ልጅ እንጅ ሸቀጥ እንዳልሆነ ተረድተው ከድርጊታው እንዲቀጠቡ የሚገስጽ ነው፡፡

***በሽልማቱ*** ተውኔት ውስጥ ምጸታዊ ስላቅ ቀርቦ የምናገኝ ሲሆን ምጸቱም ሸላሚው ንግግር ሲያደርግ ሽልማቱ ምን ያህል ተሸላሚዎች በጥንቃቄ እንደተመረጡ እና ከሙስና የጸዳ እንደሆነ የገለጸ ቢሆንም ሽልማቱ ሲከናዎን ግን የስብሰባው ተሳታፊዎች አዘጋጆቹ እርስ በርስ ከመሸላለም ባለፈ ለሌላ ኮከብ ሰራተኛ ሽልማት እንዳልተሰጠ አይተዋል፡፡ ነገር ግን ሰብሳቢው ገና ንግግር ሲያደርግ የሰሩት ስራ የሰራተኛውን አፍ ሊያሲዝ እንደሚችል ሲገልጽ ይስተዋላል፡፡

"…ሳይመረመር…‹‹በዘመድ ነዉ፡ በትዉዉቅ ነዉ፡፡ በጉቦ ነዉ››… ተብሎ ለምን ይወራብናል? …እ?…እ? …ይሁንና ዛሬ ሁሉንም በአደባባይ ለማዉጣትና **ወሬኛዉንም አፉን ለማስያዝ እነሆ ከፊታችሁ ቀርበናል**"፡፡ አጽንኦት የኔ

(ጌታቸው ታረቀኝ2015፣172)

ሰብሳቢው የሰራነው ስራ ከአድሎአዊ አሰራር፣ከትውውቅ እና ከሙስና የጸዳ ነው ቢልም የተሰጠው ሽልማት ግን ከራስ ለራስ መሆኑን እናያለን፡፡ ስለዚህ ወሬኛው አፉን የሚይዝ የተሰጠው ሽልማት ፍትሀዊ ስለሆነ በመደነቅ ሳይሆን ሽልማቱ ጭራሽ አይኑን ያፈጠጠ ምን

ታመጣላችሁ ተብሎ የተዘጋጀ፤ አዘጋጁም፣ ባለስልጣኑም፣ የኮሚቴ አባሉም ሆነ ተሸላሚው አካል ተመሳሳይ ሰዎች መሆናቸውን ለማሳየት የቀረበ ምጸታዊ የአቀራረብ ዘዴ ነው፡፡ ለስላቅ የቀረቡ የመንግስት ባለስልጣናት ሲሆኑ ምጸቱም የማበረታቻ ስርአቱ ላልሰራ ሳይሆን ለሰራ እንዲሆን ለመጠቆም ነው፡፡

### 3.1.4 አለመመጣጠን

አለመመጣጠን ብዙውን ጊዜ ወለፈንዲያዊ የስላቅ ዘዴ ሲሆን ያልተጠበቀ ነገር ወደ ሌላ የተለመደ ትዕይንት ወይም ታሪክ የሚያቀርብበት ዘዴ እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ***በሳጥናኤል አበሳ*** ተውኔት ውስጥ ያልተለመዱ ጉዳዮች ሲቀርቡ እናያለን፡፡ ተውኔቱ ከተለመደው የሰው ልጅ እንቅስቃሴ ወደ ያልተለመደው የሰማይ ቤት ሲኦል ወስዶ የተኮናኘን ነፍስ መግቢያ በሶሻሊስት እና ካፒታሊስት ሪዮተ ዓለም አስተሳሰብን ለተኮነነች ነፍስ የመግቢያ አማራጭ ሆኖ ሲቀርብ እናያለን፡፡ ይህ አቀራረብ ኮርንዌል (2013) እንደሚለው "የተከለከሉ ርእሰ ጉዳዮችን፣ ወሲባዊ ጉዳዮችን እና የሞት ጭብጦችን ለማንሳት ወለፈንዲን መጠቀም እንደሚስተዋል" ሲገልጽ ይስተዋላል፡፡ በሳጥናኤል አበሳም ተውኔት ውስጥ የታየው ለማሰብ የማንፈልገውን ጉዳይ ሳቅን እያጫረ ሲያቀርብ ይስተዋላል፡፡ ለዚህም እንደ ምሳሌ ከተውኔቱ የሚከተለውን ለማሳያነት ማየት እንችላለን፡፡

> ነፍስ አባት፡- **መንግስተ ሰማያት ቦታ ስለ ሌለ… ያዉ ሌላ ቦታ ይሄዳል** ነዉ የሚለት…
>
> እናት፡- **የት ነዉ ሌላ ቦታ ማለት?**…ወይኔ..
>
> ለቀስተኞች፡- ተረረረም ረረም ..ወይኔ ተረረረም ተረረም ..ወይኔ ተረረም ተረም… (ያሸበሽባሉ).. **ገሀነበሳት …በጣም ብዙ እሳት…** እንዴት ብሎ ሊኖራት …ገሀነበሳት..ገሀነበእሳት በጣም ብዙ እሳት…..
>
> አበራ፡- ሌት ተቀን ዝንተዓለም የማይጠፋ ንዳድ…ትልቅ የገሞራ ጉድጓድ፡፡
>
> እናት፡- እኮ በምን አቅሙ ችሎት?...እንኩዋን የገሀነበሳት…እዚህ አፋር ደብቲ ለስራ ሂድ ቢሉት፤ ሙቀቱ አቅቶት ተመልሶ የለ እርግፍ አድርጎት…አዬ ለፍቶ መና…

ለቀስተኞች፡-ገሀነበሳት የእሳት እራት… እሱ እንደሁ እርግማን የለበት…ሁሉም
እያለዉ ድክመት…የምን ገሀነበሳት…አባባ አባክዎ ይርዱት..

ነፍስ አባት፡-እኔማ ሞከርኩኝ.. ፊርማ አስፈረምኩኝ፤ ማተም አስደረግኩኝ …ከመዝገብ ቤት እሰወጣሁኝ ..ኮፒ አስገባሁኝ …ፎቶዉን አያያዝኩኝ… እንዴት ግን ቦታ ይሞላል?…(አጽንኦት የኔ)

(ጌታቸው ታረቀኝ፣2007፣7)

በዚህ ተውኔት ውስጥ የነፍስ አባት ወደ ሰማይ ቤት ደውለው ሟች ቦታ እንዲሰጠው ሲጠይቁ መንግስተ ሰማያት መሙላቱ ሲገለጽላቸው አንደኛው ለቤተሰቦቻቸው ገሀነም እሳት እንደሚገባ ለመናገር ሲጨነቁ እና የሰሙትን ነገር ማመን አቅቷቸው በተለያየ ስልክ ጉዳዩን ለማጣራት ሲጥሩ እናያለን፡፡ ይህ ነገር መስማት ለሰው ልጅ ከባድ ዜና ነው፡፡ ምክንያቱም የሰው ልጅ በምድር ሲኖር ጥሩ አደረገም መጥፎ ሰራም የንስሀ አባት ንስሀ ከተቀበለ እና ቅኖና ሰጥቶት ከሞተ በክርስትና እምነት ተከታዮች (በኦርቶዶክስ ተዋህዶ) ዘንድ ጽድቅ እንደሚገኝ ይታመናል፡፡ የነፍስ አባትም የተጨነቁት ለሟች ከመሞቱ በፊት ንስሀ መቀበላቸውን እና በጸሎት አምላክን ይቅር ይለው ዘንድ ስለለመኑ መንግስተ ሰማይ እንደሚገባ እርግጠኛ ስለነበሩ ሲደነግጡ እናያለን፡፡ ምክንያቱም ሟች መንግስተ ሰማያት ካልገባ የት ሊገባ እንደሚችል ስለሚያውቁ ነው፡፡ አበራም የገሀነም እሳቱን አሰቃቂነት አስፈሪነት እና የሚያስጨንቅ መሆኑን ሲገልጽ ለቀስተኞቹ የነፍስ አባት ጭንቀት እና መረበሽ ተከትለው በማሽብሽብ የሙዚቃ መሳሪያ ድምጽ በማሰማት በሲኦል ያለውን የእሳት መጠን ሲገልጹ ይስተዋላል፡፡ ይህም በድርጊቱ እና በክስተቱ መካከል አለመመጣጠን መኖሩን ያሳየናል፡፡ ምክንያቱም የለቀስተኞቹ ድርጊት ከሰሙት ነገር ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም ለቀስተኞቹ የሲኦልን እሳት በሙዚቃዊ ቃና በማሽብሽብ ሲገልጹት የነፍስ አባት፣እናት እና አበራ በድንጋጤ ይገልጹታል ይህም አለመመጣጠኑን የሚያሳይ ሲሆን ሁነቱ ወለፈዲ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው በአንድ ትዕይንት ውስጥ ያሉ ገፀ-ባህሪያት ያልተለመዱ ድርጊቶች የተለመደ በሚመስሉ ሆኔታዎች ሲቀርቡ አለመመጣጠን ሲሆን ድርጊቱ ግን ወለፈንዲያዊ ስላቅን እንደሚያሳይ እንረዳለን፡፡ በዚህም አስመሳይ የሀይማኖቱን ተከታዮች ከአስመሳይነታቸው የማይቆጠቡ ከሆነ መዳረሻቸው የት እንደሆነ ለማስተማር የቀረበበት መንገድ ነው፡፡

ሌላው ማሳያ ደግሞ የነፍስ አባት ሟች የሚገባበት ቦታ ሲኦል መሆኑ ከተነገራቸው በኂላ ሲኦል ሁለት አማራጭ እንዳለው ሲገለጽላቸው እናያለን ይኸውም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ካፒታሊዝም እና ሶሻሊዝም እንደሆነ ይነገራሉ። ከሁለቱ አንዱን እዲመርጡ ይነገራሉ። እዚህ ላይም የምናየው አለመመጣጠንን ነው ። ምክንያቱም የሞተን እሬሳ ከፊት አስቀምጦ መንግስተ ሰማያይ ይገባል የተባለው ነፍስ መግቢያ አጥቶ አማራጩ ገሀነም እሳት ሆኖ ከገሀነም እሳት ውስጥ አማራጭ ቀርቦለት የተሻለውን ለመምረጥ ጭቅጭቅ ውስጥ ሲገባ እናስተውላለን። ጭቅጭቁም ፖለቲካዊ ትርጉም ተሰጥቶት ካፒታሊዝም ከገባ የዘይት እና የቅቤ እጥረት ስለማያጋጥም ሌትም ቀንም በዘይት እና በቅቤ እየታሹ መቃጠል ሊኖር እንደሚችል አንደኛው ቡድን ሲገልጽ፤ ሁለተኛው ቡድን ደግሞ ሶሻሊዝም ከገባ የዘይት እና የቅቤ እጥረት ስለሚኖር ዘይት እና ቅቤ እስኪገኝ እረፍት ሊኖር እንደሚችል የማሳመኛ መከራከሪያ በማቅረብ ሲከራከሩ እናያለን። ይህም ያልተለመደ ነገር ግን በምናውቀው የአለም ኑሮ ውስጥ የምናየውን ጭቅጭቅ በሞተ ሰው አስከሬን ፊት ቆሞ የሚደረግን ሙግት እናያለን።

> ነፍስ አባት፡- ለኛማ ሁለቱም አንድ ነዉ …ያዉ ሲኦል መቃጠል ነዉ …በዘይት በቅቤ ሰዉነትን እያሹ ..ሲጠብሷቸዉ ነዉ የሚዉሉት…ወየዉ ቢለም በድጋሚ በቅቤ በዘይት እየነከሩ እንደገና መልሰዉ ከእሳቱ ነዉ…መከራ ነዉ…ሳጥናኤል እግራቸዉን እንዲህ ይዞ እንደ አሻንጉሊት እንደ መጫወቻ ሲያሽከረክራቸዉ ነዉ የሚውለዉ…

> አበራ፡- ይልቅ…አሁን ሳስበዉ ከካፒታሊስቱ ሲኦል የሶሻሊስቱ ሲኦል ቢገባ ይሻለዋል…

> እናትየዉ፡- እሀሀሀ…ልጄን ሳጥናኤል…በዘይትና በቅቤ እየነከረ ወደ እሳቱ….እሀሀሀ..

> አበራ፡- እንዴት መሰለዎት ማዘር…በርግጥ እንደሰማነዉ…እንደሱ ነዉ ሳጥናኤል የሚያደርጋቸዉ..ግን ምን መሰለዎት…ከሶሻሊስቱ ገሀነብ ከገባ…በቂ ዘይትና ቅቤ ስለማይኖር…ገና ተለምኖ እስከሚመጣ..ልጅዎ በሰላም ትንሽ ጊዜ ያገኛል..አስቡት እረፍት ይኖረዋል…( አጽንኦት የኔ)

(ጌታቸው ታረቀኝ፤2007፤10-11)

በዚህም ተውኔት ውስጥ የምናየው በተስፋ አስቆራጭ መልስ ውስጥ ተስፋ ለማግኘት የሚደገግ የህይወት ግብ ግብን ነው፡፡ አበራ ከካፒታሊስቱ ይልቅ ሶሻሊስቱ ሲኦል ይሻላል ብሎ አማራጭ ሲያመጣ የኑሮ ውድነትን ፣የሰው ልጅ ገዝቶ የመጠቀምን አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደ ማሳመኛ ሲያቀርብ፤ ለቀስተኞቹ ደግሞ ተቀምጦ ከመዋል ከካፒታሊስቶች ጋር በመሆን ሲሰሩ እና ሲዝናኑ መዋልን እንደ መከራከሪያ ሃሳብ አንስተው ሲሞግቱ እናያለን ፡፡ በዚህ በሁለቱ ክርክር መካከል የሚች እናት ልቅሶ እና ሀዘን እናያለን ይህ የሚያሳየው በድርጊቶች እና ሁነቱ መካከል ያለውን አለመመጣጠን ሲሆን አለመመጣጠኑም ከከባድ የኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ የተሻለውን ከባድ ለመፈለግ የሚደረግ ጥረት ነው፡፡ የሰውን ልጅ ያህል ክቡር ፍጡር ሞት መቀበል ከባድ ሸክም ሆኖ ሳለ የሞት ሞቱ ደግሞ ገሀነመ እሳት አማራጭ የሌለው ምርጫ ሆኖ መቅረቡ ወለፈንዲያዊ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ስላቁ በዚህ መንገድ የቀረበው ማን አለብኝ ብለው በምድር ላይ ክፍት እና ተንኮል የሚሰሩ ሰዎች ሊሞቱ እንደሚችሉ ለማመልከት ሲሆን ሲሞቱ መግቢያቸው ገሀነመ እሳት እንደሆነ ለማመልከት ነው፡፡ በተጨማሪም በእነሱ ሞት የሚደሰቱ ሰዎች መኖራቸውን ለማመላከት የለቀስተኞቹ ድርጊት ለማሳያነት ቀርቦ እናገኘዋለን፡፡

በሌላ በኩል ሚች ወደ ሲኦል ከሄደ እና ከሳጥናኤል ጋር ከተገናኘ በኋላ በሲኦል ውስጥ እነማን እነማን እንዳሉ ሲያስተዋወቀው የሳጥናኤል አበሳ ጸሀፌ ተውኔት እና በምን አይነት ስራ መስክ የተሰማሩ ሰዎች በሲኦል ውስጥ እንደሚገኙ ይነግረዋል፡፡

ሳጥናኤል፡- አቶ ደምሱማ ልትሆን አትችልም…

ሬሳ፡- ኧረ ነኝ…ሁለም ሰዉ አቶ ደምሱ ነዉ…. ማለቴ ነበር ብል የሚጠራኝ..

ሳጥናኤል፡- **ስነግርህ…አቶ ደምሱ ልትሆን አትችልም…አቶ የሚል ማእረግ ያላቸዉ ሙታን እዚህ አይመጡም…ድክተሮች ፕሮፌሰሮች ደላሎች ጠበቆች ኪስ አዉላቂዎች፤ቤት ሰርሳሪ ማጅራት መቺዎች** ….መውለቅ የሌለበትን ጥርስ ያውለቁ የጥርስ ሐኪሞች …የማያስፈልግ መድኃኒት የሚያዙ ዶክተሮች…ቁስለን ከማዳን እግሩን ቢቆርጡት ትርፍ ይገኛል እያሉ ብዙ እጅና እግር የቆረጡ ሰርጀኖች…ለድሀ ብለዉ እርዳታ ከሰበሰቡ

በሁዋላ በገንዘቡ ደህዉን እንደመርዳት ለራሳቸዉ ፎቅ ቤት የሰሩ…የምታያቸዉ በሞላ የተማሩ አጭበርባሪዎች ናቸዉ …አዉቀዉትም ሳያዉቁትም…. ግዴለም ላሁኑ ላይገባህ ይችላል… (ለተመልካች) …ጎበዝ…‹‹ደምሱ ሸወደዉ በጢሱ››.. ብንለዉስ?….አንተን ቅር ይልሃል?

ሬሳ፡- አይ..ኧረ ምንም አይደል…

ሳጥናኤል፡-ግሩም እንግዲያዉ …አሁን ሂዴና ተቀመጥ፤ አይዞህ…እዛ ጋ…ጌታቸዉ ታረቀኝም…ያዉልህ…ኪስ አዉላቂዎቹ መደዳ፤ (አጽንኦት የኔ)

(ጌታቸው ታረቀኝ፣2007፣17)

ሳጥናኤል በሲኦል ውስጥ አጭበርባሪ የተማሩ ሰዎች፣ ያለ አግባብ የሰው ገንዘብ የሚወስዱ ሰዎች፣እንዲሁም ደላሎች ናቸው ገሀነም ውስጥ ያሉት ሲለን አቶ የሚል ማእረግ ያላቸውን ሰዎች ግን ገሀነም እንደማይኖሩ ይገላጻል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን የሳጥናኤል አበሳ ጻሀፌ ተውኔት ጌታቸው ታረቀኝ ከኪስ አውላቂዎች ጋር ገሀነም ውስጥ እንደሚገኝ በህይወት ያለን ሰው ለመሳለቂያነት ሲያቀርብ እናያለን፡፡

በተጨማሪም ታዋቂ የኪነጥበብ ባለሙያዎች በሲኦል ውስጥ እንዳሉ እና ሲኦል ውስጥ ባሳዩት መልካም በሀሪ ከሶሻሊስቱ ገሀነም እሳት ወደ ካፒታሊስቱ ገሀነም እሳት እንደተሸጋገሩ፤ እዝያም ዋና ተግባራቸው የተኮነነን ነፍስ በዘይት እና በቅቤ እያሹ የሚያቀብሉ ናቸው ተብሎ ሲገለጽ መስማት አስደንጋጭ ነው፡፡ በተለይ የእነሱን የጥበብ ውጤት የሚያውቅ ታዳሚ እና አንባቢ ሲሰማ የገሀነመ እሳት አስከፊነት እና አስፈሪነት  ያስጨንቃል፡፡

ሁላችሁም ምናልባት አንድ ቀን መንግስቱ ለማን እዚህ ታገኙት ይሆናል…ምድቡ እዚህ ከሶሻሊስቱ ሲሆን በመልካም ጠባዩ የተነሳ በካፒታሊስቱ ገሀነመ እሳት ስራ አግኝተንለት እዛዉ ነዉ የሚውለዉ…አሁን ቀኑን ሙሉ ዮኂንስ አድማሱ ከተባለ ጉዋደኛዉ ጋር እነኚህ አዳዲሶች፡ የጋዜጣዉን ርእሰ-አንቀፅ በግጥም የሚጥፉ የዘመኑ ‹‹ባለቅኔዎች›› ሲመጡ በቅቤና ዘይት እያሹ ያቀብሉናል…

(ጌታቸው ታረቀኝ፣2007፣19)

ከላይ የቀረበውን ሃሳብ ስናይ በቅቤ እና በዘይት እያሹ ለሳጥናኤል ገሀነመ እሳት የሚያቀብሉ መንግስቱ ለማ እና ዮናስ አድማሱ ሲሆኑ እየታሹ የሚቀርቡት ደግሞ ባለቅኔዎቹ ናቸው። ባለቅኔዎቹ እነማን ናቸው ስንል ጋዜጠኞችን ነው። ለህዝብ መረጃ የሚያደርሱ፣ ብልሹ አሰራር እንዲወገድ በማስረጃ የሚያቀርቡ፣ አንዳንዶች ደግሞ የህዝብ ለቅሶ የማይሰማቸው የመንግስት እስትንፋስ የሆኑ ጋዜጠኖችን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። ጋዜጠኞች ከእውነት ጎንም ይቁሙ ከሀሰት ጎን በዚህ ደረጃ ገሀነመ እሳት ውስጥ ነው የሚገቡት ብሎ ማሰብ ለተመልካች ከባድ መርዶ ነው። በዚህ መልኩ የጋዜጠኞች ህይወት በሲኦል ውስጥ መገኘታቸው የጋዜጠኞች ህይዎት በመንግስት ብልሹ አሰራር ምክንያት ችግር ውስጥ መሆናቸውን ለመግለጽ የተሞከረበት ነው። ለህዝብ ትክክለኛውን መረጃ የሚያደርሱ ጋዜጠኖች ግማሹ የህይዎት ዘመናቸው በእስር ቤት ውስጥ መማቀቅ መሆኑን ለማመልከት ሲኦልን እንደ መሳለቂያ ሲጠቀምበት እናያለን።

***በቤገዮሎጂ*** ተውኔት ውስጥ የአሊጋዝ እና የተሰማ ንግግር በተውኔቱ ውስጥ አለመመጣጠን እንዳለ ያሳየናል። በዚህም ተውኔት ውስጥ የምናየው ከፈጣሪ እና ከስራው ጋር ፍጥጫ ተገብቶ እናያለን። የሰውልጅ አምላክ የፈጠረው ከሁሉም እንስሳ የተራረፈውን ሰብስቦ መጣያ ሲያጣ ሰውን ፈጠረ ስለዚህ የሰው ልጅ የተከበረ አይደለም በሚል ከአሊጋዝ ጋር ሲከራከር እናያለን። ይህም በተውኔቱ ውስጥ አለመመጣጠንን በስላቅ ዘዴነት ጥቅም ላይ እንደዋለ እናስተውላለን።

> አሊጋዝ፡- እንግዲያ ታስረን ልንቀር ነዋ! …መቼም ወገኖቼ፤ ይሄ እርስ በእርስ በሚደረገዉ መናቆር ክቡር የሰው ልጅ ህይወት እንደዋዛ ሊጠፋና፤ …ፈጣሪ በራሱ አምሳል የፈጠረዉን ክቡር የሰዉ ፍጡር…
>
> ተሰማ፡- አባቴ የምን መዘብዘብ ነው …ፈጣሪ በአምሳሉ የፈጠረዉ ታላቅ ክቡር የሰዉ ልጅ ምናምን…ፈጣሪ የሰዉን ልጅ የመጨረሻ ቀን ላይ ከደከመው በኋላ የፈጠረው ነገር ነው። ሁሉን ፈጥሮ ፈጥሮ…በጉን ውሻውን ጅቡን ከፈጠረ በኋላ …ከሁሉም የተራረፈውን ሰብስቦ ከምጥለዉ ብሎ የፈጠረዉ ነገር ነው።

(ጌታቸው ታረቀኝ ፣2013፣33)

በቅዱሳን መጽሀፍት አስተምሮ የምናውቀውን የፈጣሪን ስራ ለስላቅ አላማ ቀርቦ እናገኛለን። የቀረበበት ዘዴም አለመመጣጠንን የተጠቀመ ሲሆን የሰው ልጅ አፈጣጠር እና ክብር ከውሻ እና ከጅብ ያነሰ መሆኑን ሲገለጽ እናያለን። ይህም የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ክቡር አላማ ተነጥሎ ኢሰብአዊ ድርጊት እየፈጸመ መሆኑን እና የሰው ልጅ ህሌና ቢስ እየሆነ መምጣቱን ለመግለጽ የተሞከረበት ነው። ለመገሰጽ የተፈለገውም እኔ ብቻ ልኑር ፤ ከኔውጭ ያለው ሰው ገደል ቢገባ አያገባኝም ለሚሉ በየደረጃው ላሉ ባለስልጣናት፣ ደላሎች እና ባለሀብቶችን ለመገሰጽ የተሞከረበት ነው።

ሌላው በተውኔቱ ውስጥ የምናገኘው አለመመጣጠን ለልመና የተመለመሉ ተማሪዎች ለልመና የሚጠቀሙበት ማህበራዊ ችግር ነው። የሴቶች ኪነት 1 ላይ የቀረበው ታሪክ የሰው ልጅ በህይዎቱ እንዲደርስበት ብቻ ሳይሆን እንዲሰማው የማይፈልገውን የትዳር አጋር ሞት እና እናት እንዲደርስባት ቀርቶ መስማት የማትፈልገው የልጅ ሞት ለልመና ስልት ሲባል የቀረበው ታሪክ ነው። ይህን ታሪክ መስማት አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን አስደንጋጭ ነው። ነገር ግን ለልመና ማሳመኛ ሲባል የተፈጠረ ታሪክ ሆኖ እናገኘዋለን። ለማሳያ የሚከተለውን ከተውኔቱ የተወሰደ ጽሁፍ መመልከት እንችላለን።

> ሴቶች ኪነት 1 ፡- የልጅነት ባሌ ገና ከጫጉላ ሳንወጣ በልብ ድካም ሲሞትብኝ፤ ሰዉ ሁሉ ‹አንቺ ገፊ ምናምን› ብለዉኝ በሰፈሩ መቆሚያ መቀመጫ ቢያሳጡኝ በጋሪ ተሳፍሬ ልብሴን እንኳ ሳልይዝ በሌሊት ዉልቅ አልኩላቸዉ። እኔማ ያመለጥኩ መስሎኝ ነበር ግና በዘጠኝ ወሬ ያላሰብኩት ልጅ ተወለደ። እሱም እንደ አባቱ አርጅቶ ተወልዶ ነዉ መሰል፤ በሁለት ወሩ በልብ ድካም ሞተ። እሰቲ አሁን ምን ልብ ኖሮት ነዉ የሚደክመዉ? …አባቱስ ይሁን ልጁም እንዳባቱ? መከራ ገባሁላችሁ። እኔም ያለ እድሜዬ አረጀሁ …ብሞት እንኳ ቀባሪ የለኝም። እናም የእናንተን እርዳታ ካላገኘሁኝ የኔም ልብ መፍረጧ ነዉ። መረዳዳት ደግ ነዉ። ዝም አትበሉ ‹‹ገና ልጅ ነሽ ሌላ ባል አግብተሽ ተቀመጪ›› የሚሉኝ ብዙ ሰዎች አሉ ….ግና እንደገና ቢሞትብኝስ? ቀድሞስ ማን ያገባኛል? አንድ ጊዜ ‹ገፊ› ተብዬ እጄን እንኳ የሚጨብጠዉ የለም።

(ጌታቸው ታረቀኝ፤2013፣7-8)

ባለታሪኳ ይህንን ታሪክ የፈጠረችው ለልመና ስልት መሆኑ የተፈጠረው ስነልቦናዊ ጫና እና ታሪኩ የተፈጠረለት አላማ ወለፈንዲያዊ አለመመጣጠን እንደተንጸባረቀበት መረዳት ይቻላል፡፡ ወለፈንዲነቱ የተነሳው ጭብጥ ሲደርስብን ቀርቶ ልንሰማው የማንፈልገው የህይዎታችን አንዱ ክፍል የተነሳ መሆኑ ሲሆን አለመመጣጠኑ ደግሞ ታሪኩ የተፈጠረበት አላማ የተፈጠረው ታሪክ ከሚፈጥረው ስነልቦናዊ ጫና አንጻር ነው፡፡ በተጨማሪም "ባል አግቢ ይሉኛል" ፣"ግን እኔን ማን ያገባኛል?"እና "ገፊ" ናት እያሉ ይርቁኛል፡፡ የሚሉት የስቆቃ የልመና ስልቶች የሰው ልጅ ያለውን ቀርቶ የሌለውን እንዲሰጥ የሚያደርጉ አሳዛኝ ቃላት እና ሀረጋት ሲሆኑ ለሚያዳምጠው አካል ግን በራሱ ላይ እንዲደርስ የማይፈልገው ጉዳይ ነው፡፡ ስላቁ በዚህ መንገድ የቀረበበት ምክንያት ለልመና ሲባል በየመንገዱ ዳር የሚፈጠሩ አሳዛኝ ታሪኮችን ለመተቸት እና ለመገሰጽ ያለመ ሲሆን የዚህ ስላቅ ተተኳሪዎችም በማስመሰል ለልመና የተሰማሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ታላሚ ያደረገ ነው፡፡

## 3.2 የይዘት ትንተና

በሳጥናኤል አበሳ (2007) *፣በቢጊዮሎጅ(2013)* እና ሽልማቱ ተውኔቶች ውስጥ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ይዘት ያላቸው ስላቆች በስፋት ቀርበው እናገኛለን፡፡

### 3.1.1 ፖለቲካዊ ስላቅ

*በሳጥናኤል አበሳ ፣በቤጊዎሎጅ እና ሽልማቱ* ተውኔት ውስጥ በስልጣን ላይ ያሉ ቡድኖችን እና ግለሰቦችን ኢላማ በማድረግ ስላቆች ተንጸባርቀው እናገኛቸዋለን፡፡

***በሳጥናኤል አበሳ*** ተውኔት ውስጥ ፖለቲከኞች ስላቅ ሲደረግባቸው እናያለን፡፡ የፖለቲካ አስተሳሰብ ሶሻሊስቱን ስራፈት ሲያደርገው ካፒታሊስቱን ደግሞ በሙስና እንዲዘፈቅ እንዳደረገው በተውኔቱ ሲቀርብ እናያለን፡፡ በተጨማሪም ካፒታሊስቱ የምርት መትረፍረፍ ሲያጋጥመው ሶሻሊስቱ የምርት እጥረት በመኖሩ መሰረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎት አለመሟላቱን በስላቅ መንገድ ቀርቦ እናገኘዋለን፡፡

ነፍስ አባት፡-መቼም ጠልቄ ባላዉቀዉም …እንደኔ እንደኔ ከሶሻኒስቱ ይሻለዋል ካፒታሊስቱ

አበራ፡- እንደ እኔ ከሆነ ደሞ…የሶሻሊስቱ ይሻለዋል

ለቀስተኞች፡-(ለሁለት ተከፍለዉ ይጨቃጨቃሉ) ምነዉ ምን በወጣዉ…ከነማርክስ ከሌኒን ጋር የሚቀመጠዉ…እስኪደክመዉ የሚሰራዉ…ካፒታሊስቱ ይሻለዋል… ከክሊንተን ከኤልቢስ፣ ማይክል ጃክሰን ጋር ሆኖ ፌስ ቡክ ይከፍታል ዳንስ ፋሽን ያምርበታል…

እናቱ፡- አዬ…ሲኦልማ ያዉ መንደድ መቃጠል እንጂ…ዘፈን ማን ይከፍትለታል?…

ለቀስተኞች፡-ለምን ብሎ… ምን በወጣዉ ነዉ ከካፒታሊስቱ የሚቀመጠዉ …ሁሉም ነገር በሽታ ነዉ..ፌስ ቡክ ቢከፍት ቀኑን ሙሉ ቢያወራ የተራ ሽቀጥ መሞከሪያ ነዉ የሚሆነዉ…አንዱ ሌላዉን የሚያጠምድበት… ክብር የሌለዉ ዉሻ ነዉ የሚሆነዉ…

(ጌታቸው ታደቀኝ፣2007፣9)

ፖለቲከኞች በሚያመጡት ፖለቲካዊ አስተሳሰብ የመጀመሪያው ተጎጅዎች ህዝቡ መሆኑን ለማስረዳት የሦሻሊዝምን እና የካፒታሊዝምን አስተሳሰብ ወደ ሲኦል ወስዶ መሳለቂያ ያደረገው ሲሆን፤ መሳለቂያነቱም ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረገ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የፖለቲከኞች ለህዝብ የሚጠቅም ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ካላመጡ የመጀመሪያው ተጎጅ ህዝብ እንደሆነ የተገለጸበት ስልት ሲሆን ለስላቅ የቀረቡትም ፖለቲከኞች እና የፖለቲከኞችን አስተሳሰብ ተሸክመው የሚያራምዱ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ ማስተካከል የተፈለገውም አንድ ሪዮተ አለም እንደ አስተሳሰብ ሲወሰድ መጀመሪያ ጠቀሜታው በአግባቡ ከታየ እና የሚጠቀመውስ የማህበረሰብ ክፍል የትኛውን ነው ተብሎ በአግባቡ ተጠንቶ መሆን እንዳለበት ለማሳየት ነው፡፡

በሳጥናኤል አበሳ ተውኔት ውስጥ ባለስልጣናትም የስላቁ አካል ተደርገው እናገኛቸዋለን፡፡ ለምሳሌ የሚከተለውን እንይ፡-

በል ወዳጄ ፖለቲካ ልታናግረኝ ነዉ አንተ?...ይልቅ እዛ መሀል ያሉትን ትልቁን ሰዉዬ ታያቸዋለህ?…ነጭ ሸሚዝ?...እሳቸዉ ሁጎ ቻቬዝ ይባላሉ፡፡ ቬንዝዌላ የሚባል አገር ፕሬዜዳንት የነበሩ ናቸው፡፡ እሳቸዉም ትልቅ ስህተት ስለሰሩ ሁሌጊዜም አዲስ ከመጣዉ ጋር እየተቀመጡ እኔን በደምብ እንዲመለከቱ የተፈረደባቸዉ ናቸዉ::: ለምን መሰለህ?..የተባበሩት መንግስታት የሚባለዉ የስብሰባ ቦታ ላይ ንግግር ሲያሰሙ…ጆርጅ ቡሽ የሚባለዉን ሰዉዬ ‹ሰይጣን› ነዉ ብለዉ...ባልዋልኩበት ቦታ ከማላዉቀዉ ሰዉ ጋር እኔን ስላመሳሰለኝ…ሌላ ጊዜ እድሉን ካገኙት እኔን በደምብ እንዲለዩኝ እና የተባበሩት መንግስታት ከሚባለዉም የስብሰባ ቦታ እኔ ራሴ መሄድ እንደምፈራ እንዲያዉቁት ተብሎ ነዉ እዚህ እንዲውል የተፈረደባቸዉ፡፡ እንደምታያቸዉ መሳቅ እንኳ አይችለም፡፡

(ጌታቸው ታረቀኝ፣17፣2007)

ሳጥናኤል የተባለው ገጸባህሪ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ጉዳይ እያወራ ፖለቲካ እንዳታናግረኝ ማለቱ ስላቅ ሲሆን በተውኔቱ ውስጥ በአለም ላይ ያለውን የፖለቲካ አመራሮች ሴራ እና ክፋት እንዲሁም የበቀል እርምጃ ምን እንደሚመስል ተንጸባርቆ እናገኛለን፡፡ ይኸውም የተባበሩት መንግስታት የሚሰሩት ፖለቲካዊ ሴራ ሳጥናኤል እራሱ ሊያስበው በማይችል መንገድ እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን ለምን ተነካሁ፣ የሚሉ የፖለቲካ አካላት ላይ ምን አይነት በደል እንደሚፈጸሙ እናያለን፡፡ ሳጥናኤል ለምን ስሜ ተጠራ በሚል ስበብ የቬንዚዊላውን ፕሬዘዳት የሚቀጣበት መንገድ የፖለቲካ ሹማምንቶች ለምን ከኔ የተለየ ሀሳብ ኖረህ በሚል ሰበብ በህዝቡ ላይ የሚያደርሱትን ስቃይ ለማንጸባረቅ ሲሞክር እናየዋለን፡፡ በዚህም በስልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ለምን ጥፋቴ ተነገረኝ በሚል ሰበብ ህዝብን ከማሳቀየት እና የሚያደርሱትን ኢ-ሰብአዊ ድርጊት እንዲያቆሙ የተተቸበት ነው፡፡

ሁላችሁም ምናልባት አንድ ቀን መንግስቱ ለማን እዚህ ታገኙት ይሆናል…ምድቡ እዚህ ከሶሻሊስቱ ሲሆን በመልካም ጠባዩ የተነሳ በካፒታሊስቱ ገሀነመእሳት ስራ አግኝተንለት እዛዉ ነዉ የሚውለዉ…አሁን ቀኑን ሙሉ ዮጊንስ አድማሱ ከተባለ ጉዋደኛዉ ጋር እነኚህ አዳዲሶች፡ የጋዜጣዉን ርእሰ-አንቀፅ በግጥም የሚጥፉ የዘመኑ ‹‹ባለቅኔዎች›› ሲመጡ በቅቤና ዘይት እያሹ ያቀብሉናል…

(ጌታቸው ታረቀኝ፣2007፣19)

የጥበብ ሰዎች እና ጋዜጠኞች በሚጽፉት  ድርሰታቸው እና መጣጥፎች ለመንግስት ስለማይመች እና የመንግስትን እኩይ ተግባር ለህዝብ ስለሚያጋልጡ ለመንግስት አይመቹም፡፡ መንግስቱ ለማ ከቆሎ ተማሪነት ተነስቶ የለንደን ስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ ደቀመዝሙርነት እስከ መሆን በቅቶ የቅኔ ቤት ሊቅነት ሳይበቃው የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ቀደምቶች መሃከል ለመደብለቅ የበቃ ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ድንቅ ገጣምያን/ፀሃፌ ተውኔቶች አንዱ ነው፡፡ መንግስቱ ፖለቲካ ላይ ስምምነት አልነበረውምና በብዙ ተንገላቷል፡፡ ዲሞክራሲያዊ አመለካከቱ፣ በራስ የመተማመን ልዕልናውና ፍጹማዊነቱ በእጅጉ ዋጋ እንዳስከፈለው ይነገራል፡፡ በዚህም ተውኔት መንግስቱን ስራው ምን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለው ለመግለጽ  ሲባል በስላቅ መልኩ የፖለቲካው ምህዳር ምን ያህል ፈታኝ እንደሆነ ለመግለጽ የታሰበበት ሲሆን ጋዜጠኞችም ቢሆኑ ያዩትን፣ የሰሙትን እና መስተካከል ያለበትን ጉዳይ ለህዝብ ሲያቀርቡ መንግስት የሚያደርስባቸው ስቃይ ከገሀነም እሳት ስቃይ የማይተናነስ ስቆቃ እንደሆነ ለመግለጽ የተሞከረበትን ሁኔታ እናያለን፡፡ ዮሐንስ አድማሱ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ ታላቅ አስተዋጽኦ ያበረከተ ገጣሚ እና ሃያሲ እንደነበረ የማይካድ ሀቅ ነው፡፡ በ1955 የሶስተኛ ዓመት ተማሪ እያለ “እስኪ ተጠየቁ” የሚለውን ረጅም ግጥሙን አቅርቦ የቀዳማዊ ኀይለሥላሴን ሥርዓት በመውቀሱ ከዩኒቨርስቲ ለመባረር  እንደበቃ ይነገራል፡፡ ስለዚህ የዮሐንስ አድማሱ ለመንግስት አካላት የማይመች እና ፖለቲካዊ ይዘት የነበረው ስራ እንደነበር እንረዳለን፡፡ ስለዚህ በዚህ ተውኔት ውስጥ በስላቅ መልኩ ገሀነመ እሳት ድረስ ገብተው የምናገኛቸው ሀያሲያን፣ ደራሲያን እና ጋዜጠኖች በነጻነት እንዲጽፉ መንግስት ያልፈቀዳላቸው  ሰዎች ናቸው፡፡ አሁንም ድረስ መንግስት በጸሀፍት እና በጦማሮች ላይ እያደረሰ ያለውን ስቆቃ እና አፈና እንዲያቆም የተተቸበት ነው፡፡

***ቤገዮሎጅ*** ተውኔት ውስጥም ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ስላቆች የቀረቡ ሲሆን ኸውም መንግስት በእርዳታ ስም በተለያዩ ሀገራት ዘመናዊ ልመናን እያስፋፋ መሆኑ እና ለጋሽ ድርጅቶች የሚሰጡት ማንኛውም እርዳታ ለህዝብ እንደማይደርስ ተንጸባርቆ እናገኛለን ፡፡ መንግስት በተለያየ ምክንያት የሚያመጣው እርዳታ የመጀመሪያዎች ተጠቃሚ በስልጣን ላይ ያሉ አካላት እንደሆኑ ተንጸባርቋል፡፡  በተለይ በዲፒሎማቶች አማካኝነት የሚገኘው የእርዳታ ገንዘብ ከፍተኛ ቢሆንም በአግባቡ ለህዝብ ከማድረስ ይልቅ ለራስ ጥቅም እንደ ሚውል እና እርዳታውም ሲጠየቅ ጸደይ ላይ ተቀምጦ ገና የበልግ እና የክረምት ዝናብ ስለማይኖር ቀጣይ ህዝባችን

ሊራብ ስለሚችል እርዱን የሚሉ ያልተጨበጡ ግምቶችን በመያዝ በህዝብ ስም ልመና እንደሚካሄድ ያሳየናል፡፡ ነገር ግን የተለመነበት ህዝብ ከተለመነው ገንዘብ በመሰረተ ልማትም ይሁን በሌላ መንገድ ተጠቃሚ እንዳልሆነ ተንጸባርቆ እናገኛለን፡፡ በሌላ በኩል መንግስት ለዜጎች ዘላቂ መፍትሄ ከማምጣት እና የህዝቡን ኑሮ ከመቀየር ይልቅ በሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሮአዊ አደጋ ለችግር የተጋለጡ ሰዎችን ወደ ቋሚ የተረጅነት ስሜት እንዲመጡ ትልቅ አስጸዋጽኦ እንዳለው በተውኔቱ ውስጥ ቀርቦ እናገኘዋለን፡፡ ለምሳሌ የሚከተለውን ማሳያ ማየት እንችላለን፡-

ተሰማ፡- አስታራቂ ሃሳብ አለኝ ክቡራን… /በዜማ/… የእርዳታ ሚኒስቴርም
እርዳታውን ተቀበሎ እንዳመቼነቱ በየሱቁ ይሸጠው፡፡

ተቃዋሚ ድርጀቱም ገንዘቡን ተቀብሎ ጠመንጃና ቦምቡን ይግዛዉ

ምንድነዉ ንትርክ ጉሽማ ሽኩቻ

ተጠቀሙ ዉሰዱት ሁኑ አቻ ለቻ

የእኛ ማዕከልም በቻርተራችን ዘገባ

በማናችሁም የዉስጥ ጉዳይ ጣልቃ ሳንገባ

እናደሳለርን ሁለን በየፈርጁ

እናንተም ተስማሙ አይቆጣ ፈረንጁ! (ለአሊጋዝ)…ጌታዬ የእርስዎም ጉዳይ ከዚሁ ጋር አብሮ ይታያል፡፡ ጥሩ ሃሳብ አይመስላችሁም ክቡራን…

(ጌታቸው ታረቀኝ፤2013፣28-29)

ከላይ ካለው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው የውጭ ጣልቃ ገብነት በእርዳታ ስበብ እንደሆነ ነው፡፡ በተለይ የመንግስትን አቅም ለማዳከም የተቃዎሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን መደገፍ እና በእርዳታ ሰበብ እንዳይስማሙ በማድረግ ሀገርን ማፍረስ የውጭ ሀይሎች ተቀዳሚ ተግባር እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ይህም በስላቅ መንገድ ተንጸባርቆ እናያለን፡፡

በታዳጊ ሀገር ላይ ያሉ መንግስታት የውጭ ሀይሎች በእርዳታ ስበብ የሚጭኑባቸውን ሴራ ካልተቀበሉ በግልጽም ሆነ በስውር በየሚዲያው ማብጠልጠል ዋና ተግባራቸው እንደሆነ በስላቅ መንገድ ቀርቦ እንደሚከተለው እናገኛለን፡፡

> ተሰማ፡- ጓዶች ስነ-ስርአት እንያዝ!...ካልተስማማችሁ የዓለም ጋዜጦች ከመሬት ተነስተዉ ያላረጋችሁት ቢሆንም ባይሆንም ታሪካችሁን አቆሽሸዉ እንዲያቀርቡት ...ሁለታችሁም ግፍና መከራ ማድረሳችሁንም በማስረጃ አቅርበን ...በሰብአዊነት ስም ሌሎች የተኙትን ቀስቅሰን እናነግሳለን፡፡ ሁለታችሁንም የአለም ፍርድ ቤት ባሉት ጓደኞቻችን መጥሪያ እናስልካለን፡፡ ...በድብቅ ያስቀመጥንላችሁን ብር ሁሉ በቢቢሲ ጋዜጠኛ እናስነግራለን...ግን የተማራችሁ ሰዎች በመሆናችሁ እዛ አንደርስም...
>
> አሊጋዝ፡- ተቃውሞ መሰንዘር ይቻላል?
>
> ተሰማ፡- የምን ተቃውሞ?
>
> አሊጋዝ፡- አሁን እርሰዎ በተናገሩት ላይ...

(ጌታቸው ታረቀኝ ፤2013፣31)

የአለም መንግስታት በታዳጊ ሀገሮች ላይ የሚያደርሱት ማስፈራሪያ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ የተገለጸበትን ሁኔታ ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንችላለን፡፡ የበለጸጉ ሀገሮች ለታዳጊ ሀገራት ወዳጅ መስለው እና ረዳት መስለው የሀገራትን መረጃ እና ሚስጥር ከወሰዱ በኋላ እንደማስፈራሪያ እየተጠቀሙ የሀገርን ሀብት በምን መልኩ እንደሚመዘብሩ የተገለጸበት የስላቅ ዘዴ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ተሰሚነት ያላቸውን የአለም ሚዲያዎች በመጠቀም የሀገራትን የወደፊት ሰርቶ የመለወጥ ተስፋ እንዴት እንደሚያጨልሙ በተውኔቱ ውስጥ ተንጸባርቆ እናገኛዋለን፡፡ በዚህም ለስላቅ የቀረቡት የፖለቲካ ፓርቲዎች እና መንግስት ናቸው፡፡ መገሰጽ እና መተቸት የተፈለገውም ኢኮፖለቲካዊ አስተሳሰባቸው በሀገር በቀል አስተሳሰብ የተቃኘ እንዲሆን ለማሳየት ሲሆን በተለይ ህዝብ አምኖ ኃላፊነት የሚሰጣቸው ህዝቡን እንዲያገለግሉ እንጅ ለራሳቸው ጥቅም ብቻ እንዲቆሙ እንዳልሆነ ለማስገንዘብ ነው፡፡ በተለይ ከህዝብ ጋር አብሮ ያልቆመ ፖለቲከኛ መዳረሻው ውድቀት እንደሆነ በስላቅ መንገድ ቀርቦ እናያለን፡፡

በሽልማቱ ተውኔት ውስጥ የምናገኘው ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ስላቅ ተንጸባርቆ እናገኛለን፡፡

*"እጅግ በጣም በደሮ ዘመን"*

(ሽልማቱ፣1983፣171)

ሽልማቱ የተሰኘው ተውኔት መቸቱን ስናይ በአንድ አዳራሽ ውስጥ እና ዘመኑም እጅግ በጣም በድሮ ዘመን ይላል፡፡ ይህ ተውኔት የሚያወራው እውን ስለ ድሮ ዘመን የመንግስት መዋቅር እና አስተዳደር ነው ወይ ስንል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ምክንያቱም የኮሚቴ ሰብሳቢው ንግግር ሲያደርግ የሚያነሳው ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ቀውስ የተፈጸመው የደርግ መጨረሻ የኢህዴግ መጀመሪያ ያለውን እና አሁን ያለንበትን ዘመን የሚያመለክት ነው፡፡ ምን አልባትም ተውኔቱ 1983 ላይ ለመድረክ የበቃ ቢሆንም አሁን ያለንበት ዘመንን ታይቶት ያሳየን ተውኔት ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡ ምክንያቱም በተውኔቱ ይዘት እና ድርጊት የምንመለከተው መንግስት በዚህ ዘመን በተጨባጭ ያሳየበት ተውኔት ነው፡፡ ነገርግን በሀገሪቱ ውስጥ ያለው ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ ነጻነት የተነፈገው ስለሆነ ይህን ችግር ፊት ለፊት መጋፈጥ እስር ቤት ከመወርወር እስከ መገደል ስለሚያደርስ እሱን ለመሸሽ መቸቱን አርዝሞ ተጠቅሞ እናገኘዋለን፡፡ ነገር ግን መስተካከል ያለበትን የመንግስት ስርአት በሳቅ እያዋዛ የሸነቆጠበት ተውኔት ነው፡፡ መንግስት ከራሱ ሹማምንቶች በስተቀር ሌላውን ህዝብ የለውጥ አካል አድርጎ የማበረታቻ ስልት ነድፎ የሰራውን ሰርተሀል ብሎ እውቅና ከመስጠት ፤ያልሰራውን አልሰራህ ብሎ የተጠያቂነት ስልት ዘርግቶ ከመጠየቅ ይልቅ ያልሰራ የሚሸለምበት ፤የሰራ በሰራው ስራ ረክቶ የሚደሰትበት ሳይሆን አንገቱን እንዲደፋ የሚደረግበትን የፖለቲካ ስርአት የተተቸበትን ስልት እናያለን፡፡

በሦስቱም ተውኔቶች በግልጽ በሀገራችን ውስጥ ያለው የፖለቲካው ምህዳር ድቀት ምን ያህል ህዝቡን ዋጋ እያስከፈለው መሆኑን በስላቅ መልኩ መተቸት የተቻለበት ሲሆን የቀረበበት መንገድም በዋናነት የምጸት፣ የማጋነን፣ የማዛባትን እና አለመመጣጠን ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡

### 3.1.2 ማህበራዊ ስላቅ

ማህበራዊ ስላቅ የህብረተሰቡን ወይም የሰውን ተፈጥሮ አንዳንድ ገፅታዎችን ለመተቸት ምፀት ፣ማጋነን ፣ቧልት ወይም አሽሙር ይጠቀማል። በሥስቱም ተውኔቶች ውስጥ ማህበራዊ ስላቅ ተንጸባርቆ እናገኛለን። ለስላቅ የቀረበውም የሀይማኖት ስርአቱ፣ የትምህርት ስርአቱ፣ ቤተሰባዊ ጉዳዮች እና ሌሎች ጉዳዮች በስላቅ ቀርበው የምናገኛቸው ሲሆን እያንዳንዱን እናይለን።

ሀይማኖታዊ ይዘት ያለው ስላቅ በሳጥናኤል አበሳ ተውኔት ውስጥ እናገኛለን። ሚች ከሞተ በኋላ ወደ ገነት እንዲገባ ሲደረግ የነበረው ጥረት አንዱ ሀይማኖታዊ ይዘት ያለው ስላቅ ነው። የሚች የነፍስ አባት መንግስተ ሰማያት ስለሞላ ቦታ ያለ ሲኦል ነው ሲባሉ በምእመኑ ውስጥ ያለውን የእምነት ሁኔታ ግራ በመጋባት ሲያቀርቡ እናያለን።

> "ነፍስ አባት፡-እኔ መችም አልገባኝም…/ራሳቸዉን በሀዘን ይነቀንቃል/ …መቼም ሲመጣ ሳየዉ ሲሳለም ጋቢ ኩታ አለባባሱ… አነሳስ አጎናበሱ… ሲያቀረቅር አይኑን ሲጨፍን ሲዘጋ…ከራሱ ተዘቅዝቆ በሆዱ ሲዘረጋ፤ …ፅናፅል አያያዙ ሲወርብ ከበሮ ሲደልቅ፤ ከታቦቱ ፊት ፊት እየዳኸ ሲወድቅ…መቋሚያ አያያዙ ዜማ አነሳሱ፤ መቁጠሪያ አይጠፋም ደሞ ከኪሱ። ለስጋዎደሙ ሲጋፉ፤ በግምባሩ ሲወድቅ ከመቅደሱ ደጃፍ ሲደፋ….አጥሩን በሩን ይዞ ፋካሬን ኤሎሄን ሲል…ሲያማትብ ሲያንጋጥጥ ወደ ላይ፤ ለጠበል ሲሽቀዳደም ፤ መቼም እንደሱ ማንም የለም። ድርሳኑን ወንጌሉን በቃል እሚወጣ…ገበታ ቤት ቆሞ ግብር እሚያበላ እሚያጠጣ……ይሄ መቼም እማይታመን ነዉ…እንዴት ነዉ ለሱ ቦታ የማይኖረዉ?...ነገሩ ትንሽ ችግር አለዉ…"
>
> (ጌታቸው ታረቀኝ፣ 2007፣8)

የሚች የነፍስ አባት ሆነው መንፈሳዊ አገልግሎት በሚሰጧቸው የንስሀ ልጆቻቸው ላይ ትልቅ ጥያቄ ሲያነሱ እናያለን። ሀይማኖታዊ ስርአት የሚከተሉ መስለው አስመሳይ አማኞች እንዳሉ እና እነዚህ አማኞች የእውነት አምነው ትክክለኛውን መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲሰጡ እና ትክክለኛውን ሀይማኖታዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ካልተደረገ አስመሳይ አማኝ እና አስመሳይ

አገልጋይ ተያይዘው እንደሚወድቁ በስላቅ መልኩ የቀረበ ሀይማኖታዊ ይዘት እናገኛለን፡፡ በዚህ ተውኔት ለስላቅ ቀርቦ የምናገኘው አስመሳይ  የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡

በተጨማሪም ሳጥናኤል እንኳን አጥምቁኝ ፣ፈውሱኝ፣ዘይሩልኝ፣ ዱዋ አድርጉልኝ እንኳ ቢባሉ በሰው ልጅ ጭንቀት እና ህመም የሚደሰቱ የእምነቱ አገልጋዮች እሽሊሉ የማይችሉ ሆድ አደር አገልጋዮች እንዳሉ የቀረበበትን ሁኔታ እናያለን፡፡ ስለዚህ በዚህ ተውኔት ውስጥ ሀይማኖታዊ የሆኑ ጉዳዮች በስላቅ መንገድ ቀርበው እናገኛለን፡፡

ሌላው የቀረበው ማህበራዊ ስላቅ የትምህር ስርአቱ ነው፡፡ ለዚህም በቤጊዮሎጂ ተውኔት ውስጥ የትምህርት ስርአቱ ፈተና ውስጥ መውደቁን በስላቅ መልኩ ቀርቦ እናገኘዋለን፡፡  **"በልመና የትምህርት ዘርፍ የሚማሩ ማንኛውም የከፈለ ተማሪ ዲግሪ ይሰጠዋል"**፡፡ ይህ ሀሳብ የሚያመለክተን ሰው ከከፈለ የትኛውም የግል ትምህርት ተቋማት ብቃት ያለው ተማሪ ከማስመረቅ ይልቅ ዋና አላማው ወደ ገንዘብ መሰብሰብ መሰማራቱን የሚያሳይ ነው፡፡ ተሰማ የተሰኘው ገጸባህሪ ምንም ሳይማር ኢንጅነር፣ዶክተር፣ የፕሮፌሰርነት ማእረግ እንዳለው ተደርጎ ተገልጾም እናገኛለን፡፡ ይህም ሳይማሩ ምንም አይነት የትምህርት ማስረጃ ሳይኖራቸው፣ ቢኖራቸውም የሀሰት የትምህርት ማስረጃ ይዘው ምሁር ሳይሆኑ ምሁርነን ብለው ሀገር የሚያጠፉ ሰዎች ላይ የቀረበ ትችት ነው፡፡ እንዲሁም የሀገሪቱ የትምህርት አሰጣጥ ችግር ውስጥ ያለ መሆኑን ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡፡(አጽንኦት የኔ)

የትዳር ሁኔታ  የቀረበ በስላቅ መልኩ ቀርቦ እናገኘዋለን፡፡ በትዳር ላይ መባለግ እና ዝሙት በስላቅ መልኩ ቀርቦ እናገኛለን፡፡ ***በሳጥናኤል አበሳ*** ተውኔት ውስጥ ወሲብ አንዱ እና ዋነኛው ሲኦል ውስጥ ሳይቀር የሚፈጸም ቅሌት እንደሆነ የቀረበበት ሁኔታ እናገኛለን፡፡  ስለዚህ በዚህ ተውኔት ውስጥ ወሲብ አንዱ መሳለቂያ ሆኖ የቀረበ ሲሆን የወሲብ ቅሌቱ በየቦታው ልጅ መውለድን እና ልጆች ያላሳዳጊ እንዲቀሩ እያደረገ እንደሆነ ተገልጾ እናገኘዋለን፡፡ ልቅ በሆነ የወሲብ ቅሌት በተለይ አባት የሌላቸው ልጆች እንደሚፈጠሩ በስላቅ መንገድ የቀረበ ሲሆን **በሽልማቱ** ተውኔት ውስጥ ደግሞ በትዳር ላይ መባለግ እና ህሌና ቢስ በመሆን እንዴት በሌሎች ዘንድ እንደምናሳብብ በተለይ የቤት ሰራተኞች ከአባወራዎች ወልደው እንዴት እንደሚካዱ እና እንግልት እንደሚቀርብባቸው በስላቅ መልኩ የቀረበበትን ሂደት እናያለን፡፡

***በቤጊዮሎጂ*** ተውኔት ውስጥ ፍች፣ ሞት፣ መደፈር፣ ፍትህ ማጣት፣ ድህነት እና መሰል ጉዳዮች የተነሱ ሲሆን የባልና ሚስት ፍች በልጆች ላይ ሊያደርስ የሚችለው  አካላዊ እና

ስነልቦናዊ ተጽኖ በጭብጥነት የተነሳ ሲሆን ከተማሪዎች ውስጥ አንዷ ተማሪ የተፈጠረላትን ታሪክ ለልሄቃኑ ስታቀርብ መረዳት ይቻላል፡፡

> ሴቶች ኪነት2፡- አባትና እናቴ ድብድቡ ሲበቃቸዉ ፤ በቃ ይፊቱ ተባሉና ተለያዩ፡ ፡ እኔም ገና እፍይ ብዬ ሳልተነፍስ የእናቴ አዲስ ቦይ ፍሬንድ ማታ ላይ በተኛሁበት ዘሎ እላዬ ላይ ሲከመር፤ ምናባቱ አልኩኝና በጥፊ በቡጥጫ ብዬዉ ልነሳ ስል ፤ ጠጉሬን ይዞ መቼ ሊለቀኝ …እንዳልጮህ ደግሞ በሌላኛዉ እጁ አፌን ሲይዘኝ ጣቱን ንክስ አድርጌ ...ቢጮህ እንኳ አልለቅም ብዬ በድንጋጤ ሳላዉቀዉ ጣቱን ቅርጥም አድርጌ ቆረጥኩታ፡፡ እኔ መች አዉቄ …ደንግጩ ነፍሴን አላዉቀዉም ነበር… በኋላ በፖሊስ ተይዤ በፍርድ ቤት አንቺ ነሽ ጥፋተኛ …‹‹ቡዳ የሰዉ ስጋ የምትበይ›› ተብዬ ሁለት አመት ከርቸሌ፡፡
>
> (ጌታቸው ታረቀኝ፣8፣2013)

በባለታሪኳ ላይ የመጀመሪያው የእናት እና አባቷ ባለመስማማት መፋታት የሚፈጥርባት የስነልቦና ችግር ሲኖር በሁለተኛ ደረጃ በእናቷ ባል የአስገድዶ መድፈር ጥቃት መድረሱ ሌላ አካላዊ እና ስነልቦናዊ ጫና የሚፈጥር ነው፡፡  አስገድዶ ለመድፈር የሞከረው አካል ሳይቀጣ ለላመደፈር ብላ በወሰደችው እርምጃ  ባደረሰችው አካላዊ ጉዳት “ቡዳ” ተብላ መታሰሯ የሚፈጥረው ስነልቦናዊ ችግር እንዳለ እንረዳለን፡፡ በተጨማሪም  ፍትህ ሲዛባ እና መፈረድ በሌለበት አካል ሲፈረድ እናስተውላለን፡፡ በተለይ የፍትህ ስርዓቱ ምን ያህል ኢ-ፍትዊ እንደሆነ የተገለጸበት ሁኔታ እናገኛለን፡፡ ስለዚህ በዚህ ተውኔት ውስጥ የፍትህ እጦት የቤተሰብ መበተን የሚያደርሰው ማህበራዊ ጫና በጭብጥነት የቀረበ ሲሆን የቀረበበት ስልት ግን ስላቅን በመጠቀም ነው፡፡

በአጠቃላይ በሦስቱም ተውኔቶች የቀረቡት ማህበራዊ ስላቆች ያነሱት ይዘት የተለያያ ቢመስልም በማህበረሰቡ ዘንድ ቀውስ የሚያስከትሉ፣ ማህበረሰቡን የሚጎዱ ጉዳዮች በስላቅ መንገድ የቀረቡ ሲሆን በስነ-ምግባር የታነጸ፣ ጥሩ ስብዕና ያለው፣ ግለኝነት ሳይሆን እኛነት እንዲጎለብት የሚጠቁም ስላቅ ተንጸባርቆ እናገኛለን፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት  ስላቅ በጌታቸው ታረቀኝ የተውኔት ስራዎች የሚል ነው። ከጌታቸው ታረቀኝ ስራዎች ውስጥ  በሳጥናኤል አበሳ፣በቤጊዮሎጅ እና በሽልማቱ ተውኔቶች ከስላቅ ንድፈ ሃሳብ አንፃር ምልከታ የተደረገበት ነው። በእነዚህ ተውኔቶች የታዩት የስላቅ ዘዴ የሆኑት  ማጋነን ፣ ማዛባት፣ አለመመጣጠን እና ምጸት  እንዴት እንደተንጸባረቁ የስላቅ ንድፈ ሀሳብን ማንጸሪያ በማድረግ ለመተንተን ተችሏል።

ተውኔቶቹ በየዘመኑ የነበረውን ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በስላቅ ዘዴ ለማሳየት ተችሏል። በእነዚህ ተውኔቶች ውስጥ በምናገኛቸው ገፀ ባህሪያት አማካኝነት ስላቅ እንዴት እንደቀረበ እና የስላቁ ታላሚ የትኛው አካል እንደሆነ ተተንትኖበታል።

በተውኔቶቹ  ውስጥ የተንጸባረቀው ይዘት ስላቅን በመጠቀም ለመተቸት  የስላቅ ዘዴዎችን በመጠቀም ተግሳጽ ሲቀርብ  አይተናል። በተለይም በህዝቡ ላይ የስብእና መንደል መኖሩ የሰው ልጅ  እርሰ በርስ እዳይተዛዘን እንዳደረገው፣ እኛነት የሚለው አስተሳሰብ ቀርቶ እኔነት መግነኑን፣የሀይማኖት  አባቶች ሳይቀሩ የስብእና መንደል እንደገጠማቸው፣ ምእመኑ ከላይ ሲታዩ እና ውስጣቸው ሲታይ የሚቃረን መሆኑ፣ የፖለቲካው አለመረጋጋት በሀገር ላይ እያደረሰ ያለው ማህበራዊ እናኢኮኖሚያዊ ቀውስ ምን ላይ እንደደረሰ፣ የፖለቲካ አመራሮች ኃላፊነት የማይሰማቸው መሆኑ፣ በህዝቡ ላይ ያለው ኢኮኖሚያዊ  እና ፖለቲካዊ ጫና የውጭ ሀገር ተጽእኖ እንዳለበት  በስላቅ መንገድ  እንዴት እንደቀረበ ተፈትሾበታል።

እነዚህን እና መሰል ይዘቶችን  ለማንፀባረቅ እንደ ስልት የሚጠቀሙ የተለያዩ የስለቅ ዘዴዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል  በተመረጡት ተውኔቶች በስፋት እና በተደጋጋሚ ከምናገኛቸው መካከል ማጋነን(ግነት) መጠቀም አንዱ ነው። በተውኔቱ ውስጥ መስተካከል ያለበት ጉዳይ እንዲስተካከል እና ለውጥ እንዲመጣ በማሰብ የግነት ዘዴን በስፋት ተንጸባርቆ አግኝተናል። አለመመጣጠን  እንዲሁ የእነዚህ ተውኔቶች የማቅረቢያ ዘዴ ነው።  ድርጊቱ ከሁኔታው ጋር በማይመጣጠን መንገድ በማቅረብ መስተካከል ያለበት ጉዳይ እንዲስተካከል ይህ የስላቅ ዘዴ ቀርቦ አግኝተናል። በተለይም ሀይማኖታዊ የሆኑ ህጸጾች በዚህ ዘዴ ቀርበው በስፋት አይተናል። ምጸት እና ማዛባትም በተመረጡት ተውኔት ውስጥ በስፋት የታየ ሲሆን የትምህርት ተቋማት

እና የእምነት ተቋማት ካሉበት ችግር እንዲወጹጡ እና በተቋማቱ ውስጥ ያለውን ችግር ጥቆማ ተሰጥቶበት አይተናል፡፡

እነዚህን የስላቅ ዘዴዎች በመጠቀም ስላቁ መቅረቡ ለስነጽሁፍ የሰጠው ስነጽሁፋዊ ውበት አለው፡፡ የተውኔቶቹ የቋንቋ አጠቃቀም ምጥን እና ገላጭ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ይኸውም ተውኔቱ እንዳይሰለች እና በተውኔቱ ውስጥ የተነሱት ይዘቶች ለዛ ባለው መንገድ እንዲቀርብ አድርጎታል፡፡

# አባሪዎች

## አባሪ 1፡ የሳጥናኤል አበሳ አጽመ ታሪክ

በሳጥናኤል አበሳ ተውኔት ውስጥ በዋናነት 10 ገጸ ባህርያት አሉ፡፡ በዚህ ተውኔት ውስጥ የሰው ልጅ  ክፋት፣ተንኮል፣ ምቀኝነት፣ አለመተሳሰብ እና መሰል ኢ-ሰብአዊ ጉዳዮችን እያነሳ የሚሞግት ነው፡፡ ታሪኩ የሚጀምረው ሚችን በነፍስ አባት አማካኝነት ወደገነት ለማስገባት በሚደረግ ጥረት ነው፡፡ ሚች በሰራው ክፉ ስራ መንግስተ ሰማያት አትገባም ተብሎ አማራጩ ሲኦል እንደሆነ ሲነገረው የነፍስ አባት እና የሚች እናት ይደነግጣሉ፡፡ በሌላ በኩል አልቃሾች የሚችን ተንኮል ያውቁ ስለነበር ሲደሰቱ የሚያሳይ ነው፡፡  ሳጥናኤል የተሰጠውን የተኮነነ ነፍስ ወደ ገሀነበ እሳት በመውሰድ ሎታንን ያስጎበኘዋል፡፡ ሚች በጉብኝቱ እነማን ሲኦል ውስጥ እናዳሉ ከሳጥናኤል ጋር በነበረው ቆይታ ይተዋወቃል፡፡ ሳጥናኤል በሲኦል ያሉ ነፍሶችን ሲገልጽ በአብዛኛው አቶ የሚባል ስም የሌላቸው ኢንጅነሮች፣ ዶክተሮች፣ ደላሎች፣ አጭበርባሪዎች እና ትላልቅ የፖለቲካ እና የጥበቡ ሰዎች እንዳሉ ስም እየጠራ ያስተዋውቃል፡፡ በዚህም በአለም ላይ ያለውን ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳይ እያነሳ ገለጻ ሲያደርግ ያሣየናል፡፡

ሳጥናኤል ለሚች አስጎብኝቶ ከጨረሰ በኋላ  ለእናኑ ከእሳት ማውጣት እና እሳት ማስገባት ሰለቸኝ ተመምቄ ሰው መሆን እፈላጋለሁ   በማለት ወደ ሀይማኖት አባቶች ይሄዳል፡፡ የሀይማኖት አባቶች ግን ከራሳቸው ጥቅም ጋር በማሰብ ሰው መሆን ምኞቱን  ሲከለክሉት ያሳየናል፡፡  ሳጥናኤል እሱ ሰው ቢሆን እና ተንኮል እና ክፋት ቢተው የአለም ህዝብ ሰላም እንደሚሆን ቢያስረዳም የሀይማኖት አባቶች ሀይማኖታዊ   ተልኳቸውን በመዘንጋት በእንቢታቸው ይጸናሉ፡፡ ሳጥናኤልም ወደ ሲኦል በመመለስ  መደበኛ የማቃጠል ስራውን ሲፈጽም የሚያሳይ ነው፡፡

## አባሪ 2፡ ቤጌዮሎጅ (የልመና ጥበብ) አጽመ ታርክ

በዚህ ተውኔት ውስጥ 12 ገጸ-ባህርያት አሉ፡፡ ቤጊዮሎጅ ተውኔት የልመና ጥበብ የሚማሩበት ሳይሳዊ የልመና ስልት ነው፡፡ በዚህ ተውኔት ውስጥ ተሰማ የተሰኘው ገፀባህሪ ተማሪዎች እንዴት ትምህርቱን መማር እንዳለባቸው እና እንዴት ሆነው አለም አቀፍ ለማኝ ሆነው እንደሚወጡ ለተመራቂ ተማሪዎች ንግግር ሲያደርግ የሚጀምር ነው፡፡ የልመናው ስልት ከመደበኛ ለማኞች ልቆ በመገኘት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት ሀብታም መሆን እንደሚቻል የሚያሳይ ነው፡፡

አላዛር በልመና የሚማሩትን ተማሪዎች የሚያስተምር ሲሆን አለማቀፋዊ የልመናስልት ምን መምሰ እንዳለበት ለተማሪዎች ሲያስገነዝብ ያሳያል፡፡ ጥጋቤ፣ቤተልሄም፣ምስክር እና ሌሎች ተማሪዎች ልመና የሚማሩ ሲሆኑ ከዚህ በፊት እንዴት ይለምኑ እንደነበር ቶሞክሮአቸውን ለተማሪዎች ያካፍላሉ፡፡ አላዛር የተማሪዎችን ተሞክሮ በመስማት የትኛው ልመና ስልት አዋጭ እንደሆነ ትንታኔ ይሰጣል፡፡

በሌላ በኩል ተሰማ ለመንግስት እና ለተቃዋሚ ፓሪዎች እርዳታ ከውጭ በማምጣት ተስማምተው እንዲካፈሉ ከልተስማሙ ግን ሌሎችን ተቃዋሚ በመቀስቀስ ችግር ውስጥ ሊከቷቸው እንደሚችል ይዝታሉ፡፡ ዛቻው በዚህ ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን የማይስማሙ ከሆነ የውጭ ሚዲያዎችን በመጠቀም ስም በማጥፋት በሀገራቸው ላይ ኢኮኖሚያዊ ጫና እንደሚፈጥሩ ተሰማ ይገልጻል፡፡ መንግስትን ወክላ የቀረበችው ሮዚና ተቃዋሚዎች ወንበዴ ናቸው በማለት ለማስረዳት ብትሞክርም አድማጭ ታጣለች፡፡ ተቃዋሚዎች እና መንግስት ከውጭ የመጣውን እርዳታ በስምምነት ይካፈላሉ፡፡

ተማሪዎች ልመና እንዲስፋፋ ሰርቶ ማደር እንዲጠፋ በሀገሪቱ ውስጥ ጦርነት፣ሽብርተኝነት፣ ስደት እና ልመና እንዲስፋፋ የሚሰብኩበት ነው፡፡

## አባሪ 3 የሽልማቱ ተውኔት አጽመ ታሪክ

ሽልማቱ ተውኔት ባለ አንድ ገቢረ ሲሆን 4 ገጸ ባህሪያትያሉት ተውኔት ነው፡፡ ታሪኩ የሚጀምረው አንድ መስሪያቤት የተሸለ የስራ አፈጻጸም ያላቸውን ሰራተኞች ለማበረታት ሽልማቱን የሚያዘጋጅ እና የተሸለ የስራ አፈጻጸም ያላቸውን ሰራተኞች የሚመርጥ ኮሚቴ ተዋቅሮለት ነው፡፡ የኮሚቴው ሰብሳቢ ዘርጋባቸው ነው፡፡ ዘርጋባቸው የኮሚቴዎችን የስራ ድካም፣ተሸላሚዎችን ለመለየት የሄዱበትን የማጣራት ሂደት ለተሰብሳቢዎች ይገልጻል፡፡ ከገለጻው በኋላ ሽልማቱ ይጀመራል ፡፡ ሽልማቱን አራቱ የሽልማት ኮሚቴዎች ቦታ እየተቀያየሩ ይወስዳሉ፡፡ ሽልማቱ ሲያበቃ የተዘጋጀው የምሳ ግብዣ  አቅራቢዎች እንዳልተመቻቸው ለተሰብሳቢዎች  ተነግሮ የሽልማቱን ሂደት ሲጠናቀቅ የሚያሳይ ነው፡፡

# አባሪ 4 ስለተውኔቶቹ የህትመት ዘመን ማብራርያ

ቤጊዮሎጅ መጀመሪያ የተጻፈው 1984 ሲሆን ሁለተኛው የእንስሳት ጥናት እና ሌሎች ሌሎች የትያትር ጨዋታዎች በሚል መድብል 2007ዓ.ም የታተመ ነው፡፡ ተሻሽሎ pdf የተዘጋጀ ደግሞ 2013 ነው፡፡ ለዚህ ጥናት አጥኝዋ የተጠቀመችው ተሻሽሎ የተዘጋጀውን የ2013 ቱን ለትንተና ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

የሳጥናኤል አበሳ 2007 የታተመ ሲሆን ለዚህ ጥናት ለትንተና ጥቅም ላይ የዋለው የእንስሳት ጥናት እና ሌሎች ሌሎች የትያትር ጨዋታዎች በሚል መድብል 2007ዓ.ም የታተመ ነው፡፡

ሽልማቱ በ1983 የተጻፈ ሲሆን የእንስሳት ጥናት እና ሌሎች ሌሎች የትያትር ጨዋታዎች መድብል 2007 ዓ.ም ታትሟል፡፡ ለዚህም ጥናት ትንተና ጥቅምላይ የዋለው የእንስሳት ጥናት እና ሌሎች ሌሎች የትያትር ጨዋታዎች በሚል መድብል 2007ዓ.ም የታተመው ነው፡፡

## አባሪ 5 የቃላት የመገኛ ቋንቋቸው ፍች

- ስላቅ (satire)
- የስላቅ ዘዴዎች (Techniques of Satire)
- ማጋነን (Exaggeration)
- ምጸት ( Irony)
- ፓሮዲ (Parody)
- ተገላቢጦሽ (Reversal)
- አሻሚነት (Ambiguity)
- ማዛባትን (distortion)
- አቅጣጫ ማስያዝን (indirection)
- ውጫዊነትን (externality)
- አጭርነትን (brevity)
- ልዩነትን (variety)
- ከመጠን በላይ መናገር እና ማቃለል (Overstating and understating)
- ቡርሌስክ (Burlesque)
- ካሪካቸር፡- Caricature

# ዋቢጽሁፎች

መጽሐፍ ቅዱስ። (2001)። የብሉይ እና የሀዲስ ኪዳን መጽሐፍት።የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር።አዲስ አበባ።

ባህሩ ዘርጋው።2006) ።*ዘርጋው ከፍተኛ የአማርኛ መዝገበ ቃላት።* አዲስ አበባ።ሮሆቦት አታሚዎች።

አንተነህ አወቀ። (2001*)።የአማርኛ ስነጽሁፍ ባሳለፍነው ሚሊኒየም።* የአማራ ህዝብ ባህልና ቋንቋ።

ዘሪሁን አስፋው። (1992) ። *የስነፅሁፍ መሠረታዊያን።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል። (1993) *።የአማርኛ መዝገበ ቃላት* ፤አዲስ አበባ።አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ደበበ ሠይፉ። (1973) ። *የቲያትር ጥበብ።* አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፣

ጌታቸው ታረቀኝ። (2013) ። *ቤጊዮሎጂ (የልመና ጥበብ)።*PDF

ጌታቸው ታረቀኝ። (2007) ። *የእንስሳት ጥናት እና ሌሎች ሌሎች የትያትር ጨዋታዎች* ። አዲስ አበባ።

ፈንታሁን እንግዳ። (1992)። *የተውኔት አጻጻፍ ዘዴ* ።አዲስ አበባ።

Agabey, G. (2021). Satıre as a form of expressıon ın Azerbaijan. Revista Universidad y Sociedad, 13(5), 431-438

Applebee, Arthur N., Ed. The Language of Literature: British Literature. Evanston, IL: McDougal Littell, 1997 the senior textbook used in HISD.

*Bates, A.ed. (1906), "Political and social satires of Aristophanes", The Drama, Its History, Literature and Influence on*

Bloom, Edward A. and Lillian D. Bloom.(1979). Satire's Persuasive Voice. Ithaca and London: Cornell University

Burke, K. (1984). Attitudes toward history. Berkeley: University of California Press.

Camus, Albert. (2000). the Myth of Sisyphus and Other Essay. Trans. JustinO.Brien.New York: Knopf.

Cornwell, N. (2013) .The absurd in literature; Manchester University Press; Annotated edition (August 30, 2006)

Chapman .J & H. C. Foot (Eds.), It's a Funny Thing, Humour [Welsh Branch, British Psychological Society] (pp. 13—16). Oxford: Pergamon Press.

Charles A. Knight.(2004) *.The Literature of Satire;* Cambridge Unversity Press, New York*..*

Combs.L. (2016).The Power of Politcal satire: dose it influence viewers to participate in politics? Bachelor of Arts Strategic Communication, Oklahoma State University.

Feinberg, L. (1967). Introduction to Satire.Iowa: Iowa State University Press.

Fletcher, M.D. (1987) Contemporary Political Satire: Narrative Strategies in the Post-modern Context. Lanham, University Press of America.

Frye, N. (1971a). The mythos of winter: irony and satire. In Paulson, 233-248.

Frye, N. (1957), Anatomy of Criticism (in particular the discussion of the 4 "myths").comparison, analogy, and double entendre are all frequently used in satirical speech and writing.

Green.P.(1927).https://www.uh.edu/honors/Programs-Minors/honors-and-the-schools/houston-teachers-institute/curriculum-units/pdfs/2008/comedy/green-08-comedy.pdf

Griffin, D. (1994). Satire: A Critical Reintroduction. Kentucky: University Press of Kentucky.

Hamer, T. (2020). A Critique of Humoristic Absurdism. Problematizing the legitimacy of a humoristic disposition toward the Absurd; Utrecht University.

Harris,R.(1990).The Purpose and Method of Satire, Virtual Salt, 1- http://www.virtualsalt.com/satire.htm

Kane, T. R., Suls, J., & Tedeschi, J. T. (1977). Humour as a tool of social interaction.

Kernan, A. 1973. Satire. In Dictionary of the history if ideas. Studies of selected pivotal ideas, ed. P. P. Wiener, 211—217. New York: Scribner

Lazar .G.(1993). Literature and Language Teaching; A guide for teachers and train-ers, Cambridge Unversity Press.

Luke. A. (2023).https://smartblogger.com/satire-examples/

Mitchell.(2003). Characteristics of Tragedy &Com .http://www.dbu.edu/mitchell/comedytr.htm (April 17, 2008)

Pollard, A. (1970). Satire [The Critical Idiom Series]. London: Routledge

Press, An entire book about the different kinds of satire.

Robert Harris, (2004).The Purpose and Method of Satire.

Simpson .P. (1959) .On the Discourse of Satire: To wards a stylistic model of satirical hu-mour. Queen's University Belfast

SntaYehu Gnet .(2008).Political and soclal satire as reflected in Bewketu Seyum's En-qilf ena Edmie and Berari Kiteloch, Addis Ababa University.

The New Encyclopedia Britannica (2005, 23,173). Chicago: University of Chicago.

The New Encyclopedia Britannica (1993, 10,467). Chicago: University of Chicago.

The Use of Satire and Comedy in Literature Works. (2018, Feb 10). Retrieved from https://graduateway.com/the-use-of-satire-and-comedy-in-literature-works/

Ugolini, P. (2016) .https://www.researchgate.net/publication/308861073